https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

29181.doc

34329.doc

36749.doc

39462.doc

40229.doc

42569.doc

42903.doc

43067.doc

43499.doc

43527.doc

43561.doc

43657.doc

43731.doc

43886.doc

44164.doc

44720.doc

45882.doc

45886.doc

45889.doc

45982.doc

46117.doc

46958.doc

47005.doc

47035.doc

47469.doc

47487.doc

48266.doc

50157.doc

452661.doc

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሠበር መ/ቁጥር 29181

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተገኔ ጌታነህ
2. መንበረፀሐይ ታደሰ
3. ሐጎስ ወልዱ
4. ሂሩት መለሰ
5. ታፈሰ ይርጋ
6. አልማው ወሌ
7. ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ልየው ቾኮል
2. " ሚሊዮን መንግስቱ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በብድር የተሠጠን ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ጋር በተያያዘ ዕዳው እንደተከፈለ ሲቆጠር የሚችልበትን የሕግ አግባብና ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ ለንግድ ስራቸው ማስፋፊያ የሚውል ታህሳስ 11 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) የተበደሩ መሆኑን፣ ዋናውን ብድርና ልዩ ልዩ ወጪዎችን ጨምረው በዓመት 14% /አስራ አራት በመቶ/ ወለድ እየታሰበ ከታህሳስ 11 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ ብር 900.00 እየከፈሉ ሳያቋርጡ እስከ ታህሳስ 10 ቀን 1988 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍለው ለማጠናቀቅ መስማማታቸውን፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ለተበደረው ለዚሁ የገንዘብ መጠን የአንድነትና የነጠላ ዋስ በመሆን መፈረማቸውን በመግለፅ ዋናውን ብድር ብር 10,000.00 እስከ ሐምሌ 24 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ የታሰበ ወለድ ብር 13,783.64(አስራ ሦስት ሺህ ሠባት መቶ ሰማንያ ሦስት ብር ከስድሳ አራት ሣንቲም) እና ለኢንሹራንስ የተከፈለ ብር 1,813.80(አንድ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሦስት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም) ስለመሆኑ በመዘርዘር በድምሩ ብር 25,097.54(ሃያ አምስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሣንቲም) ያልተከፈለ ዕዳ የመቀጫ ወለድ 3%

https://chilot.me https://t.me/ethiopianlegalbrief join telegram

ጨምሮ በድምሩ 17% ወለድ እየታሰበ ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ቀርበው የቀረበባቸውን ክስ በመቃወም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፣ መክፈል ያልቻልኩት በደረሰብኝ ኪሳራ ስለሆነ ለመክፈል የማልችል ስለሆነ ባንኩ ተገንዝቦ ከአስር ዓመት በላይ ስለቆየ ክሱ ውድቅ ነው የሚሉትን ክርክሮች አንስተው ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ባንኩ በተበዳሪው ላይ ክስ መስርቶ ሀብቱን ሣያጣራ በዋሱ ላይ ክስ መመስረቱ ያላግባብ መሆኑን፣ ባንኩ በአዋጅ በተሠጠው ሥልጣን መጠቀም ሲገባው ክስ መመስረቱም ከአዋጁ ዓላማ ውጪ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሁኖ በነፃ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ የሠጠው ብድር ክፊያ መጠናቀቅ የነበረበት በውላቸው መሠረት እስከ ታህሳስ 10 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፣ አመልካች በዚህ ጊዜ ውስጥ አልጠየቀም በፍ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሠረት አበዳሪው የተወሠነ ጊዜ ተበጅቶለት በዓመት ወይም ከዓመት በፊት የሚከፈለውን የገንዘብ ዕዳ ሣይጠይቅ እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ከቆየና ከሁለት ዓመት ጊዜ በኋላ ከጠየቀ ገንዘቡ በተበዳሪው እንደተከፈለ ወይም ዕዳው ምህረት እንደተደረገለት ሕግ ግምት ይወስዳል፣ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በሠ/መ/ቁጥር 17068 በሰጠው ውሣኔ ላይ በሕግ ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ክርክር ተከሳሽ ፍሬ ነገሩን ካደ አልካደም ፍርድ ቤቶች የሕግ ግምቱን ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው የሚል አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሠጥቷል የሚል ምክንያት በመያዝ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፣ ገንዘቡ በጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው የተጠሪዎች ግዴታ ቀሪ ሁኗል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 22 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት 3(ሦስት) ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ መሠረት ያደረገው ድንጋጌ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በፍ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ የሰበር ችሎት ለፍ/ህ/ቁጥር 2024 የሰጠው ትርጉምም አምና ለሚከራከር ተከራካሪ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ተሽሮ

ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ መሠረት በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸውን ብር 25097.54(ሃያ አምስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሣንቲም) ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 17% (አስራ ሰባት በመቶ) ወለድ እየታሰበ ከክርክሩ ወጪና ኪሣራ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የሠበር ሠሚ ችሎትም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በፍ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሰረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል ውድቅ እንዲሆን የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ያልቀረቡ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 28 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የፍ/ህ/ቀጥር 2024(ረ) ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆኑን፣ የሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 17068 የሠጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆኑን ዕዳው አለመከፈሉን አምነው የተከራከሩት ሁኔታ አለመኖሩን ገልፀው የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሲፀና ይገባል በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ሐምሌ 25 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረት ውሳኔ እንዲሠጥ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሲታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪዎች ያበደረውን ብድርና ወለድ እንደተከፈለው ይቆጠራል በማለት ፍርድ ለመስጠት መሰረት ያደረጉት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተውን የሕግ ግምት በመሆኑ በዚህ አንቀፅ የተጠቀሰው የሕግ ግምት ለባንኮች የሚሰራ መሆን አለመሆኑ ይሰራል የሚባል ቢሆን አመልካች በምስክር፣ በሰነድና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ግምቱን ለማስተባበል ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉት ነጥቦች መፈታት ያለባቸው ጭብጦች ሁነው አግኝተናቸዋል፡፡ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት በቅድሚያ የሕግ ግምት ምንነት ባሕርያት በጠቀሳሳውና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌን ይዘትና ባህሪን በትኩረት ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡

የሕግ ግምት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ስንመለከተው ሕግ አውጪውን ለግምት መነሻ ከሚሆኑ የተወሰኑ ፍሬ ጉዳዮች በመነሳት አንድ ድርጊት ተፈፅሟል ወይም አልተፈፀመም ብሎ የሚደርስበትን መደምደሚያ በሕግ የሚደነግጋቸውን ሁኔታዎች የሚያመላክት ነው፡፡ የሕግ ግምቶች ዳኞች አንድን ፍሬ ጉዳይ የተፈፀመ ወይም ያልተፈፀመ መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ ረገድ የሚገጥማቸውን ክፍተት በመሙላትና የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን ጫናውን

በማቃለል በኩል የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑ ይታመናል፡፡ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይም የሕግ የህሊና ግምት ዓይነተኛ ዓላማ የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን ጫና የማቃለል፣ ውሳኔ ሠጪ አካልንም ተገቢና ግልፅ ሆኖ የሚታይ የጠራ ማስረጃ ካላገኘ ወደ ውሳኔ በአፋጣኝ እና በቀላሉ እንዲደርስ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሠጥ መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ወደሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስንመጣ ይህ ድንጋጌ በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን (Legal Presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎቹ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት የሕግ የህሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ አይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ ድንጋጌው በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሲከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች (እዳዎች) በዚሁ የሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆነ ክፍያውን(እዳውን) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደተከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት ያስገነዝባል፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ፣ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ በተጠቀሰው ቁጥር በፊደል(ረ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡

<u>ቁ 2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው

(ረ) በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሲከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጂም፡-

<u>Art.2024 presumption of payment after two years</u>

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት አቀራረፅ እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች(ክፍያዎች) እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሕግ ግምት የሚወሰድባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጋጌው ፊደል(ረ) ስር የተመለከተው ሲታይ

በብድር የተሠጠ ወይም ስማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ይህ ድንጋጌ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ግምት መሆኑ የመጀመሪያው ባህሪው ሲሆን ማናቸውም የተፈጥሮም (ባንክና ሌሎች አበዳሪ ተቋማትም) ሆነ የሕግ ሰው የገንዘብ ብድር ካበደረ በኋላ ብድሩ ተከፍሎ የሚያልቅበትን የጊዜ ገደብ ካበቃ ከሁለት ዓመት በኋላ የብድሩ የወለድ ይከፈለኝ ጥያቄ በሕግ እንደተከፈለ የሚገመት መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው የሕግ ግምት ለዳኞች የሕሊና ሚዛን እድል የማይሰጥ ዳኞች የነገሩን ሁኔታ በማየት ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት፣ ከነገሩ ሁኔታ አንፃር አስፈላጊ ሆኖ ካላገኙት የሚተውት ፈቃጅ የሆነ የሕግ ግምት አይደለም፡፡ በአንጻሩ ይኸው ድንጋጌ የሚሸፍነው ጉዳይ ባጋጠማቸው ጊዜ ዳኞች ያለምርጫ ሊከተሉትና ሊፈፅሙት የሚገባ አስገዳጅ የሕግ ግምት ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ ስር የሰፈረው የሕግ ግምት ሁሉንም አይነት ዕዳዎች በአጠቃላይ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ባንኮች በሚሠጧቸው ብድሮችም ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ጭምር የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ይኸው አንቀፅ ባንኮች ስሚያቀርቡት ክስ አግባብነት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላው ነጥብ ይኸው የሕግ ግምት የሚመለከተው ወለዱን ብቻ ነው ወይስ ዋናውን ዕዳ ያጠቃልላል የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድንጋጌውን በመጠቀስ ወለዱ ብቻ ሳይሆን ዋናውን ዕዳ ጭምር ሁለት ዓመት ካለፈው እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ባንክ ይህ ትክክለኛ ትርጉም አይደለም በማለት ይከራከራል፡፡

በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ ለመፍታት የድንጋጌውን አቀራረፅ እና መንፈስ በጥንቃቄ መመርመር ይስፈልጋል፡፡ አከራካሪ የሆነው የሕግ አንቀፅ በብድር ስተሠጠ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ...(ሰረዝ የተጨመረ) በማለት የሚደነግግ ነው፡፡ ከዚሁ የሕግ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው የድንጋጌው የመጀመሪያው ክፍል በብድር የተሠጠ የገንዘብ ወለድን በልዩ ሁኔታ ጠቅሶ በሁለት ዓመቱ የሕግ ግምት ውስጥ እንደሚካተት ያስቀምጣል፡፡ ሕግ አውጪው በዚሁ አንቀፅ የሰፈረው የሕግ ግምት ዋናውንም ዕዳ እንደያጠቃልል ቢፈልግ ኖሮ

ወለዱን ለይቶ ያስቀምጣል ተብሎ አይገመትም፡፡ ስለዚህ በድንጋጌው የመጨረሻ ክፍል የሚገኘውና “ሊከፈል የሚገባው ዕዳ” የሚለው ሐረግ ብድርን ስለመመልከት የገባ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ወለዱንና ዋናውን ዕዳ ለይቶ በሕግ ግምት የሚሸፍነው ወለዱ ብቻ እንደሚሆን አድርጊ እያለ በመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት ዋናው ዕዳ ጭምር ሁለት ዓመት ካለፈው በሕግ ግምት እንደተከፈለ ይቆጠራል ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተደነገገው የሕግ ግምት በማስረጃ ቀሪ ሊሆን የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ድንጋጌ ስር በተመለከቱት መንገዶች ነው፡፡ ሆኖም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የተቀመጠውን የሕግ ግምት ለማፍረስ የሚያስፈልጉት ማስረጃዎች በጣም ውስንና በሕግ በግልጽ የተደነገጉ መሆናቸውን ማየትና በጥብቅ ሥርዓት እና በውስን የማስረጃ ዓይነቶች ብቻ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑን መገንዘብ የግድ ይላል፡፡ በዚህም መሰረት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተደነገገው የሕግ ግምት ቀሪ ሊሆን የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር እንደተመለከተው ባለዕዳው በፁሑፍ ዕዳውን ያመነ እንደሆነ በሕግ የተደነገገው የጊዜ ውሳኔ ሳይደርስ ባለገንዘቡ ገንዘቡን እንዲከፍለው ባለዕዳውን ከፍርድ ቤት አስጠርቶ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ድንጋጌ ሲታይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው በሕግ የተሸፈነ የፍሬ ነገር የህሊና ግምት ከመሐላ ቃል በስተቀር በሌላ ማስረጃ ሊፈርስ እንደማይችል ደንግጓል፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው የሕግ ግምት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር በተመለከቱት ሁለት ዓይነት ማስረጃዎች ቀሪ የሚሆን ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር ሁለትና ሦስት ድንጋጌዎች መሰረት ደግሞ በመሐላ ቃል ካልሆነ በቀር በሌላ አይነት ማስረጃ ሊስተባበል የማይችል ማስረጃ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026(1) ድንጋጌ በግልፅ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተውን የሕግ ግምት ለማስተባበል ያለው ዕድል ውስንና ጠባብ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እንግዲህ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 አስገዳጅ የሆነ እና በውስን መንገዶች ብቻ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑ ሁለት ግልፅና የተለዩ ባሕርያት ያሉት ድንጋጌ መሆኑን ከላይ ከገለፅናቸው ህጋዊ ምክንያቶች መገንዘብ የምንችለው ነጥብ ነው፡፡

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ስር የተደነገገውን የሕግ ግምት ባንኮች ለማስተባበል የሚችሉት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌ ስር በተመለከቱት ማስረጃዎች ብቻ ነው ወይስ የሰው ምስክር የሰነድና ሌሎች ማስረጃዎችን በማቅረብ የሕግ ግምቱን ማፍረስና ማስተባበል ይቻላሉ? በሌላ አገላለፅ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር አንድ

ድንጋጌ መሰረት ባንኮች ያበደሩትን ብድርና ወለድ ያልተከፈላቸው መሆኑን ለማስረዳት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ ሲታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለጥያቄው ተገቢውን ምላሽ ለማግኘት ይቻል ዘንድም ባንኮችና ሌሎች ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ገንዘብ ያበደሩ መሆኑን ያበደሩት ገንዘብ ያልተከፈላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሲያቀርቡ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት እንደዚሁም በተመሳሳይ ሁኔታ የባንክና የሌሎች ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ደንበኞች ገንዘብ ያለመበደራቸውን ወይም ብድር መክፈላቸውን ለማስረዳት ሲያቀርቡ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ አንቀፅ ሁለት የተደነገገውን ማየትና ማገናዘብን ያስፈልጋል፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472(1) በብድር የተሰጠ ገንዘብ ከአምስት መቶ የኢትዮጵያ ብር በላይ ሲሆን የብድሩን ውል በፁሑፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሓላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት የማይቻል መሆኑን በአስገዳጅ ኃይለ ቃል የደነገገ ሲሆን የተጠቀሰው ድንጋጌ ንዑሰ ቁጥር ሁለት ደግሞ በንዑስ ቁጥር አንድ ከተመለከተው ልዩ የሰነድ ማስረጃ በስተቀር ለብድር ውል ማናቸውም ሌላ ማስረጃ ለማቅረብ የማይቻል መሆኑን ደንግጓል፡፡

ሆኖም በባንክ፣ በአበዳሪ ተቋማት እና በደንበኞቻቸው መካከል ያለውንና የሚኖረውን የጠበቀ እምነትና ግንኙት፣ ባንኮችና አበዳሪ ተቋማት የዕለት ተዕለት የሥራ ተግባራቸው ብድር በመስጠትና ተከፋይ የብድር ገንዘብ በመሰብሰብ ቀልጣፋ የፋይናንስና የንግድ ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ በኩል ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በማገናዘብ ሕግ አውጪው ባንኮችና ሌሎች አበዳሪ ተቋማት ደንበኞቻቸው ገንዘብ የተበደሩና የተበደሩትን ገንዘብ ያልከፈሉ መሆኑን ለማስረዳት በተመሳሳይ ሁኔታ የባንክ ተበዳሪ ብድር ያልወሰደ ወይም የወሰደውን ብድር የከፈለ መሆኑን ለማስረዳት በሰው ምስክር እና በሕሊና ግምት ለማስረዳት የሚችሉ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ በባለባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ስላለ ግንኙነት ሲቀርብ የሚችለውን ማስረጃ አይነት በተመለከተ አመላካች የሕግ ድንጎጌ በመሆኑ ባንኮችም ሆነ ተበዳሪዎች የሰነድ የሰው ማስረጃ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን በማቅረብ ለማስረዳት የሚችሉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ ቁጥር ሦስት ድንጋጌ በተለዩ ሲታይም በባለባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ስላሉ ግንኙነቶች የብድርን ውል ወይም የተበደረውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ገንዘብ መልሶ መክፈልን በምስክሮች ወይም በአእምሮ ግምት ለማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ መደንገጉ ከላይ የተመለከተውን ምክንያት የሚያጠናክር ነው፡፡

የባንክ ደንበኞች የተበደሩትን የብድር ወለድ የከፈሉ መሆኑን በሕሊና ግምት ለማስረዳት ከሚችልባቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ስር የተመለከተው የሕግ ግምት አንደኛው ሲሆን ይህ ከሆነ አበዳሪው ባንክ ደንበኛው በህሊና ግምት ከፍዬዋለሁ በማለት ያቀረበበትን ክርክር ለማስተባበልና የብድሩ ወለዱ ያልተከፈለው መሆኑን ለማስረዳት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር በተደነገገው መሰረት የሰው ምስክር፣ የህሊና ግምት፣ የሰነድና ሌሎች ማስረጃዎችን በማቅረብ ግምቱን ማስተባበል የሚችል በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌን ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ ሊተረጎምና ተፈፃሚ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሰረቱ የብድር አገልግሎት መስጠት፤ ከተሰጠውም ብድር በማትረፍ የተሻለ አገልግሎት መስጠት የባንክ እና አበዳሪ የፋይናንስ ተቋማት ዋና ተግባር ብቻ ሳይሆን ለእነዚህ ተቋማት ሕልውና መሰረት ሲሆን ተበዳሪዎች ብድሩን ለማንኛውም የኢኮኖሚ መስክ ለማዋል የሚችሉት ደኽው የአበዳሪ ገንዘብ ተቋማት ህልውና ሲጠበቅ ነው፡፡ ይህ ሊሳካ የሚችለው ደግሞ ህግ አውጭው ለእነዚህ ተቋማት ያደረገውን ልዩ ጥበቃ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለሕጉ ሊፈፀም የሚችል ውጤት የሚሠጥ ትርጉም በመስጠት መሆኑን እምነንበታል፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ሕጋዊ ምክንያቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026(1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ በባንኮች፣ በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና በደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የሕግ ድንጋጌ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ባንኮች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር በተመለከተው የሕግ ግምት የሚገዙ ቢሆንም ለደንበኞቻቸው ያበደሩት የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን የሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ ይህን የሕግ ግምት ለማስተባበል የሚችሉበት የፍርድ ሂደት መኖር ይገባዋል፡፡ በዚህ መሰረት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የብድሩ ወለዱ ያልተከፈለው መሆኑን ለማስረዳት እድሉን ሳይሠጡ፣ ያቀረባቸውንም ማስረጃዎችን ሳይመረምሩና ሳይመዝኑ ውሳኔ መስጠታቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መንፈስና ዓላማውን ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ስለአገኘነው ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

በስር ፍርድ ቤት በዋና ተበደሪነት የተከሰሱት የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከስር ጀምሮ ያቀረቡትን ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የሰፈረው የሕግ ግምት እና አመልካች ካቀረባቸው ማስረጃዎች አንፃር ነገር ስንመለከተው በአመልካች የተጠየቀው እዳ ያልተከፈለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ የሕግ ግምት ተጠቃሚ ቢሆኑም አመልካች ይህንን የሕግ ግምት ሊያፈርስ የሚችል በቂ ማስረጃ ያቀረበ በመሆኑ በክርክሩ ሂደት በተረጋገጠው መሰረት 1ኛ ተጠሪ ዕዳውን የማይከፈሉበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ የ2ኛ ተጠሪ ክርክር ሲታይም አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ክስ መስርቶ ሃብት ሳያጣራና በህጉ በተሠጠው ስልጣን መሰረት መብቱን ሳያስከብር ዋሱ ላይ ክስ መመስረት አይችልም በማለት የሚከራከሩ የነበረ መሆኑንና በዚህ ችሎትም ካስመቀረባቸውም በላይ የ1ኛ ተጠሪ ክርክር የሚጠቀማቸው አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ 2ኛ ተጠሪ የገቡት የዋስትና ዓይነት የአንድነትና የነጠላ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ተጠሪን ከዋናው ተበዳሪ ጋር በአንድ ላይ መክሰሱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1933(1) ድንጋጌ አንፃር ህጋዊ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረትም የተሠጠውን ሥልጣን ባንክ የሚጠቀመው መያዣ በአስያዙ ተበዳሪዎች ላይ ሆኖ በእነዚህ ተበዳሪዎችም ቢሆን ባንክ በአዋጁ የተሠጠውን ሥልጣን በመተው ፍርድ ቤት ክስ ከመመስረት የሚከለክልበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ሕጎቹ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪም በገቡት ግዴታ አይነትና በክርክሩ ሂደት በተረጋገጠው መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ለአመልካች የማይከፍሉበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 09312 ሚያዝያ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02227 ሕዳር 27 ቀን 1999 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ መሰረት በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸውን ብር 25097.54(ሃያ አምስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሳንቲም) ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 17%(አስራ ሰባት በመቶ) እየታሰበ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካች ለዳኝነት ያወጣውን ወጪ ደረሰኝ በመሰከረው መሰረት ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡

4. በክርክሩ የወጡትን ሌሎች ወጪዎችና ኪሳራዎችን የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

# ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ መዝገብ ውሳኔ ግልባጭ በመ/ቁጥር 26363፣ 32196፣ 32199፣ 32202፣ 32203፣ 32205፣ 33222፣ 33282፣ 34329 እና 35605 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 34329

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. ተገኔ ጌታነህ

2. መንበረፀሐይ ታደሰ

3. ሐጎስ ወልዱ

4. ሂሩት መለሰ

5. ታፈሰ ይርጋ

6. አልማው ወሌ

7. ዓሊ መሐመድ

**አመልካች:-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ አንዳርጋቸው ዳኛው ቀረቡ

**ተጠሪ:-** 1. አቶ ፈቃደ ደምስስ
2. ሸዋረጋ ገብሬ } የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በብድር የተሠጠን ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ጋር በተያያዘ ዕዳው እንደ ተከፈለ ሲቆጠር የሚችልበትን የሕግ አግባብና ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ ለንግድ ስራቸው ማስፋፊያ የሚውል የካቲት 26 ቀን 1987 በተፃፈ የብድር ውል ከባንኩ ዳለቻ ቅርንጫፍ ብር 30,000.00(ሠላሣ ሺህ ብር) የተበደሩ መሆኑን፣ ዋናውን ብድርና ልዩ ልዩ ወጪዎችን ጨምረው በዓመት 14% አስራ አራት በመቶ ወለድ እየታሰበ እስከ የካቲት 25 ቀን 1988 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍለው ለማጠናቀቅ መስማማታቸውን፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ለተበደረው ለዚሁ የገንዘብ መጠን የአንድነትና የነጠላ ዋስ በመሆን መፈረማቸውን በመግለፅ ዋናውን ብድር ብር 30,000.00 እስከ ጥር 22 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የታሰበ ወለድ ብር 21,220.36(ሃያ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ብር ከሠላሣ ስድስት ሣንቲም) እና ለኢንሹራንስ የተከፈለ ብር 3,350.65(ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሃምሳ ብር ከስድሣ አምስት ሣንቲም) ስለመሆኑ በመዘርዘር በድምሩ ብር 54,751.53(ሃምሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ብር ከሃምሳ ሶስት ሳንቲም)

ከሆነው ገንዘብ ውስጥ ወደ ብድሩ የተከፈለው ገንዘብ ብር 23,759.53 ተቀናሽ ሲሆን እስከ 22/05/1996 የሚፈለግ ዕዳ በአጠቃላይ ብር 30,991.48(ሠላሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ብር ከአርባ ስምንት ሣንቲም) የመቀጫ ወለድ 3% ጨምሮ በድምሩ 17% ወለድ እየታሰበ ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎችም ቀርበው የቀረበባቸውን ክስ በመቃወም የበኩላቸውን ክርክር አንስተው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ የሠጠው ብድር ክፍያ መጠናቀቅ የነበረበት በውላቸው መሠረት የካቲት 25 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፣ አመልካች በዚህ ጊዜ ውስጥ አልጠየቀም፣ ክሱን ያቀረበውም ከስምንት ዓመት በኋላ፣ በፍ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሠረት አበዳሪው የተወሠነ ጊዜ ተበጅቶለት በዓመት ወይም ከዓመት በፊት የሚከፈለውን የገንዘብ ዕዳ ሣይጠይቅ እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ከቆየና ከሁለት ዓመት ጊዜ በኋላ ከጠየቀ ገንዘቡ በተበዳሪው እንደተከፈለ ወይም ዕዳው ምህረት እንደተደረገለት ሕግ ግምት የወሰዳል የሚል ምክንያት በመያዝ አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ያቀረበው ክስ አያስከስስም፣ የ1ኛ ተጠሪ ግዴታ ቀሪ ስለሆነ የሁለተኛ ተጠሪ ግዴታም ቀሪ ሁኗል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ተሠርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ታህሳስ 04 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 3(ሦስት) ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቀርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ መሠረት ያደረገው ድንጋጌ አግባብነት የሌለው መሆኑን በፍ/ህ/ቁጥር 2025 ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ተሽሮ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ መሠረት በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸውን ብር 30,991.48(ሠላሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ብር ከአርባ ስምንት ሳንቲም) ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 17%(አስራ ሰባት በመቶ) ወለድ እየታሰበ ከክርክሩ ወጪና ኪሳራ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ የሠበር ሠሚ ችሎትም አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በፍ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሰረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል ውድቅ

እንዲሆን የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡

ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው እያንዳንዳቸው የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 3(ሦስት) ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የፍ/ህ/ቁጥር 2024(ረ) ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆኑን የፍ/ህ/ቁጥር 2025 መሠረት ያደረገው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ መሆኑን ዕዳው ከሚከፈልበት ጊዜ ለተራዘመ የብድር ግዴታም የማይጠቁ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 1928(2) ድንጋጌ እንደሚያሳይ ገልፀው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ባቀረቡት የሠበር አቤቱታ መሠረት ውሣኔ እንዲሠጥ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሲታይ ይገባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ይህ ችሎት በመ/ቁጥር 29181 አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች በመተርጎም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026(1) ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገውን የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2473/2/ ድንጋጌ ዋጋ በሚያሳጣ መንገድ ሊተረጎምና ተፈፃሚ መሆን እንደማይገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026(1) ድንጋጌ በባንኮችና በሌሎች አበዳሪ ተቋማትና ደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈጻሚነት የሌለው የህግ ድንጋጌ መሆኑን በመተንተን ባንኮች ለደንበኞቻቸው ያበደሩትን ብድርና ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን በሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተደነገገውን የሕሊና ግምት ለማስተባበል የሚችሉ መሆኑን በመግለፅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ የሕግ ትርጉም መሰረት በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ለውሳኔው መሰረት ያደረጉት ምክንያት አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለውን ሕግ ባለመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

በስር ፍርድ ቤት በዋና ተበዳሪነት የተከሰሱት የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ችሎትም ሆነ በስር ፍርድ ቤት በሠጡት መልስ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ለጉዳዩ አግባብነት አለው፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ነው በማለት መከራከራቸው ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ለክርክሩ መሰረት የሆነው ገንዘብ ያልተከፈለው ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ባቀረባቸው ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም አመልካች 1ኛ ተጠሪ የተበደሩትንና ለክሱ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ያልከፈሉ ስለመሆኑ እስከአሁኑ የክርክሩ ሂደት በተረጋገጠው መሰረት የማይከፍሉበትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ሕጋዊ ምክንያት አሳገኘንም፡፡ 2ኛ ተጠሪም በስር ፍርድ ቤት በሰጡት መከላከያ መልስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ክርክር ከመሆኑ በተጨማሪ ዋስትናው ያላግባብ ስለተራዘመ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1928 መሰረት ልጠየቅ አይገባም የሚል ነው፡፡ በዚህ ችሎትም ይህንኑ አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ውሳኔ ከመስጠቱ ውጪ 2ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1928(2) አንፃር ያቀረቡትን ክርክር ተገቢውን የሕግ ምክንያት ያልሰጠበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን ይህ ችሎት የዚህን ድንጋጌ ይዘት ሲመለከተው ባለገንዘቡ ዋሱን ሳያስፈቅድ ለባለዕዳው ከቀድሞው ውል ከተጠቀሰው ጊዜ ውጪ በሆነ ሁኔታ የመክፈያ ጊዜ አራዝሞ የሠጠ እንደሆነ ዋሱ ነፃ የሚሆንበት ሁኔታ የሚያሳይ እንጂ በመጀመሪያው ውል መሰረት እዳውን በመክፈያ ጊዜ ያልጠየቀን ባለገንዘብ የሚመለከት ባለመሆኑ 2ኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክርም ከኃላፊነት ነጻ የሚያደርጋቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ በገቡት ግዴታ መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ለአመልካች የማይከፍሉበትን ሕጋዊ ምክንያት አሳገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 8206 ሰኔ 01 ቀን 1999 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03232 ህዳር 09 ቀን 2000 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ መሰረት በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸውን ብር 30,991.48(ሠላሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ብር ከአርባ ስምንት ሳንቲም) ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 17%(አስራ ሰባት በመቶ) ወለድ እየታሰበ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ለዳኝነት ያወጣውን ወጪ ደረሰኝ በመሰከረው መሰረት ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
4. በክርክሩ የወጡትን ሌሎች ወጪዎችንና ኪሳራዎችን የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 36749

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተገኔ ጌታነህ

2. መንበረፀሐይ ታደሰ

3. ሐጎስ ወልዱ

4. ሂሩት መለሰ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ አበባው ይግዛው ጠበቃ አምሣሉ ባዬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ደስታ ሲበን ቀረቡ

2. የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር - ነ/ፈጅ ወልደማሪያም ስዩም ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የባለሃብትነት መብትን መሰረት በማድረግ የቀረበው የቤት ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበረው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተው በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 18 ቀበሌ 26 ክልል የሚገኘውን፣ በይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር 21017፣ ቁጥር 303 በሚል የሚታወቀውን ቤት እንዲያስረክበው ይወሰንለት ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ ለማስረጃነትም የካቲት 03 ቀን 1985 ዓ.ም በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተሠጠኝ ያሉትን ቁጥር ነ-11/35/85 የሆነ የተጻፈ ደብዳቤ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሳሽነት ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ፤ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሁኗል በማለት በብይን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

እኛም የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር ማመልከቻ ያቀረቡትን ቅሬታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር

ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ አለኝ የሚሉትን የባለሃብትነት መብት መሰረት ያደረገው ክስ በይርጋ ቀሪ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሷቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ለክሱ መነሻ የሆነው ንብረት (ቤት) የማይንቀሳቀስ ሃብት በመሆኑ ክርክሩ መታየት ያለበት በንብረት ሕግ መሰረት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677 እና 1845 ስር የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ጉዳዩን ሲከታተሉት የነበሩት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1851 መሰረት የይርጋ ማቋረጫ ምክንያቶች ሲሆኑ ይገባ ነበር የሚሉ ናቸው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ይርጋን በሚመለከት በተያዘው ጭብጥ ላይ ተመስርተው ክርክሩን አቅርበዋል፡፡ በዚህም መሰረት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 ድንጋጌ ስር የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት አለው፡፡ ድንጋጌው ውልን መሰረት አድርጎ ለሚነሳ ክርክር ብቻ ነው አግባብነት ያለው የሚለው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ግዴታዎች ከውል ባይመነጩም የውል ደንቦች ተፈፃሚ እንደሚሆንባቸው በሕጉ ተደንግጓል የሚሉትን የመከራከሪያ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡ የ1ኛ ተጠሪ ነ/ፈጅ አመልካች አለኝ የሚሉት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የካቲት 07 ቀን 2000 ዓ.ም መሰረዙን በመግለፅ አመልካች በቤቱ ላይ ክስ አቤቱታ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም የሚል ተጨማሪ ክርክርም አቅርቢል፡፡

ግራ ቀኙ ወገኖች ከስር ጀምረው ያደረጉት ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ የሚያስነሳው ጭብጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የሚቀርበው የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ አለ ወይ? የሚለው ነው፡፡ ጭብጡ የሕግ ጭብጥ በመሆኑ መልስ ሊያገኝ የሚችለው በዚህ ረገድ አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌዎችን በመፈተሽ ነው፡፡

አመልካች ክሱን የመሰረቱት የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን ገልፀውና በዚህ ረገድም የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዳላቸው በማመልከት ነው፡፡ ጥያቄው የቤቱ ባለሃብት በመሆኔ ከሕግ ውጪ ይዞብኝ የሚገኘውን ተጠሪ በፍርድ ኃይል እንዲለቅ ይደረግልኝ በሚል በግልፅ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1206 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን የመፋለም ክስ (Petitory Action) የሚመለከት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ክሱ በዚህ መልክ ቢቀርብም ተጠሪ የክሱ መቅረብ አግባብ አለመሆኑን የሚመለከቱና ይጠቅሙኛል የሚላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሳት መከላከያውን ያቀርባል ተብሎ ይገመታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ለመከላከያ ይጠቅሙኛል ያላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ይርጋን መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ያደረገ መቃወሚያ ነው፡፡ ስዚህ ክርክሩ በዋቢነት የጠቀሰው በፍትሐብሔር ሕጉ በአራተኛ መፅሐፍ “ስለግዴታዎች” በተደነገገው በአንቀጽ 12 ስር ካሉት ድንጋጌዎች ስር የሚገኘውን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 ስር የተመለከተውን የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው፡፡ እንግዲህ ይህ ድንጋጌ የሚገኘው በፍትሐብሔር ህጉ ሦስተኛ መጽሐፍ “ስለንብርት” ከሚለው አንቀጽ ስድስት እና “ስለግል ሃብት” ከሚለው ከአንቀጽ ሰባት ውጪ በመሆኑ ከተያዘው የይርጋ መቃወሚያ አግባብነት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከማየታችን በፊት አግባብነት ያላቸው የንብረት ሕጉ ድንጋጌዎችን ሁኔታ መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 43600 ላይ ተመሳሳይ ጉዳይ ቀርቦለት አግባብነት ያላቸውን የንብረት ሕግ ድንጋጌዎችን በመመርመር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1206 ስር የተመለከተው የመፋለም ክስ (Petitory Action) በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677 እና 1845 መሰረት በአስር አመት የይርጋ ጊዜ የማይታገድ መሆኑን፣ ይልቁንም በሌሎች ሕጋዊ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር በይርጋ ሊታገድ የማይችል ጉዳይ ስለመሆኑ ሰፊ የሕግ ትንታኔ በማስቀመጥ አስገዳጅነት ያለው የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡

በአጠቃላይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት ቀሪ የሚሆነው በይርጋ ሳይሆን በሌሎች ሁኔታዎች ይሆን ዘንድ የሕጉ ፍላጎት እንደሆነ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ሊያደርጉት የሚገባው ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ክሱን ማቋረጥ ሳይሆን ክሱ እንዲቀጥል በማድረግ ከሳሹ በእርግጥም የባለቤትነት መብበት ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማጣራት፣ ባለቤት ከነበረም ሕጋዊ በሆነ ስርዓት የባለቤትነት መብቱ መቋረጥ አለመቋረጡን በማስረጃ በማጣራት እና ተገቢ የሆነውን ውሳኔ መወሰን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የባለቤትነት መብት ባሕርይ ቀጣይነት (perpetuity) በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በዚህ የሕግ ትርጉም መሰረት አንድ ክስ በይርጋ አይታገድም ከማለታቸው በፊት የክሱ መሰረታዊ ይዘት የባለቤትነት መፋለም (petitory Action) መሆኑን ማረጋገጥ የጠበቅባቸዋል፡፡ ከባለቤትነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገር ግን ከመፋለም መብት ውጪ ያሉት ሌሎች ክሶች እንደሚጠይቁት መፍትሔ (Remedy) እና ለክሱ ምክንያት እንደሆነው ጉዳይ ዓይነት (ጋብቻ፣ ውርስ፣ ሽያጭ፣ ወዘተ...) በሌሎች ልዩ ሕጎች የይርጋ ደንቦች የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የይርጋ ጉዳይ ክስ ይቀጥል አይቀጥል የሚለውን ነጥብ የሚመለከት ብቻ በመሆኑ ሙግቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በፍሬ ነገሩ የሚሠጠው ውሳኔ በሕጉ ይዘትና ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቡት ማስረጃ ጥንካሬ የሚወሰን መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች የዚህን ውሳኔ የሕግ ትርጉም በዚህ መንፈስ ሊረዱት ይገባል፡፡ 2ኛ ተጠሪ የአመልካች ካርታ ተሰርዞአል በማለት ያቀረበው ክርክርም በዚህ

ችሎት የክርክር ደረጃ የሚታይበት ስርዓት ባለመኖሩ ታልፏል፡፡ ስለሆነም ከላይ ከተሠጠው ትንታኔ አንጻር አቤቱታ የቀረበበት ብይን የንብረት ሕጉን መሰረተ ሃሳብ ያልተከተለ፣ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39447 ህዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሠጠው ፍርድ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35276 መጋቢት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም መብት ክስ (Petitory Action) በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ክሱ ስረ-ነገር በመግባት ግራ ቀኙን ወገኖች ከአከራከረ በኋላ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram
https://chilot.me

የሰበር መ.ቁ 39462

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ንጉሴ ታምራት - አልቀረቡም

2. አቶ ደንበል ጋቸና - አልቀረቡም

3. አቶ ዮሴፍ እንዳስ - አልቀረቡም

4. አቶ ፈቃዱ በዳዳ - አልቀረቡም

5. አቶ ሰለሞን በቀለ - አልቀረቡም

6. አቶ ዮሴፍ ሮኮ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** በከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር - ነገረ ፈጅ ይልማ ገመቹ ቀረበ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በመዝገብ ቁጥር 39352 ባቀረቡት የሰበር አቤቱታና 5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች በመዝገብ ቁጥር 39351 ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ከተጠሪ ጋሬ ከሚያደርጉት ክርክር ጋር ተመሣሣይ የህግ ጭብጥ ያለው ሆኖ ስላገኘነው የመዝገብ ቁጥር 39462፣ የመዝገብ ቁጥር 39352 እና የመዝገብ ቁጥር 39351 በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 11 ንዑስ አንቀፅ 5 መሠረት በማጣመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በተለያዩ ሶስት መዝገቦች የአዳማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካቾችን ክርክር ሰምቶ የሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ከላይ በተጣመሩት የሰበር መዝገቦች አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከተጣመሩት የመዝገብ ግልባጮች እንደተገነዘብነው ተጠሪ በአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ

ቤት በመዝገብ ቁጥር 04069፣ በመዝገብ ቁጥር 04075 እና በመዝገብ ቁጥር 04072 በአመልካቾች ላይ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ

1. አንደኛ አመልካች የድርጅቱ ከባድ መኪና ሾፌር ሆኖ ሲሠራ ከጅቡቲ ጭኖ ግልገል ጊቤ ሣሊኒ ፕሮጀክት ማድረስ ከነበረበት ከፊት ዋጋው 18750 (አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) የሆነ 3000 ኪሎ ግራም ብረት ያጎደለ በመሆኑና ሁለተኛው አመልካች አንደኛው አመልካች በድርጅቱ ሾፌር ሆኖ ሲቀጠር እስከ ብር 100000 (መቶ ሺህ ብር) ለሚያደርሰው ኪሳራ የዋስትና ግዴታ የገባ ስለሆነ ገንዘቡን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ
2. ሶስተኛ አመልካች የድርጅቱ ከባድ መኪና ሾፌር ሆኖ ሲሠራ ከጅቡቲ ጭኖ ግልገል ጊዜ ሳሊኒ ፕሮጀክት ማድረስ ከነበረበት ብረት ዋጋው ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) የሆነ 500 ኪሎ ግራም ብረት ያጎደለ በመሆኑና ሶስተኛው አመልካች የድርጅቱ ሾፌር ሆኖ ሲቀጠር አራተኛው አመልካች በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ኪሣራ እስከ ብር 100000(መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የዋስትና ግዴታ የገባ በመሆኑ ያጎደለውን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ
3. አምስተኛው አመልካች የድርጅቱ ከባድ መኪና ሾፌር ሆኖ ሲሠራ ከጅቡቲ ጭኖ ግልገል ጊቤ ሣሊኒ ፕሮጀክት ማድረስ ከነበረበት ብረት ዋጋው ብር 14375 (አስራ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ አምስት ብር) የሆነ 2300 ኪሎ ግራም ብረት ያጎደለ በመሆኑና ስድስተኛው አመልካች አምስተኛ አመልካች የድርጅቱ ሹፌር ሆኖ ሲቀጠር በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ኪሣራ እስከ ብር 100000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የዋስትና ግዴታ የገባ በመሆኑ ያጎደለውን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

የተጠሪ ሠራተኞች የነበሩት አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች በተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ በየተከሰሱበት መዝገብ ባቀረቡት መልስ ብረቱን ከጅቡቲ መዝነን አልተቀበልንም፡፡ ለሳሊኒ ፕሮጀክትም መዝነን አላስረከብንም፡፡ ሳሊኒ ፕሮጀክት ጭነን ያመጣነውን ብረት ሲረከቡ ጉድለት የተገኘ መሆኑን በማስረከቢያ ቅፅ ላይ ሞልቶ ወዲያውኑ አልገለፀልንም፡፡ ከጅቡቲ የጫነውን ጥቅል ብረት ሣንካካ ከመድረሻው ግልገል ጊቤ አጓጉዘን በአግባቡ ያስረከብን በመሆኑ ብረቱ ሲመዘን ለደርሰው ጉድለት ተጠያቂ የምንሆንበት ምክንያት የለም የሚል ይዘት ያለው መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

የአንደኛ አመልካች የሶስተኛ አመልካችና የአምስተኛ አመልካች ዋስ ናቸው በማለት ተጠሪ ክስ ያቀረበባቸው ሁለተኛ አመልካች አራተኛ አመልካችና ስድስተኛ አመልካች በበኩላቸው በተከሰሱባቸው መዝገቦች ባቀረቡት መልስ ተጠሪ ሹፌሮችን በጊዜያዊነት ሲቀጥር ዋስ መሆናቸውንና ተጠሪ ሹፌሮችን ቋሚ ሠራተኛ ያደረገው ያለእነርሡ ፈቃድና ስምምነት መሆኑን ገለፀው ሹፌሮቹ ቋሚ ሠራተኛ ሆነው ላደረሡት ጉድለት የመክፈል ኃላፊነት የለብንም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካቾችን ክርክር ከመዘነ በኋላ የተጠሪ ከባድ መኪና ሹፌሮች የሆኑት አንደኛ፣ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች በጉድለት የተገኘባቸውን ብረት ዋጋ የመክፈል ኃላፊነት እንዳለባቸውና ሁለተኛ፣ አራተኛ ስድስተኛ አመልካቾች አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ሹፌር ሆነው ሲቀጠሩ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት እስከ ብር 100000 (መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል እያንዳንዳቸው የዋስትና ግዴታ የገቡ በመሆኑ ጉድለቱን በአንድነትና በነጣላ የመክፈል ኃላፊነት እንዳለባቸው ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔም

- አንደኛና ሁለተኛ አመልካች ብር 18750 (አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) በአንድነትና በነጠላ ለተጠሪ እንዲከፍሉ
- ሶስተኛና አራተኛ አመልካቾች ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) በአንድነትና በነጠላ ለተጠሪ እንዲከፍሉ
- አምስተኛና ስድስተኛ አመልካቾች ብር 14375(አስራ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ አምስት ብር) በአንድነትና በነጠላ ለተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ ለማቅረብ ያወጣውን የዳኝነት ክፍያና ሌሎች ወጭና ኪሣራዎች አመልካቾች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

አመልካቾች በተለያዩ መዛግብት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በየበኩላቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞባቸዋል፡፡ አመልካቾች በየበኩላቸው የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

አመልካቾች በዚህ መዝገብና ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምረው በታዩት የሰበር መዛግብት የየበኩላቸውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች መዝነው ያልተረከቡትን እና መዝነው ያላስረከቡትን ብረት አጉድላችኋል ተብለው በኃላፊነት እንዲጠየቁ

የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው የጠየቁ ሲሆን ሁለተኛ አራተኛና ስድስተኛ አመልካቾች በበኩላቸው የዋስትና ውል የፈፀሙት አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች በጊዜያዊነት ተቀጥረው ስሚያጠፉት ጥፋት ሆኖ እያለ ከዋስትና ውሉ ውጭ ቋሚ ሹፌር ሆነው ያጎደሉትን ጉድለት ክፈሉ ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን የሚል ይዘት ያለው የሰበር አቤቱታ ቀርበዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ከዚህ መዝገብ በቃል ክርክር በሌሎቹ የሰበር መዝገቦች በፅሑፍ ባቀረበው መልስ አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች ጅቡቲ ተረክበው ከጫኑት ብረት ውስጥ መጠኑና ዋጋው በክሳችን የተገለፀውን ብረት ያጎደሉ መሆናቸውን በበቂ ሁኔታ አስረድተናል፡፡ ሁለተኛ አራተኛና ስድስተኛ አመልካቾች እያንዳንዳቸው የዋስትና ውል የፈረሙት አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች ሹፌር ሆነው ሲሠሩ ተጠሪ ላይ ስሚያደርሱት ጉዳት እስከ ብር 100000 (መቶ ሺህ ብር) ስመክፈል መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት አስረድተናል፡፡ ስለዚህ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካቾች በየበኩላቸው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታና ተጠሪ የሰጠው መልስ ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው

1ኛ/ አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች ከጅቡቲ ወደብ ጭነት ሲጭኑ

የጫኑትን ዕቃ አይነትና መጠን የሚገልፅ የመረካከቢያ ቨርቫል ፈርመው የተረከቡ መሆኑንና ጭነቱ ግልገል ገቤ የሚገኘው የሳሊኒ ፕሮጀክት ካራገፉ በኋላ ብረቱ ሲመዘን አንደኛው አመልካች በቨርቫል ፈርሞ ከተረከበው ሶስት ሺ ኪሎ ግራም ብረት የጎደለ መሆኑ፣ ሶስተኛው አመልካች ፈርሞ ከተረከበው ብረት ስምንት መቶ ኪሎ ግራም ብረት የጎደለ መሆኑን አምስተኛው አመልካች ፈርሞ ከተረከበው ብረት ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ኪሎ ግራም የጎደለ መሆኑን በማረጋገጥ የጎደለውን ብረት ዋጋ ሣሊኒ ኮንስትራክሽን ከተጠሪ ተከፋይ ሒሳብ ቀንሶ ያስቀረ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው ክርክርና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ ሦስተኛና አምስተኛ አመልካቾች በሰነድ ፈርመው የተረከቡትን እቃ አጓጉዘው ለባለንብረቱ የማስረከብ ግዴታና ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተደግፎ የቀረበለትን የተጠሪን ክስ በመቀበል የተጠሪ ሠራተኞች የሆኑት አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች ያጎደሉትን ብረት ዋጋ እያንዳንዳቸው የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎት ማፅናታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ተገቢና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ውሳኔ ሆኖ ስላገኘነው አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች በየበኩላቸው ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

2ኛ/ ሁለተኛ አራተኛና ስድስተኛ አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር መከራከሪያ

ስንመለከት ሁለተኛው አመልካች አንደኛ አመልካች ለተጠሪ ድርጅት ሹፌር ሆኖ ከተቆጠረበት ጊዜ ጀምሮ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት እስከ ብር 100000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የዋስትና ውል የፈረመ መሆኑ አራተኛው አመልካች ሶስተኛው አመልካች በተጠሪ ድርጅት ሹፌር ሆኖ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት እስከ ብር 100000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የዋስትና ውል የፈረመ መሆኑና ስድስተኛው አመልካች አምስተኛው አመልካች በተጠሪ ድርጅት ሹፌር ሆኖ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት እስከ ብር 100000(አንድ መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የዋስትና ውል የፈረመ መሆኑን ከቀረበለት ማስረጃ ማረጋገጥ እንደቻለ የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልጿል፡፡ ሁለተኛ አራተኛና ስድስተኛ አመልካቾች ያደረጉት የዋስትና ውል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1925(1) የተደነገጉትን መስፈርቶች የሚያሟላና ዋሶቹን የማስገደድና ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የዋስትና ውል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤት ሁለተኛ አራተኛና ስድስተኛ አመልካቾች ዋስ ከሆኑላቸው የተጠሪ ሠራተኞች ከሆኑት አንደኛ ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች ጋር ያጎደለውን ብረት ዋጋ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ችሎት ማፅናታቸው ህጋዊና በአግባቡ የተሰጠ ውሳኔ ሆኖ አግኝተነዋል

በአጠቃላይ ስንመዝነው የኦሮሚያ ክልል የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት

- አንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ብር 18,750(አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር)
- ሶስተኛና አራተኛ አመልካቾች ብር 5000(አምስት ሺህ ብር)
- አምስተኛና ስድስተኛ አመለካቾች ብር 14,375(አስራ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ አምስት) ብር በአንድነትና በነጠላ ከልዩ ልዩ ወጭዎች ጋር እንዲከፍሉ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለው በመሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት አፅንተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 04069፣ በመዝገብ ቁጥር 04075 እና በመዝገብ ቁጥር 04072 የሰጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡

2. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የመዝገብ ቁጥር 53083 በመዝገብ ቁጥር 53175 እና በመዝገብ ቁጥር 53084 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 61410 በመዝገብ ቁጥር 61422 እና በመዝገብ ቁጥር 61414 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ አመልካቾችና ተጠሪ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 40229

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ - ጠበቃ አታክልት ሃ/ስላሴ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ መዲና በያን - ቀረቡ

2. አቶ ደኑር አብደላ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ሲሆን የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከተወሰነ በኋላ የንብረት ክፍፍሉንም ፍ/ቤቱ ተመልክቶ በ8-2-2000 ዓ.ም ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ የእኔን ሚስትነት ሰርዘው እኔ በማላውቀው ሁኔታ የባልና ሚስት ፍቺ አስወስነው የንብረት ክፍፍልም እንዲደረግ የተወሰነ ስለሆነ ይህ ውሳኔ የእኔን መብት የሚጐዳ ስለሆነ ይሰረዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የመቃወም አመልካች በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር በቀጠሮ ላይ እንዳለ ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የጣልቃገብነት አቤቱታ አቅርባ አመልካችና ተጠሪ (የአሁን ተጠሪዎች) መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነገር ግን የመቃወም አመልካች ትዕዛዙን ባለማድረሳቸው ድጋሚ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በድጋሚውም ትዕዛዝ መሠረት ባለመፈጸማቸው አቤቱታቸውን ባለመቀበለ ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው ደግሞ ክርክር እየተደረገ መሆኑን ያልተገነዘበ ወገን በሌለበት ክርክር ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ መብቱን የነካበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ነገር ግን ክርክር መኖሩን የተገነዘበ ሰው ከበስተጀርባ ሆኖ የክርክሩን ሚዛን በመገምገም እርሱን በሚመለከት አጥጋቢ ፍርድ ባልተሰጠ ጊዜ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ማቅረብ ከሥነ-ሥርዓት ሕጉ ዓላማ አኳያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በዚህም ጉዳይ የመቃወም አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ለመሆን አቤቱታ አቅርባ መጥሪያ እንድታደርስ ለሁለት ጊዜ ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም በትዕዛዙ መሠረት ሳትፈጽም ቀርታ ከውሳኔ በኋላ ወደ ክርክሩ ለመግባት አቤቱታ ማቅረቧ ክርክር መኖሩን እያወቀች ስለሆነ አቤቱታው በተገቢው አኳኋን አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ መ/ሰጭዎችን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተገቢነቱን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማንኛውም ሰው ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ለማቅረብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 ላይ ተመልክቷል፡፡

መቃወሚያ ማቅረብ የሚፈቀድበት ደንብ መሠረታዊ ዓላማም ምንአልባት ፍርድ መስጠቱን ያላወቀና በተሰጠው ፍርድም ጥቅሙ የሚነካ ሰው ፍርዱ ቢፈጸም በጥቅሙ ላይ ሊከተል የሚችለውን ጉዳት መከላከል ነው፡፡ አንድ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ለማቅረብ የሚችለውም በጉዳዩ የሚያገባውና በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 41 መሠረት የክርክሩ ተሳታፊ ሲሆን የሚችል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ነው፡፡ አመልካችም በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር ስለሚመለከተኝ የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ይገባኛል ብለው በፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 41 መሠረት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ነበር፡፡ አቤቱታቸውም ተቀባይነት አግኝቶ ፍ/ቤቱ ክርክሩን አግዶ የጣልቃገብነት ማመልከቻው ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስና መልስ እንዲሰጡበት ከአንድም ሁለት ጊዜ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የጣልቃገብነት አቤቱታ ለተከራካሪ ወገኖች ሳይደርስ

የቀረው በአመልካቹ ጉድለት በሆነ ጊዜ ደግሞ ጣልቃገቡ ነገሩን ሆነ ብሎ እንደተወው ተቆጥሮ መብቱ እንደሚሰረዝበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 41(4) ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች በተጠሪዎች መካከል ክርክር እየተደረገ መሆኑን ተገንዝበው በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የጣልቃገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባቸው ይህን ሳይፈጽሙ ቀርተው መብታቸው ከተሰረዘ በኋላ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ማቅረባቸው ክርክር መኖሩን በሚገባ በተገነዘቡበት ሁኔታ ስለሆነ በዚህ መልኩ የሚቀርብ አቤቱታ ከሕጉ ዓላማ ጋር ስለማይጣጣም የሥር ፍ/ቤቶች አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ እንጂ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 56832 በ20/8/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 67878 በ21/11/2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. ግራ ቀኝ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 42569

ታህሳስ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

አመልካች፡- 1. ዳግማዊ ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ወ/ሮ ፍሬህይወት ታመነ
2. ናትናኤል ታዲዮስ
} ጠበቃ ፋንታሁን አባተ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ወ/ሮ ቤተልሄም ግርማ - ጠበቃ አልታዬ ወ/አማኑኤል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ልጅነት ይታወቅልኝ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ሞግዚትና አስተዳዳሪ መጋቢት 13 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ሕፃን ሐናን ከአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ የወለድኳት ስለሆነ ሕፃን ሐና የአቶ ታዲዮስ ልጅ መሆኗ በፍርድ ውሳኔ ይታወቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው ፍርድ ቤቱም የአሁኑ አመልካቾች በሌሉበት የተጠሪን ምስክሮችን በመስማት የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 143(መ)ን መሰረት በማድረግ ሕጻን ሐና የአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት በማለት ግንቦት 22 ቀን 1997 ዓ.ም ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ውሳኔው መብታችንን የሚነካ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ለመቃወሚያው መሰረት ያደረጓቸው ነጥቦችም ለውሳኔ መሰረት የሆነው የልደት ምስክር ወረቀት የወጣው አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ህዳር 06 ቀን 1997 ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ጥር 18 ቀን 1997 ዓ.ም ነው፣ የጥምቀት ምስክር ወረቀቱም አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ያልፈረሙበት ነው፣ የተሰሙት ምስክሮችም ለውሳኔው መሰረት የሆነው ድንጋጌ የሚጠይቀውን መመዘኛ በሚገባ አሳስረዱም የሚሉ ናቸው፡፡ የአሁኗ ተጠሪም በአመልካቾች መቃወሚያ ላይ መልስ ሲሠጡ በጉዳዩ ላይ

የቀረቡት የጽሑፍ ማስረጃዎች የወጡበት ሁኔታ በአሰራር ደረጃ የተለመደ በመሆኑ ማስረጃዎች በሕግ ፊት ተቀባይነት ያላቸው መሆኑንና ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅም ሕፃን ሐናን እንደአባት ሁነው ሲንከባከቧት የነበረ መሆኑ በምስክሮች ባግባቡ መመስከሩን ገልፀው መቃወሚያው ውድቅ ሲሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ሕፃን ሐና የሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ስለመሆኗ ልጅነት በፍርድ ከሚታወቅባቸው መንገዶች መካከል በአንዱ አልተረጋገጠም በማለት ቀደም ሲል የሠጠውን ውሳኔ ሠርዞታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ እና የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሚ ከተሰሙ በኋላ ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሕፃን ሐና ወላጅ እናት ጋር ቀጣይነት ባለው ግንኙነት ውስጥ እንደነበሩ፣ ሕፃኗን እንደ አባት በመሆን ያሳድጓት እንደነበር መረጋገጡን እና የልደት ምስክር ወረቀትም ማስረጃውን በሠጠው አካል እስካልተሠረዘ ድረስ ተቀባይነት እንዳለው በመግለፅ ሟቹ የአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ የህፃኗ አባት መሆናቸው በልደት ምስክር ወረቀትና በምስክሮች ቃል ተረጋግጧል በማለት በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51348 ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተሠጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ጥር 06 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የልደት ምስክር ወረቀቱ አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሞቱ በኋላ የወጣ መሆኑ እየታወቀ እና የተጠሪ ምስክሮች ቃልም የሕፃኗ እናት እና አባት የተባለው ሰው በሕግ በተመለከተው የአርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት አብረው የነበሩ ስለመሆኑ ሕጉ በሚጠይቀው መመዘኛ የመሰከሩ ስለመሆኑ የማያረጋግጥ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተቀመጠውን ጥብቅ መመዘኛ በማለፍ ሟች የሕፃን ሐና አባት ናቸው ብሎ የወሰነው ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ሕፃን ሐና የሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት በሚል የተሠጠው የልጅነት ምስክር ወረቀት ሟች ከሞቱ በኋላ የተሠጠ ነው እየተባለ የስር ፍርድ ቤት ይህንን የልጅነት ምስክር ወረቀት ብቻ መሰረት አድርጎ ሟች የሕፃኗ አባት ናቸው በማለት የሠጠው ውሳኔ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ሐምሌ 08 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካቾች ጠበቃም ነሐሴ 20

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me join telegram

ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሲታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው የልደት ምስክር ወረቀት ለተጠሪ የተሠጠው አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ሕዳር 06 ቀን 1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ጥር 18 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን፣ ይህንኑ የልደት ምስክር ወረቀት የሠጠው አካልም ሥልጣን ያለው ሆኖ ማስረጃውን ያልሰረዘው መሆኑን፣ ተጠሪ ከዚህ የሰነድ ማስረጃ በተጨማሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ማስረጃ የሰው ምስክሮችን የሚጨምር መሆኑን የስር ፍ/ቤት በጉዳዩ ሳይ ውሳኔ የሠጠው የሰነድ እና የሰው ምስክሮች ቃል በመመዘን መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜም ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ የህፃን ሐና አባት መሆናቸው በልደት ምስክር ወረቀትና በምስክሮች ቃል ተረጋግጧል የሚል ስለመሆኑም የውሳኔው ግልባጭ በግልፅ የሚያሳይ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ ልጅነት ደግሞ በቀዳሚነት በልጅነት የምስክር ወረቀት የሚረጋገጥ ሲሆን የልጅነት ምስክር ወረቀት ከሌለ ደግሞ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማሳየት እንደሚረጋገጥ፣ የልጅነት ሁኔታ የሌለ ከሆነ ሲሆንም ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት እንደሚቻል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ እንደቅደም ተከተሉ በአንቀፅ 156፣ 168፣ 158፣ እና 169 ስር ደንግጓል፡፡ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ደግሞ የልደት ምስክር ወረቀት ለተጠሪ የተሠጠበት ጊዜ ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሞቱ በኋላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የልደት ምስክር ወረቀት አባት ነው የተባለው ሰው ከሞተ በኋላ የተሠጠ ሆኖ ሲገኝ ዋጋ የለውም የሚል የሕግ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ማስጃው በተገቢው አካል እስካልተሰረዘ ድረስ ዋጋ አለው በማለት ከተጠሪ የሰው ምስክሮች ቃል ጋር አዛምዶ በመመዘን ክብደት መስጠቱ በማስረጃ አቀባበል ሳይ የተፈፀመ ስህተት ስለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲታይ መሰረት ያደረገው ማስረጃ ምዘናን ነው፡፡ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ የሰበር ችሎት ስልጣንና ኃላፊነት አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3/ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 እና 22 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ሳይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ሊፀና የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57322 ጥቅምት 10 ቀን 2001 ዓ.ም በተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር ታህሳስ 01 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ሕፃን ሐና የሚች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰበር መ/ቁ 42903

ታህሳስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች:-** 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች:-** ወ/ሮ በላይነሽ ቶሎሳ - ቀረቡ

**ተጠሪ:-** 1. አቶ ተሾመ ጉተማ - ቀረቡ

2. አቶ ነገደ ፈይሳ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል::

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የከተማ ይዞታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኗ አመልካች ላይ በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 02 ማህበራዊ ፍርድ ቤት ታህሳስ 23 ቀን 2000 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ መነሻ ነው:: የክሱ ይዘትም ባጭሩ አመልካች የተጠሪዎች ይዞታ በሆነው ቦታ ላይ ገብተው አጥርና የቤት ግንብ ስለገነቡ ጉዳዩን ለቀበሌ ጽ/ቤት አመልክተን ቀበሌው የደንብ አስከባሪ ልኮ እንዲያነሱ ቢነግራቸውም ለማንሳት ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም በላይ ከመሬት አስተዳደር መሐንዲስ መጥቶ የቀለም ምልክት አድርጎ ግንባታውን እንዲያነሱ ሲነግራቸው ፈቃደኛ ስላልሆኑ በተሠጠን ካርታ መሰረት የግንባታ ፈቃድ አውጥተን ግንባታ ለማከናወን ችግር ስለፈጠሩብን አመልካች ያካሄዱትን ግንባታ አፍርሰው እንዲያነሱ ይወሰንልን የሚል ነው:: የአሁኗ አመልካችም በተከሳሽነት ቀርበው ጉዳዩን ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን ተጠሪዎችም ክስ ለመመስረት መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ግንባታውን እንዲያነሱ በመሀንዲስም ሆነ በሌላ አካል ያልተወሰነ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሲሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል::

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተነሱትን የአመልካችን የክርክር ነጥቦችን ውድቅ ከአደረገ በኋላ በፍሬ

ነገር ረገድም ስክርክሩ ምክንያት በሆነው ቦታ ገመድ በመወጠር ግራ ቀኙ ተስማምተው እንዲኖሩ ጥረት ከአደረገ በኋላ አመልካች ጉዳዩ በሕግ እንዲያልቅ በመግለፃቸው ቦታውን ተገቢው አካል በመሐንዲስ አስለክቶ ውጤቱን ስፍርድ ቤቱ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሠጥቶ መሐንዲሱ ተገቢውን ስመፈፀም ቦታው ላይ ሲገኝ አመልካች ቤታቸውን ስባስሙያው ስመክፈት ፈቃደኛ አስመሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ስባስሙያው ቤታቸውን ስመክፈት ፈቃደኛ አስመሆናቸው ክሱን እንዳመኑበት ይቆጠራል በማለት ግንባታውን አመልካች ያስምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲያፈርሱት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ስድሬዳዋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ በጉዳዩ ላይ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ጉዳዩ ስከተማው ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበበት ቢሆንም ይኸው ችሎት ያልተሟላ በመሆኑ ሳይታይ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ስማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 02 ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስረ ነገር ሥልጣን የሌስው መሆኑን ተጠሪዎች ስክርክሩ መነሻ በሆነው ቦታ ላይ መብት ወይም ጥቅም የሌሳቸው መሆኑን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሻር ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ስማየት ሥልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም? የሚለውን ነጥብ ከአዋጅ ቁጥር 416/96 አንቀፅ 41 አኳያ ስመመርመር ሲባል ጉዳዩ ስዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎች መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በጋራ በፃፉት ሁስት ገፅ ማመልከቻ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ስማየት ስልጣን አስው የሚሉበትን እና ውሳኔውም የግራ ቀኙን ክርክርና ሕግን መሰረት ያደረገ ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ሚያዚያ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ስሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ስሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር ይገባዋል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተስው መልኩ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻስው ግራ ቀኙ የሚከራከሩት በከተማ ይዞታ መሆኑን፣ ተጠሪዎች በአከራካሪው ይዞታ ላይ መብት ያላቸው መሆኑ በተገቢው አካል መረጋገጡን፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

አመልካች በተጠሪዎች ይዞታ ላይ ያላግባብ ግንባታ ማከናወናቸው ተረጋግጦ በክፍሉ መሐንዲስ የቀለም ምልክት መደረጉን ነው፡፡ አመልካች ከክርክሩ በኋላ የክፍሉ መሐንዲስ ቦታውን በተመለከተ እንደገና እንዲያጣራ በፍርድ ቤቱ በተሠጠው ትዕዛዝ መሰረት ቦታው ላይ ሲገኝ ቤታቸውን ለመክፈት ፈቃደኛ ሳይሆኑ የቀሩ መሆኑም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነጥብ መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በይዞቱ የይዞታ ድንበር ክርክር ሲሆን ጉዳዩን የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ለማየት የስረ ነገር ሥልጣን የነበረው መሆን ያለመሆኑንም ከአዋጅ ቁጥር 416/96 አንቀጽ 33 እና 41 ድንጋጌዎች ይዘት ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየቱ በአመልካች መብት ላይ ያስከተለው ችግር የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በተለይም ጉዳዩን የድሬዳዋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በደግባኝ ማየቱ ሲታይ በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ጉዳዩን የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ማየቱም ሆነ የተሠጠው ውሳኔ ውጤት ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ስላልተቻለ ውሳኔው ሊፀና የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 02 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 059/2000 የካቲት 24 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00174/2000 ጥቅምት 14 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://chilot.me
https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram

የሠበር መ/ቁ 43067

ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች:-** ኪንግናም ኢንተርፕራይዝ ሊሚትድ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ:-** አቶ ወይሻ ወዴቦ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንብረት ካሣ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሣሽነት ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ይዘትም፤ የአሁኑ አመልካች የመንገድ ሥራ በቤቴ አካባቢ በሚያከናውንበት ጊዜ በቤቶቼና በሌሎች ንብረቶች ላይ ጠቅላላ ግምቱ ብር 500,000.00(አምስት መቶ ሺህ) የሆነ የመሰነጣጠቅ ጉዳት አድርሷል በማለት ዘርዝረው ይህንኑ የንብረት ግምት አመልካች እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚደሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተከሳሽነቱ ቀርቦ በተጠሪ ንብረቶች ላይ ደረሰ የተባለው መሰነጣጠቅ በአመልካች ድርጊት ሳይሆን በተፈጥሮና በእርጅና ምክንያት የተከሰተ መሆኑን፣ በአመልካች ድርጊት የደረሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩንና ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካችን ደረሰ ስተባለው የንብረት ጉዳት ኃላፊ በማድረግ በጠቅላላ ብር 25,144.81(ሃያ አምስት ሺህ አንድ መቶ አርባ አራት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ ቀርቦ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በሚል ምክንያት ተዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቀርበዋል፡፡ ይዘቱም በጭሩ በንብረቶቹ ላይ ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ድርጊት መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ስላልሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በፁሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ነው የተባለው የድርጅቱ እንቅስቃሴ ጉዳቱን ማድረሱ ተረጋግጦ ነውን? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለክሱ መሰረት ያደረገው የአመልካች ድርጅት የመንገድ ሥራ በቤቴ አካባቢ በሚያከናውንበት ጊዜ (የድንጋይ ካካ ሲቆፍር) በቤቶቹ ላይ የመሰነጣጠቅ ጉዳት በማድረሱ ምክንያት ለደረሰው የንብረት ጉዳት ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል በሚል መሆኑን፣ ይህንኑ የተጠሪን ክስ ይዘት ለማረጋገጥም የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በስር ፍርድ ቀርበው ያረጋገጡት ፍሬ ነገር በተጠሪ ቤት ላይ መሰነጣጠቅ መድረሱን ሆኖ የመሰነጣጠቁ ጉዳት መቼ፣ በምን ምክንያት እንደሆነ ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ ሰው ከውል ውጪ ኃላፊነት ሊኖርበት የሚችለው የራሱ ወይም የሌላ ሰው ድርጊት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ ወይም ንብረቱ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ማድረሱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በጉዳቱ እና በምክንያቱ መካከል ግንኙነት መኖሩ ሲረጋገጥ ይገባል፡፡ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ ኃላፊነት ሊኖር አይችልም፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ቤት የመሰነጣጠቅ ጉዳት የደረሰው በአመልካች ድርጅት የስራ እንቅስቃሴ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ በጉዳዩ ላይ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ የአመልካች ድርጅት የስራ እንቅስቃሴ ለተጠሪ ቤት መሰነጣጠቅ ምክንያት ሊሆን ይችላል ለማለት የማያስችል መሆኑን በግልፅ መጥቀሱ በአመልካች ድርጅት የስራ እንቅስቃሴና በጉዳቱ መካከል ግንኙነት ስለመኖሩ ያለመረጋገጡን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ድርጅት የስራ እንቅስቃሴው በተጠሪ ቤት ላይ ለደረሰው መሰነጣጠቅ ምክንያት መሆኑ ሳይረጋገጥ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆንበት ምክንያት ስለሌለ የስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me join telegram

# ው ሳ ኔ

1. በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 05932 ሚያዚያ 16 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 22422 ጥር 06 ቀን 2000 ዓ.ም፣ በዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 25618 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ድርጅት የስራ እንቅስቃሴው በተጠሪ ቤት ላይ ለደረሰው መሰነጣጠቅ ምክንያት ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡

3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 43499

ታህሳስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

**አመልካች:-** አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት - ነ/ፈጅ ጀማል አህመድ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት አዋሳ ቅርንጫፍ -

ነ/ፈጅ ክንፈ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአረቦን ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ሰኔ 14 ቀን 1999 ዓ.ም በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ተጠሪ ለአመልካች ድርጅት ሠራተኛው በስራ ላይ ለሚደርስበት አደጋ ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት የመድን ዋስትና ሽፋን በፖሊሲ ቁጥር ኤን ዳብሊው /2/2/ዳብሊው/ስኢ/ኤን 0111488 እ.ኤ.አ 1988 ዓ.ም የሚፈፀም ውል በመስጠት ውሉ በየዓመቱ እየታደሰ ፀንቶ እንዲቆይ መስማማታቸውን፣ በውሉ ስምምነት የአረቦን ገንዘብ ክፍያ ልክ የሚወሰነው አመልካች ድርጅት በየአመቱ በሚልከው የሠራተኛ የስራ መደብና በዓመት በሚከፍለው የሰራተኛ ደመወዝ መጠን እየተሰላ መሆኑ መገለፁን፣ በዚሁ ስምምነት መሰረት አመልካች ድርጅ ለሐምሌ 01 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 01 ቀን 1997 እና ከሐምሌ 01 ቀን 1997 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ በስራ መደብ የሚከፈለውን የደመወዝ መጠን 3,378,445.00 በሁለቱም ዓመታት ክፍያ እንደሚፈፀም ለመድን ሰጪ ድርጅት ማሳወቁንና በዚሁ ደመወዝ መጠንም የአረቦን ገንዘብ ክፍያ በዓመት 48,018.82 መሆን ይገባ የነበረው፣ በሂሳብ ስህተት ምክንያት ለሁለቱም ዓመታት መድን ገቢ ድርጅት ብር 4,806.38 ክፍያውን እንዲፈፅም መድን ሠጪን በመጠየቁ ምክንያት ክፍያው ሲፈፀም መቻሉን፣ በስህተት የተከፈለው ገንዘብ ተቀንሶ ብር 86,424.88(ሰማንያ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሃያ አራት ብር ከሰማንያ ስምንት ሳንቲም) በመድን ገቢ ድርጅት ለመድን ሰጪ ድርጅት ሊከፈል የሚገባ የአረቦን ገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ክፍያ መኖሩን በመግለፅ ይህንኑ ገንዘብ የአሁኑ አመልካች እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሠጠው መከላከያ መልስ፣ የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም የተጠየቀው የአረቦን ገንዘብ ክፍያ ጥያቄ የውል ዘመኑ አልፎ ውሉ ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው፣ በሂሳብ ስህተት ሲጠየቁ የሚገባቸው ስህተቱን የፈፀሙ የስራ መሪዎች መሆናቸውንና ከክሱ ጋር ተያይዘው የቀረቡት ሰነዶችም ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአሁኑን አመልካች መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ በማድረግ ለክሱ ገንዘብ ኃላፊ አድርጎ ብር 86,424.88፣ የዳኝነት ክፍያ ብር 2,943.00 ጨምሮ በድምሩ ብር 87,367.88(ሰማንያ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ብር ከሰማንያ ስምንት ሳንቲም) ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሠርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ድርጅት ነገረ ፈጅ ጥቅምት 05 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት አምስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚታገድ ሆኖ እያለና በውሉ መሰረትም የተፈፀመ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የን/ሕ/ቁጥር 674 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1756 ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ አመልካችን ለአረቦን ገንዘብ ክፍያ ጥያቄ ኃላፊ ማድረጋቸው ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረበው ክርክር መታለፉ ከን/ሕ/ቁጥር 674 ድንጋጌ አንፃር አግባብ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ድርጅት ሠራተኞች በስራ ላይ ለሚደርሰባቸው ጉዳት ተጠሪ ድርጅት የመድን ሽፋን መስጠቱን፣ ስለውሉ መኖር አመልካች

ድርጅትም ክርክር የሌለው መሆኑን፣ ግራ ቀኙን የሚያከራክረው የሁለት ዓመታት የአረቦን ገንዘብ ክፍያ መጠን የሂሳብ ስህተት ስለመሆኑ እና አመልካች ስህተቱ መከሰቱን በግልፅ ሳያስተባብል ክፍያው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመታት በኋላ መድን ሰጪ ድርጅ ጥያቄ ሊያቀርብ አይገባም በማለት የሚከራከር መሆኑን፣ ተጠሪ በበኩሉ የአረቦን ገንዘብ ክፍያ መጠን የሂሳብ ስህተት መከሰቱን ካወቀት ጊዜ ጀምሮ ቢሰላ ጉዳዩ በይርጋ ሊታገድ እንደማይችልና በግራ ቀኙ መካከል በነበረው ግንኙነት መሰረት አመልካች ድርጅት የሂሳብ ስህተት ከተከሰተባቸው ዓመታት በፊት እና በኋላም የመድን አረቦን ገንዘቡን በተገቢው ሂሳብ መሰረት ሲከፍል መቆየቱን ገልፃ የይርጋው ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች ለክርክሩ መሰረት ያደረገው የን/ሕ/ቁጥር 666(3) ለኢንሹራንስ መግቢያ ስለሚከፈለው ገንዘብ በኢንሹራንስ ሰጪ ተጠይቆ ከአንድ ወር በኋላ ገንዘቡ ሳይከፈል ቢቀር የኢንሹራንስ ውል ታግዶ የሚቆይ መሆኑን የሚያሳይ ድንጋጌ በመሆኑ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካች ነገረ ፈጅ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይሆንም፡፡

ለጉዳዩ አግባብነትና ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው በን/ሕ/ቁጥር 674(1)(2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ነው፡፡ በተጠቀሰው አንቀፅ ንዑስ ቁጥር አንድ መሰረት በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ የሚታገደው ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከተደረገበት ወይም በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት በኋላ መሆኑን ሲደነገግ፣ የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ የተሸሸገ ወይም በሐሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ ያጋጠመ ሲሆን የይርጋው ዘመን የሚታሰበው ኢንሹራንስ ሠጪው ይህንን ነገር ካወቀበት ቀን ጀምሮ ነው ሲል ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም በኢንሹራንስ ምክንያት የሚቀትብ ማንኛውም ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን ሕጉ በግልፅ ያሳያል፡፡

በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ የሒሳብ ስህተት መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ጊዜው መቆጠር ያለበት ሲሆን ይህ ጊዜ መነሻ ሲሆን በሕጉ የተመለከተው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ አላለፈም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የደረሱበት ድምዳሜ በን/ሕ/ቁጥር 674 ድንጋጌን ይዘትና መንፈስና ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ ሌላው አመልካች ድርጅት የሚከራከርበት ነጥብ ውሉ በክፍያው ዘመን ከተፈፀመ በኋላ ቀሪ የአረቦን ክፍያ ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተዋዋይ ወገን መፈፀም የሚገባውን ግዴታ ሙሉን ሳይፈፅም በቀረበት ሁኔታ ግዴታው ተፈፅሟል ተብሎ ሌላው ተዋዋይ ወገን ጥያቄ እንዳያቀርብበት የሚያደርግ የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ግዴታውን በሂሳብ ስህተት ያልፈጸመ በመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

በፍ/ሕ/ቁጥር 1756 ስር በተመለከተው የመክፈያ ዘመን ድንጋጌ መሰረት ተጠቃሚ ሲሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ስማለት ስላልተቻለ ሊፀና የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09335 ታህሳስ 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25669 ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ስተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰ/መ/ቁ 43527

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሀይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኦስትሪያ ኤምባሲ ዴቬሎፐመንት ኮኦፐሬሽን - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፍቅር ፀደቀ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ለፕሮግራም ሥራ አስኪያጅ የሥራ መደብ አወዳድሮ ለመቀጠር ባወጣው ማስታወቂያ ተወዳድሬ በማሸነፌ ከኅዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም እስከ ኅዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም ለ10 ተከታታይ ቀናት እንድሰራ ተዋውለን በመሥራት የሥራ አፈጻጸሜ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ከኅዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ለአንድ ዓመት ጸንቶ በሚቆይ ውል ላልተወሰነ ጊዜ ተዋውለን በመሥራት ላይ እንዳለሁ ተከሳሽ በውሉ አንቀጽ 3(ለ) ላይ የተመለከተው የሙከራ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት የሥራ ውሉን አቋርጫለሁ ሲል ጥር 2 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከሥራ አሰናብቶኛል፡፡ ኅዳር 21 ቀን 2001 ዓ.ም ባደረግነው ውል አንቀጽ 3(4) ላይ ሠራተኛው በአሠሪው ደመዎዝ እየተከፈለው አሰሪው ጋር መስራት ከጀመረበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ለቀጣዮቹ 45 ቀናት ለሙከራ ጊዜ ይቀጠራል ይላል፡፡ ከሳሽም ደመዎዝ እየተከፈለኝ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ መሥራት የጀመርኩት የመጀመሪያውን የሥራ ውላችንን በተፈራረምንበት ቀን ማለትም ኅዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም ሲሆን ይህ ውላችን ኅዳር 20/2000 ዓ.ም የሚያበቃ በመሆኑ በማግስቱ በተፈራረምነው ውል መሠረት የአሠሪና

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ሠራተኛ ግንኙነታችን ሳልተወሰነ ጊዜ ተራዝሟል፡፡ ተቀጥሬ መሥራት ከጀመርኩበት ኅዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም በተከሳሽ የሥራ ውል እስከተቋረጠበት ጥር 2 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ በሥራ ላይ የቆየሁት ለ54 ተከታታይ ቀናት ነው፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ የሥራ ውሉን ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ስለሆነ ወደ ሥራዬ እንድመለስ ወይንም ደግሞ በሕጉ ላይ የተመለከቱት የተለያዩ ክፍያዎች ተፈጽመውልኝ ልሰናበት በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽም በሰጠው መልስ ከሳሽ ከኅዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም እስከ ኅዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በምክር ሰጭነት ተቀጥረው ሲያገለግሉ ከቆየ በኋላ ይህ ውል በስምምነት ቀሪ ተደርጎ ከኅዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በሌላ ውል የተተካ ሲሆን በአዲሱ ውል አንቀጽ 3 መሠረት የሙከራ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት የሥራ ውሉን ማቋረጥ ስለሚቻል በዚሁ መሠረት የ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ተከሳሽ ውሉን ያቋረጠ በመሆኑ ስንብቱ ከሕግ ውጭ ነው ተብሎ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ በምክር ሰጭነት ውሉ መሠረት ከተከሳሽ ጋር መሥራት የጀመሩት ኅዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም ስለሆነ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሙከራ ጊዜው መቁጠር እንደሚጀምር ግራ ቀኙ ኅዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት ውል አንቀጽ 3 ከተመለከተው መገንዘብ ስለሚቻልና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(7) መሠረት የሠራተኛው የሙከራ ጊዜ ካለቀ በኋላ ሥራውን ከቀጠለ ለሙከራ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ በውሉ በታቀደው ጊዜ እንደተቀጠረ ይቆጠር በማለት ስለተደነገገ ተከሳሽ የሥራ ውሉን ያቋረጠው ለሙከራ የተስማሙበት ጊዜ ካለቀ በኋላ በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ብሎ ከሳሽ የ6 ወር ደመዎዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሳሽ በዚሁ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የሥራ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ መታየት እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ምላሽ የሚያሻውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ተጠሪን ከሥራ ማሰናበቱ በሕጉ አግባብ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል መጀመሪያ የተደረገው ምክር የመስጠት ሥራ ውል /Consulting Agreement/ የሚቆየው ከኀዳር 9 ቀን እስከ ኀዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ እንደሆነ በውሉ አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተ ሲሆን ግራ ቀኙም በዚህ ላይ ክርክር የላቸውም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ግራ ቀኙ ኀዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፈራረሙት የሥራ ውል /contract of employment/ ከኀዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ውሉ ጸንቶ እንደሚቆይ በዚሁ ውል ላይ ተመልክቷል፡፡

ሁለቱ ወገኖች ለሁለተኛ ጊዜ በተዋዋሉት ውል ውሉ ተፈጻሚ የሚሆነው ከኀዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን ከተስማሙ አስቀድሞ ከኀዳር 9 ቀን እስከ ኀዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ያደረጉት የምክር ሥራ ውል ቀሪ በማድረግ ሌላ ውል የተዋዋሉ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የቀድሞው ውል ቀሪ ከሆነ ደግሞ ለመብትም ሆነ ለግዴታ ምንጭ ሊሆን አይችልም፡፡ ሁለተኛው ውል ግን ተፈጻሚነት ያለው ሲሆን በዚሁ ውል አንቀጽ 3(ሀ) ላይ ሠራተኛው በአሰሪው ደመዎዝ እየተከፈለው መሥራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ከጀመረበት ቀን አንስቶ ለቀጣዮቹ 45 /አርባ አምስት/ ቀናቶች ለሙከራ እንደሚቀጠር ተመልክቷል፡፡ ማንኛውም ተዋዋይ ወገንም በሙከራ ጊዜ ውስጥ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልገው የሥራ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል በዚሁ የውሉ አንቀጽ 3 በፊደል (ለ) ላይ ተመልክቷል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ረገድ ያደረጉት ስምምነትም ከአዋጅ ቁጥር 377/96 ስለሙከራ ጊዜ /probation period/ ከተደነገገው አንቀጽ 11 ጋር የተጣጣመ ነው፡፡

አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል ያቋረጠው ጥር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንደሆነ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ሲሆን የሥራ ውሉ ከተደረገበት ከኀዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ውሉ እስከተቋረጠበት እስከ ጥር 2 ቀን 2000 ዓ.ም ጊዜ ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ በውሉም ሆነ በሕጉ ላይ ከተመለከተው የ45 ቀን የሙከራ ጊዜ በላይ ስላልሆነ በዚሁ ጊዜ ውስጥ አመልካች የሥራ ውሉን ማቋረጡ የሕግም ሆነ የውል ድጋፍ ያለው ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ ስምምነት ቀሪ የተደረገውን ውል በመጨመር የሥራ ስንብቱ የተደረገው የሙከራ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኂላ ስለሆነ ስንብቱ ሕገወጥ ስለሆነ ተጠሪ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 12988 መስከረም 2/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራለ ከ/ፍ/ቤትም በመቁ …….. በ22/5/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል ያቋረጠው በሕግ አግባብ ስለሆነ ተጠሪ ወደ ሥራ ሊመለሱ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram

የሰበር መ/ቁ 43561

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሃይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካቾች፡-** 1. ዑመር መሐመድ - ቀረቡ

2. ሰልማን አማን }

3. ከማ ዋቤ } አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** እስላማዊ ደዕዋና ዕውቀት ማሕበር

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የስራ ውላቸው በህገ ወጥ መንገድ በመቋረጡ ወደ ስራ እንዲመለሱ ክስ መስርተው ወደ ስራ የተመለሱ መሆኑን ገልፀው ነገር ግን ወደ ስራ እንዲመለሱ ከተወሰነላቸው በኋላ ተጠሪ ይግባኝ በማቅረብ ሲሞግታቸው በወቅቱ ወደ ስራ ያልመለሳቸው በመሆኑ በይግባኝ ክርክር ወቅት ያልተከፈላቸው ደሞዝ እንዲከፈላቸው እና ወደ ስራ ከተመለሱም በኋላ በተመሳሳይ የስራ መደብ ለሚሰሩ ሰራተኞች በወር ብር 300 እየከፈለ ለአመልካቾች ብር 150 ብቻ የሚከፍል በመሆኑ ወደስራ ከተመለሱ ጀምሮ ለሌሎቹ የተደረገው የደሞዝ ጭማሪ ለእነሱም እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም በመልሱ ይግባኝ አቅርቦ ስለተወሰነበት ለአመልካቾች የ6 ወር ደሞዝ ከፍሎ ወደስራ የመለሳቸው በመሆኑና ሳልተሰራ ስራ ደሞዝ ሲከፈል ስለማይገባ ጥያቄው ተቀባይነት እንደሌለውና ለሌሎች ሰራተኞች ብር 300 የሚከፈለው አዲስ ቅጥር በመሆናቸው እንጂ የደሞዝ ጭማሪ ተደርጎ ስላልሆነ ጥያቄው ውድቅ እንዲደረግለት አመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ይግባኝ በቀረበ ጊዜ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በፍ/ቤት ትዕዛዝ ታግዶ የነበረ በመሆኑና ሳልተሰራ ስራ ደሞዝ ሲከፈል ስለማይገባ ሳልሰሩበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፈል የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም እንዲሁም ተጠሪ

https://chilot.me
https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram

ያደረገው ደሞዝ ጭማሪ የሌስና ሌሎቹ በአዲስ መስፈርት የተቀጠሩ በመሆኑ አመልካቾች የደሞዝ ጭማሪ ይደረግልን በማለት ሲጠይቁ አይችሉም ሲል ወስኗል:: አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቀርበው ፍ/ቤቱን ቅሬታውን ባለመቀበል ይግባኙን ሰርዞታል:: የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው:: ይህ ችሎትም በተመሳሳይ የስራ መደብ ለሚሰሩ ሰራተኞች የሚከፈለው ደሞዝ ለአመልካቾች የተከለከለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ቀርቦ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል:: ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል::

ከመዝገቡ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች ክስ ካቀረቡበት ጥያቄዎች አንደኛው በተመሳሳይ የስራ መደብ ለሚሰሩ ሰራተኞች የተደረገው የደሞዝ ጭማሪ ለአመልካቾች እንዲሰጣቸው ነው:: የስር ፍ/ቤት በተመሳሳይ የስራ መደብ ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች የደሞዝ ጭማሪ አለመደረጉን ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ነው:: በመሆኑም አመልካቾች የደሞዝ ጭማሪ መደረጉን ሳያስረዱ ደሞዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም:: በሌላ በኩል ጥያቄያቸው ደሞዝ ጭማሪ ሳይሆን በተመሳሳይ የስራ መደብ በሚሰሩ ሰራተኞች መሃከል ልዩነት ሲደረግ አይገባም የሚል ነው ቢባል እንኳን አመልካቾች በእነሱና በሌሎቹ ሰራተኞች መሃከል የስራ መደብ ተመሳሳይነት መኖሩን ከመግለፅ በቀር በአቀጣጠር፣ በስራ ልምድ፣ በትምህርት ደረጃ፣ እና በሌሎች መመዘኛዎች በሙሉ ተመሳሳይ መሆናቸውን የገለፁትም ሆነ ያስረዱት ነገር የለም:: የስራ መደቡ ተመሳሳይ ቢሆንም እንኳን በተለያዩ መስፈርቶችና መመዘኛዎች የደሞዝ ልዩነት እንዳይደረግ የሚከለክል ህግ የለም:: በአጠቃላይ አመልካቾች የስራ መደቡን መመሳሰል ብቻ እንደምክንያት በመውሰድ ደሞዛቸው እንዲጨመር ያቀረቡት ጥያቄ የህግ ድጋፍ የሌለው ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት ፈፅመዋል ለማለት አልቻልንም::

## **ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33546 ጥቅምት 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 73110 ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል::
2. አመልካቾች ያቀረቡት የደሞዝ ይጨመርልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል::
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ::

መዝገቡ ተዘግቷል:: ለመዝገብ ቤት ይመለስ::

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 43651

ታህሳስ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች:-** አቶ ዑስማን መሐመድ ቀረቡ

**ተጠሪ:-** 1. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጎንደር ቅርንጫፍ

አቶ አክሊሉ ተስፋዬ ቀረቡ

2. ደልጊ ከተማ መሬ ማዘጋጃ ቤት አልቀረቡም

3. አቶ ብርሀኑ ሽፈራው አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 33952 የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የአሁን አመልካች ለሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ አንደኛ ተጠሪ ለሶስተኛ ተጠሪ ብድር ሲሰጥ መያዣነት የያዘውን አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬትና 50x50 ካሬ ሜትር ካርታና ፕላን ያለው የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክት ሶስተኛ ተጠሪ ብድሩን ባለመክፈሉ ምክንያት በጨረታ ሲሸጥ እኔ በጨረታው ተወዳድሬ አሸንፌ ገዝቻለሁ፡፡ ሆኖም በጨረታ የገዛሁትን አንድ ሄክታር የግጦሽ ቦታና 50x50 ካሬ ሜትር የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክት ለማስረከብና ንብረትነቱን ለማዛወር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እንዲያስረክቡኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክት በብር 14,000 (አስራ አራት ሺህ ብር) የሸጠ መሆኑን አምኖ ነገር ግን ባንኩ ለአመልካች የሸጠው 50x50 ሜትር የሆነ የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክት ለገዥው አስረክቧል ከዚህ

ውጭ ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ መሪ ማዘጋጀ ቤቱ ለአመልካች ንብረትነቱን በማዛወር የሚመዘግብት ሶስተኛ ተጠሪ ህጋዊ ካርታና ፕላን ባወጡበት 50x50 ሜትር የሆነ የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክት እንጅ አንድ ሄክታር ባዶ መሬት የማስተላለፍ ግዴታ የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ ባንክ ብድር ሲሰጥ በመያዣነት የያዘውና በጨረታ የሸጠው 50x50 ሜትር የሆነ የከብት ማድለቢያ መሆኑን ገልፀው አመልካች አንድ ሄክታር መሬት ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ተገቢ አይደለም የሚል ክርክር አቀርበዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረበውን ክስና ማስረጃ እንደዚሁም በተጠሪዎች በኩል የቀረበውን ክስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች የሸጠው 50x50 ሜትር የከብት ማድለቢያ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህንን የከብት ማድለቢያ ተጠሪዎች ሲያስረክቡትና ሲያዛውሩለት ይገባል፡፡ አመልካች አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት ለመረከብ ያቀረበው ጥያቄ ህጋዊነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ ብድር እንዲያበድረው ሲጠይቅ አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት ያለው መሆኑን ገልጿል በሚል ምክንያት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ ተጠሪዎች ለአመልካች 50x50 ሜትር ያለው የከብት ማድለቢያና አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት እንዲያስረክቡ በማለት የከፍተኛው ፍረድ ቤት ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አንደኛ ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች በየበኩላቸው ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪዎችን የይግባኝ መዛግብት በማጣመር ከመረመረ በኋላ፣ አንደኛ ተጠሪ ለሶስተኛ ተጠሪ ሳበደረው ብድር የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክቱን በመያዣነት ሲይዝ ለአንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት በመያዣ ስንጠረዥ ውስጥ ያልተገለፀና ያልተካተተ መሆኑን በመግለፅ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት ለአመልካች እንዲያስረክቡ የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክት አካል ነው፡፡ ስለዚህ የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክቱን በጨረታ የገዛሁ በመሆኑ ለእኔ ሲተላለፍ ሲገባው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1138 በሚቃረን መንገድ አይተላለፍልህም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት ለሶስተኛው ተጠሪ የተሰጠው በከብት ማድለቢያ ፕሮጀክቱ ምክንያት ነው፡፡

ስለሆነም አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት አይገባህም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች የአመልካች የሰበር አቤቱታ ከደረሳቸው በኋላ በየበኩላቸው መልስ የሰጡ ሲሆን አንደኛ ተጠሪ የሸጥንላቸው 50x50 ካሬ ሜትር የሆነ የከብት ማድለቢያ ድርጅት ነው፡፡ አመልካች ባንኩ የትብብር ደብዳቤ ቢፅፍልን ከአቀራቢያው ያለው አንድ ሄክታር የግጦሽ መሬት መሬ ማዘጋጃ ቤት ይሰጠኛል ስላሉ የትብብር ደብዳቤ የፃፍንላቸው ሲሆን ይህንን ደብዳቤ በማስረጃነት በመያዝ ያልገዙትን ንብረት ለመረከብ ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ የከብት ማድለቢያ ፕሮጀክቱ የተጠሪና 2,500 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ነው፡፡ አመልካች በውሉ ያልተካተተውንና በክፍትነት የተቀመጠውን አንድ ሄክታር (10,000 ካሬ ሜትር) ቦታ ለመውሰድ ያቀረቡት ክርክር ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን ሶስተኛ ተጠሪ በበኩሉ አንደኛ ተጠሪ ከእኔ ተረክቦ የሸጠው 50x50 ካሬ ሜትር ያለ የከብት ማድለቢያ ድርጅት ሆኖ እያለ አመልካች አንድ ሄክታር የግጦች መሬት መጠየቃቸው ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በተናጠል ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪ በዕዳ ምክንያት ለአመልካች በጨረታ የሸጠው የሶስተኛው ተጠሪ ንብረት የሆነው የከብት ማድለቢያ ድርጅት 50x50 ሜትር ማለትም በ2,500 ካሬ ሜትር ላይ የሚከናወንና ለዚህም በደልጊ ከተማ መሬ ማዘጋጃ ቤት ህጋዊ ካርታና ፕላን የተሰጠው ድርጅት ነው፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛው ተጠሪ ገንዘብ ሲበደር በብድር ውሉ የመያዣ ንብረት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ላይ የተመዘገበውም ይኸው 50x50 ሜትር ካሬ ላይ ያለው የከብት ማድለቢያ መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አረጋግጦ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንዲሸጥ የሚፈቅድለት ብድር ሲያበድር በህጋዊ መንገድ በመያዣነት የያዘውን ንብረት (ድርጅት) ነው፡፡ አመልካች ከከብት ማድለቢያ ድርጅቱ ጋር አብሮ ተሸጦልኛል በማለት ክርክር ያቀረቡበት 10,000 (አስር ሺ ካሬ ሜትር) መሬት ለሶስተኛ ተጠሪ ከብት ማድለቢያ ፕሮጀክት ካርታና ፕላን ሁለተኛ ተጠሪ ያልሰጠውና ከተማው የሚያስተዳድረው ክፍት መሬት መሆኑን ሁለተኛው ተጠሪ የሚያቀርበውን ክርክር የሚደግፍ ማስረጃ ያቀረበ ስለመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

አንደኛ ተጠሪ በመያዣነት ያልያዘውንና በሀራጅ ያልሸጠውን አንድ ሄክታር መሬት (10,000 ካሬ ሜትር) ቦታ በመጨመር ሁለተኛው ተጠሪ ስመ ንብረት እንዲዛወርለት ደብዳቤ የፃፈው አመልካች ባንኩ የትብብር ደብዳቤ እንዲፅፍላቸው ስለጠየቁ መሆን በማንሳት አንደኛ ተጠሪ የሚከራከር ሲሆን መሬቱ በህጋዊ መንገድ የተሸጠው የከብት ማድለቢያ ድርጅት አካል ስመሆኑ አጥጋቢ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ አመልካች ይህንን አንደኛ ተጠሪ የፃፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ አንድ ሄክታር መሬት የከብት ማድለቢያው አካል ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው የሚያቀርቡት ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች ክርክር ያቀረቡበት አንድ ሄክታር መሬት የከብት ማድለቢያው አካል መሆኑን የሚያሣይ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (በሁለተኛው ተጠሪ የተሰጠ ካርታና ፕላን) በሌለበት ሁኔታ አንደኛ ተጠሪ የፃፈው ደብዳቤ አንድ ሄክታር መሬቱ የከብት ማድለቢያ ድርጅት አካል ስለመሆኑ ህጋዊ የአስረጅነት ብቃት ያለው ማሰረጃ ሲሆን አይችልም፡፡

በአጠቃላይ አንደኛው ተጠሪ ለሶስተኛ ተጠሪ ገንዘብ ሲያበድር በመያዣነት የያዘው 50x50 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያለ የከብት ማድለቢያ ድርጅት ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 97/90 በሀራጅ ለአመልካች ያሸጠውም ይህንኑ በ50x50 ሜትር (2,500 ካሬ ሜትር) ቦታ ላይ ያለ የከብት ድርጅት በመሆኑና በዚሁ ቦታ አቅራቢያ የሚገኘው አንድ ሄክታር ክፍት መሬት በከብት ማድለቢያ ድርጅቱ ካርታና ፕላን ውስጥ ያልተካተተ የደልጊ ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት የሚያስተዳድረው ቦታ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክርና በቀረበው ማስረጃ መረጋገጡን በማገናዘብ አመለካች ተጠሪዎች እንዲያስረክቧቸው የጠየቁት አንድ ሄክታር መሬት አይገባቸውም በማለት የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል
2. አመልካች ተጠሪዎች አንድ ሄክታር መሬት እንዲያስረክቧቸው ያቀረቡት ጥያቄ ህጋዊ መሠረት የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

ይኽ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

**ፊ/ታ**

https://chilot.me
https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram

የሰ/መ/ቁ 43731

ታህሳስ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ሲ.ጂ.ሲ.ኦቨርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሲሚትድ

እሴኒ አስራት ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሰለሞን እንዳስ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሌለሁበት ክርክሩ እንዲሰማ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቶ ወደክርክሩ እንድገባ ይፈቀድልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረ ሲሆን፣ መልስ እንዲሰጥ በተጠራበት ቀነቀጠሮ ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት እንዲሰማ ታዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ትዕዛዙ እንዲነሳለት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.72 መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከተመለከተ በኋላ፣ አቤቱታው ትዕዛዙ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑና የአንድ ወር ጊዜው ያለፈው በበቂ ምክንያት ስመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ትዕዛዙ ሊነሳ አይችልም በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ትዕዛዙን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ ወገኖች ያሰሙትን ክርክርም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13262 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ብይን እንደተመለከተው አመልካች ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶለት

ወደክርክሩ እንዲገባ ባመለከተበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ አልተሰጠም ነበር፡፡ ከመዝገቡ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች ተከሣሽ የነበረ ሲሆን፣ በቀረበበት ክስ በጽሑፍ መልስ ሰጥቶ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለትም የአመልካቹ ሠራተኛ የሆነ ቀርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን ክርክር ለማቅረብ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን የለህም በማለት ክርክሩ አመልካቹ በሌለበት እንዲታይ አዞአል፡፡ ከዚህ በኋላም ነው አመልካች ክርክሩ በሌለበት ይሰማል የሚለው ትዕዛዝ ተነስቶለት ወደክርክሩ እንዲገባ የጠየቀው፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ መልክ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ጥያቄው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78(1) መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አልቀረበም፡፡ በህጉ ከተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለማቅረብ ያልቻለበት በቂ ምክንያት ያለው ስለመሆኑም አላስረዳም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት የሚመራው የፍትሐብሔር ክስ በቀረበ ጊዜ ክርክሩን ለመስማት ፍ/ቤቱ በያዘው ቀነቀጠሮ ተከራካሪ ወገኖች ይቀርባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 69(1) ከተቀመጠው ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም አንዳቸው ሳይቀርቡ ቢቀሩ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የሥነ ሥርዓት እርምጃዎች በሚመለከት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.69 እስከ 78 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ክርክሩ እንዲሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ሳይቀርብ የቀረው አመልካች (ተከሣሽ የነበረው) ነው፡፡ በዚህ ቀነ ቀጠሮ የአመልካች ወኪል ነኝ በማለት የቀረበው ሠራተኛ የተሟላ የውክልና ሥልጣን የለውም በሚል አመልካች እንዳልቀረበ ተቆጥሮ ክርክሩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ የመታዘዙን አግባብነት ወደኋላ የምንመለከተው ይሆናል፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን እምነት በመያዙና ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 70(ሀ) መሠረት አመልካች በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ በመስጠቱ የተነሣ አመልካች ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ያቀረበው አቤቱታ የሚስተናገደው በምን አግባብ ነው? የሚለውን ነጥበ በቅድሚያ እንመለከታለን፡፡

በመጀመሪያው ቀነቀጠሮ ባለመቅረቡ ምክንያት ክርክሩ በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከሣሽ በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ቀርቦ በቀዳሚው ቀነቀጠሮ ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነና ፍ/ቤቱም ምክንያቱን በቂ አድረጎ የተቀበለው እንደሆነ በቀረበበት ቀን መከላከያውን አቅርቦ እንዲከራከር እንደሚፈቅድለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 ተደንግጎአል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተቀመጡት ዋነኞቹ ነጥቦች አቤቱታው የሚቀርበው በሚቀጥለው ቀጠሮ ማለትም ጉዳዩ በውሳኔ ከመቋጨቱ በፊት መሆኑን እና በቀዳሚው ቀነ ቀጠሮ ሳለመቅረብ በቂ ሆኖ የሚገመት ምክንያት (እክል) መኖር ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ድንጋጌው አቤቱታው የሚቀርብበትን ግልጽ የሆነ የጊዜ ገደብ አላስቀመጠም፡፡ በዚህ

ይዘቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78(1) ከተደነገገው የሚለይ ነው፡፡ የኋለኛው "ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ስለማንሳት" የሚል ርእስ ያለው ሲሆን፣ የመጀመሪያው ግን "በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ስለመቅረብ" በሚል የተደነገገ ነው፡፡ ከዚህም በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ያለውን ልዩነት ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እና ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሚል ሊለይ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 እና 78 መካከል ያለው ልዩነት ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ የቀረ ነገር ግን በሚቀጥለው ቀነ ቀጠሮ የቀረበው ተከሣሽ ጥያቄው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78(1) አኳያ የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቁ. 78(1)ን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ያየው በአግባቡ አይደለም፡፡

በመቀጠል ያየነው አመልካች በአንድ ወር ውስጥ ቀርቦ ያላመለከተበትን ምክንያት አላስረዳም የሚለው የፍ/ቤቱ ትችት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለጽነው አመልካች አቤቱታውን ለማቅረብ የቀናትም ይሁን የወራት ገደብ አልተቀመጠለትም፡፡ በመሆኑም እንዲያስረዳ የሚጠበቀው ክርክሩ ሲሰማ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበበትን ምክንያት ነው፡፡ ለክሱ መልስ በተሰጠበት ጊዜ በኋላ በቃል የመከራከር የተሟላ ውክልና የለህም የተባለው ሠራተኛው ከመቅረቡም በላይ፣ መልሱን እራሱ ፈርሞ እንዳቀረበው በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ጉዳዩን ለመስማት (በቃል) ቀጠሮ በተያዘበት ዕለትም ይኸው ለመከራከር ይችላል ተብሎ ከአመልካች ውክልና የተሰጠው ሠራተኛ የቀረበ በመሆኑ ቢያንስ በኋላ ትዕዛዙ እንዲነሳለት ላቀረበው አቤቱታ አወሳሰን እንደበቂ ምክንይት ተደርጎ ሊወሰድለት ይገባ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች ያቀረበው በጽሑፍ የተዘጋጀው መልስ ከመዝገቡ የተያያዘ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከዚህ በመነሳት ወደፊት ያለውን ክርክሩ መስማት ሲገባው ወደውሳኔ ማምራቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ለናጠቃልለው ፍ/ቤቱ ክርክሩን የመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 የተቀመጠውን ድንጋጌ በአግባቡ ሳይጠቀም በመሆኑ አፈጻጸሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13262 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 72956 የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ከገባበት ቀን ጀምሮ ወደፊት ያለውን ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 43886

ታህሳስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገረፈጅ አቶ ተሾመ መኩሪያ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጠበቃ አቶ መኮንን ሽፈራው ቀረቡ

2. ሴፍ ኮንስትራክሽን አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 64134 የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 67523 የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የካቲት 24 ቀን 2001 በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ በአመልካችና በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ንብረትነታቸው የሁለተኛ ተጠሪ የሆኑ አምስት መኪኖች አመልካች ለሁለተኛው ተጠሪ ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዛቸውና የመድን ሽፋን የተገባላቸው መሆኑን በመግለፅ ለመኪኖቹ የመድን ሽፋን በሰጡት ጊዜ መከፈል የነበረበት የአረቦን ክፍያ በድምሩ ብር 103,391.85 የሚፈለግባቸው ስለሆነ አመልካችና ሁለተኛ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ አንደኛ ተጠሪ ክስ ሊያቀርብብኝ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ለመኪኖቹ የመድን ሽፋን እንዲሰጥለት የመድን ውል የፈፀመው ሁለተኛው ተጠሪ ስለሆነ የአረቦን ክፍያውን መክፈል ያለበት ሁለተኛው ተጠሪ መሆን እንዳለበት አመልካች የመድን ውሉ እንዲታደስ ማድረጉም አረቦን የመክፈል ግዴታ የማያስከትልበት መሆኑን በማንሣት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካችና ሁለተኛ

ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ ከጥር 26 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱ የንግድ ህግ ቁጥር 661 ንዑስ አንቀፅ 2 ተገቢ የሆነ የድንጋጌውን አቀራረፅ ይዘትና ዓላማ ባገናዘበ መልኩ መተርጎም ሲገባው የተሳሳተ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ የንግድ ህግ ቁጥር 661 ንዑስ አንቀፅ 2ን ከንግድ ህግ ቁጥር 666(2) እና ከንግድ ህግ ቁጥር 666(3) ጋር በማገናዘብ ትርጉም መስጠት ይገባው ነበር፡፡ ባንኩ የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ እንጂ ኢንሹራንስ ገቢ አይደለም፡፡ ባንኩ የኢንሹራንስ ውል ሲከፍል የነበረው በመያዣ ውል አንቀፅ 9 በሁለተኛ ተጠሪ ሂሳብ በመቀነስ በመሆኑ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸው መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ለሁለተኛው ተጠሪ ደርሶት አመልካች የንብረቶቹ ባለቤት ባይሆንም ለረዥም ዓመታት የማደሻ ትዕዛዝ እየሠጠ የመድን ሽፋን ውል ገብቷል፡፡ ይኸም በንግድ ህግ ቁጥር 675(2) መሠረት የተደረገ በመሆኑ አረቦኑን የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ ባለመፈረሙ ብቻ ተጠያቂ አይደለሁም ማለቱ ተገቢ አይደለም በንግድ ህግ ቁጥር 661(2) በንግድ ህግ ቁጥር 662 እና 666 ድንጋጌዎች አመልካች ኃላፊ የሚያደርጉ ስለሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ እኔ የመድን ውል የገባሁት ከአመልካች ብድር በማግኘት ነው አመልካች በአንደኛ ተጠሪ የአረቦን ክፍያ ሲከፍል የቆየው የእኔን ገንዘብ እንጅ የአመልካችን ገንዘብ አይደለም ስለሆነም አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ በመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ሣይሰጠኝ ክስ ማቅረቡ ህጉን ያልተከተለ በመሆኑ የአንደኛ ተጠሪ ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ በኩል ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ብድር ሲያበድር በመያዣነት ለያዛቸው የሁለተኛው ተጠሪ መኪናዎች ሁለተኛው ተጠሪ በገባው የመድን ውል መሠረት ያልከፈለውን አረቦን በአንድነትና በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አንድ ሰው የሲቪል (የፍታብሔር ግዴታ) የሚኖርበት ከውል ወይም በህግ የተደነገገና ሲፈፀመው የሚገባው ኃላፊነት ሲኖርበት ነው፡፡ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር በንግድ ህግ ቁጥር 657 ወይም በንግድ ህግ ቁጥር 675 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገው የመድን ውል የሌለ መሆኑ አንደኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤትና በሰበር ካደረገው ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ለሁለተኛ ተጠሪ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚከፈል የብድር ገንዘብ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በበኩሉ ከአመልካች ለወሰደው ገንዘብ አከፋፈል ዋስትና ይሆኑ ዘንድ ንብረቶቹ የሆኑ አምስት መኪኖች በመያዣነት አስይዟል፡፡ አመልካች መያዣው አስተማማኝ ዋስትና እንዲኖረው በማሰብ ሁለተኛ ተጠሪ በመያዣነት በተያዙት ንብረቶች ላይ ለሚደርስ ጉዳት የመድን ውል እንደገባ በማድረግ ሁለተኛው ተጠሪ ለንብረቶቹ በንግድ ህግ ቁጥር 675 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የመድን ውል ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ገብቶ በየጊዜው መክፈል የሚገባውን የአረቦን ሒሳብ አመልካች ከሁለተኛ ተጠሪ ሒሳብ እየቀነሰ ለአንደኛ ተጠሪ ሲከፍል መቆየቱንና ውሉንም በሁለተኛው ተጠሪ ስም እያሳደሰ እንደቆየ መድን ገቢው ሁለተኛ ተጠሪና አመልካች በሥር ፍርድ ቤትና በሰበር ባደረጉት ክርክር ተረጋግጧል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የአረቦን ክፍያው በመያዣ ውሉ መሠረት አመልካችን ሳይሆን የሁለተኛው ተጠሪ ኃላፊነትና ግዴታ መሆኑን አምኖ ለሥር ፍርድ ቤትና በሰበር መልስ አቅርቧል፡፡ ይኸም አመልካች ከአንደኛ ተጠሪም ጋር ሆነ ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር በተደረገ ውል የአረቦን ክፍያ የመክፈል ኃላፊነትና ግዴታ የሌለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

አመልካች ከውል ያመነጨ አረቦን የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ካልን በሁለተኛ ደረጃ ማየት ያለብን አመልካች ከህግ የመነጨ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነው፡፡ አመልካች በመያዣነት የያዛቸው መኪኖች የሁለተኛ ተጠሪ ንብረቶች ናቸው፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ እነዚህን ንብረቶቹን ከጉዳት ለመጠበቅ በማሰብ በንግድ ህግ ቁጥር 675 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የኢንሹራንስ ውል ከአንደኛው ተጠሪ ጋር የገባ መሆኑ ግራቀኙ የሚተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በንግድ ህግ ቁጥር 675 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ለንብረቶቹ በገባው የኢንሹራንስ ውል መሠረት በየጊዜው መክፈል የሚገባውን የአረቦን ክፍያ ካልከፈለ ሁለተኛ ተጠሪ በንግድ ህግ ቁጥር 666 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሁለተኛውን ተጠሪ በውሉ መሠረት ክፍያውን እንዲከፍል መጠየቅ ይገባዋል፡፡

በዚህ ሒደት የአመልካችን መብትና ግዴታ ስንመለከተው አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ በመያዣነት ለተያዙት ንብረቶች በገባው የመድን ውል ቅድሚያ ተጠቃሚ እንደሆነ አመልካችና ሁለተኛ ተጠሪ ባደረጉት የመያዣ ውል ተገልጿል፡፡ ሆኖም አመልካችና ሁለተኛ ተጠሪ የዚህ አይነት ውል ባይዋዋል ወይም ከዚህ ጋር የሚቃረን ውል ተዋውለው ቢሆንም ኖሮ ሁለተኛው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me join telegram

ተጠሪ ለንብረቶቹ የገባው የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ የመሆን የቀዳሚነት መብት አመልካች እንዳለው የንግድ ህግ ቁጥር 684 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ የመድን ሽፋን ከገባላቸውና በመያዣነት ከያዛቸው ንብረቶች አንደኛው ወይም ሁሉም ጉዳት ቢደርስባቸው በንብረቶቹ ላይ  የመያዣ መብት ስላለው ብቻ ጉዳት ለደረሰበት ንብረት ወይም ጉዳት ለደረሰባቸው ንብረቶች አንደኛ ተጠሪ መክፈል የሚገባውን የኢንሹራንስ ገንዘብ የመቀበል ወይም አንደኛ ተጠሪ ከስሶ ገንዘቡ እንዲከፈለው የመጠየቅ ከህግ የመነጨ የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑን ከንግድ ህግ ቁጥር 684 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት እንችላለን፡፡

አንደኛ ተጠሪ አመልካችን አስመልክቶ ያለው መብት አመልካች የመድን ውል የተገባላቸውና በመያዣነት የያዛቸው ንብረቶች ላይ ጉዳት ደርሶባቸው ሲከፈል የሚገባውን የኢንሹራንስ ገንዘብ እንዲከፍለው የቀዳሚነት መብቱን ተጠቅሞ ሲጠይቀው ለንብረቶቹ መድን የገባው ሁለተኛ ተጠሪ በመድን ውሉ መሠረት አረቦን ክፍያ ያልከፈለው መሆኑንና ሌሎች በመከላከያነት የሚያገለግሉ ነጥቦችን በማንሳት የአመልካችን ጥያቄ ለመከላከል የሚችል መሆኑ እንደሆነ የንግድ ህግ ቁጥር 684 ንዑስ አንቀፅ 1 "ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም እንኳን ለአንድ ንብረት የሚከፈለው የኢንሹራንስ ገንዘብ በዚሁ ንብረት ላይ የቀዳሚነት ወይም የመያዣ መብት ላላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ይሰጣል፡፡ እነዚህ ገንዘብ ጠያቂዎች በኢንሹራንስ ሰጭው ላይ በቀጥታ ክስ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ <u>እርሱም ደግሞ ኢንሹራንስ በገባው ሰው ላይ ሊያቀርብ ይችል የነበረውን መከላከያ ሊያቀርብ ይችላል</u>" በማለት ካስቀመጠው ድንጋጌ የመጨረሻውን ፓራግራፍ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህም የምንረዳው ሁለተኛው ተጠሪ ለአመልካች በመያዣነት ባስያዛቸው ንብረቶች በገባው የመድን ዋስትና ውል መሠረት ግዴታውን ባይፈፅም እና በመያዣ በተያዙት ንብረቶች ላይ ጉዳት ቢደርስ አንደኛ ተጠሪ አመልካች የኢንሹራንስ ገንዘቡ እንዲከፈለው የቀዳሚነት መብቱን ተጠቅሞ የሚያቀርበውን ክስ ለመከላከል የሁለተኛውን ተጠሪ የአረቦን ክፍያ አለመክፈል በመከራከሪያነት ከሚያነሳው በስተቀር በንብረቶቹ ላይ ጉዳት ሣይደርስና አመልካች አንደኛ ተጠሪን የኢንሹራንስ ገንዘብ እንዲከፍለው ጥያቄ ባላቀረበበት ሁኔታ በንግድ ህግ ቁጥር 675(1) መሠረት ለንብረቶቹ የመድን ዋስትና ውል የገባው የንብረቶቹ ባለቤት የሆነው ሁለተኛው ተጠሪ ያልከፈለውን የአረቦን ክፍያ አመልካች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል አንደኛው ተጠሪ ያቀረበው ክስ ህጋዊ መሠረት የለውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ሁለተኛው ተጠሪ የገባው የመድን ውል በንግድ ህግ ቁጥር 675(1) መሠረት በንብረት ላይ ስሚደርስ ጉዳት የተገባ የኢንሹራንስ ውል መሆኑንና የአረቦን ክፍያውን በንግድ ህግ ቁጥር 666 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሁለተኛው ተጠሪ መሆኑን አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ያደረጉት የመድን ውል የቀዳሚ ተጠቃሚነት መብቱ የሚመነጨው ከንግድ ህግ ቁጥር 684 ንዑስ አንቀፅ 1 በመሆኑ ኢንሹራንስ ስተገባላቸው ለመያዣ የያዛቸው የሁለተኛ ተጠሪ ንብረቶች አረቦን የመክፈል ግደታና ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ሣያገናዝብ የንግድ ህግ ቁጥር 661 ንዑስ አንቀፅ 2 ጠቅሶ አመልካች ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ አረቦን እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ከላይ በዝርዝር የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች የሚፃረስ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ስህተቱን ሣያርም የአመልካችን ይግባኝ መሠረዙ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ሁለተኛው ተጠሪ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር በገባው የመድን ውል መሠረት ያልከፈለውን የአረቦን ክፍያና ወለድ አመልካች በአንድነትም ሆነ በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. አንደኛ ተጠሪ በመድን ውል መሠረት የጠየቀውን የአረቦን ክፍያና ወለድ ሙሉ በሙሉ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሁለተኛው ተጠሪ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኝ ለየራሳቸው ይቻሉ

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሠ/መ/ቁ 44164

ታህሳስ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች:-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነገረ ፈጅ ቀርበዋል

**ተጠሪ:-** አቶ ሐሰን ኢብራሂም - ጠበቃ ስለሺ ዘዬሐንስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል::

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የብድር ውልን የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪ በ05/08/87 ዓ.ም በተፈረመ ውል ብር 200,000.00 ተበድረው በየወሩ ብር 18,000 እየከፈሉ ከሚያዝያ ወር 1988 ዓ.ም የተስማሙ ቢሆንም ብድሩን በውሉ መሠረት አልከፈሉም:: በመሆኑም በመያዣነት ለአመልካች ከሰጧቸውና አመልካች የመድን ሽፋን ከገዛላቸው ተሽከርካሪዎቻቸው ውስጥ ሁለቱን ያስረከቡ ቢሆንም በሊብሬያቸው ላይ የተጭበረበረና የተምታታ ነገር በመኖሩ ሊሸጡ አልቻሉም:: ስለዚህ ተጠሪ በዓመት 14% ወለድና 3% የወለድ መቀጫ ለመክፈል በተስማሙት መሠረት የሚፈለግባቸውን ብር 396,904.52 እና ሌሎች ወጪዎችን እንዲከፍሉ ይወሰንልን ሲል ባቀረበው ክስ ነው::

ተጠሪ በሰጡት መልስ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ተሽከርካሪዎቹ ለፎርክሎዠር የሐራጅ ሽያጭ የቀረቡ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 244(2/ሐ) መሠረት አንደኛው የህግ እርምጃ እየተካሄደ ሳለ በተደራቢነት ክስ ሊመሠረትብኝ አይገባም በማለት ቅድመ መቃወሚያ አቅርበው በፍሬ ጉዳዩ መልስ ሰጥተዋል::

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ በብድር ሰጥቶ ለብድሩም መያዣዎችን ይዟል:: ብድሩ ባልተከፈለው ጊዜ በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ወይም በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የያዘውን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ገንዘቡን ማስመለስ ይችላል:: ይህ ማለት ግን ሁለቱንም አማራጮች በአንድ ጊዜ በአንድ

ሳይ ይጠቀማል ማለት አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ያበደረውን ገንዘብ ለማስመለስ በፍ/ቤት ክስ ያቀረበው በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የያዘውን ንብረት ተረክቦ በሐራጅ ለመሸጥ በእንቅስቃሴ ሳይ እያለ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በሌላ በፍ/ቤት (በባንኩ በራሱ) ተይዞ እያለ እና ተሸከርካሪዎቹ ተሸጠው የሚያወጡት ገንዘብ ለብድሩ ወይም ለዕዳው በቂ መሆን አለመሆኑ ሳይረጋገጥ በዚህ ፍ/ቤት ክስ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 244(2/ሐ) መሠረት ተቀባይነት ስለሌለው ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 245(2) መሠረት ተዘግቷል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኝ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሳይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ብድሩን ሲወስዱ ለመያዣነት ከአስያዟቸው መኪናዎች መካከል የሰሌዳ ቁጥር 2-13518 አ.አ. በብር 17,500.00(አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ) የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም በወጣው ጨረታ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-26916 የሆነው ደግሞ ነሐሴ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በወጣው ጨረታ በብር 152,000.00(አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ) መሸጣቸው እና ሌላው መኪናም ሲገኝ አለመቻሉ ተገልጾ እያለ፣ አዋጅ ቁጥር 97/90 ባንክን ክስ ከመመስረት የሚከለክለው ባለመሆኑ የብድር እዳ እንዲመልሱ በተጠሪ ሳይ የቀረበው ክስ የፎርክሎዠር ሥርዓቱን ሳይጨርስ መቅረብ የለበትም ተብሎ ውድቅ መደረጉ የአዋጁን መንፈስ ያላገናዘበ ስለሆነ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ክሱ ከቀጠለ በኋላ አመልካች በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች ሸጧል መባሉ በክርክሩ ሂደት የሚቀር ዕዳ መኖሩንና አለመኖሩን አረጋግጦ ክስ እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ በማድረግ ፋንታ በመያዣ የተያዙ ንብረቶች መሸጫውን ብቻ መነሻ በማድረግ ክርክሩን የሚያቋርጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኝ ክርክር ሐምሌ 08 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሲመረመር ይገባዋል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች የወሰዱትን ገንዘብ በወቅቱ ባለመመለሳቸው አመልካች በመያዣነት ከያዛቸው ተሸከርካሪዎች መካከል በሕጉ በተሠጠው ሥልጣን መሰረት ራሱ ለመሸጥ እንቅስቃሴ እያደረገ ባለበት ጊዜ በፍ/ቤት ተጠሪ ብር 396,904.52(ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) ከወለድና ከሌሎች ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ በተጠሪ ላይ ክስ በመመስረቱ ፍርድ ቤቱ አመልካች የፎርክሎር ሥልጣኑን ሳይጨርስ በፍ/ቤት ክስ መመስረትን ስነ ሥርዓቱ አይፈቅድም በማለት ክሱን ለጊዜው የዘጋው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች የፍርድ ሂደትን ማለፍ ሳያስፈልግ በሐራጅ የመሸጥ ሕጋዊ መብት ያለው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በእነዚህ ህጎች በተሠጠው ሥልጣን ባንኩ ሲጠቀም ሊከተለው የሚገባው ሥነ ሥርዓትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 394 እስከ 449 ድረስ ያሉትን ድንጋዎች ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ድንጋጌ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚገኙት ደግሞ ስለፍርድ አፈፃፀም በሚገዛው የተጠቃሽ ሥነ ሥርዓት ስባተኛ መፅሐፍ ስር ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው የባንኩ ስራ ተበዳሪውን በመወከል የመያዣ ንብረቱን ሸጦ ለብድሩ ዕዳ እንዲውል ማድረግ ሲሆን ይሕም በይዘቱ የአፈፃፀም አካል ሊባል የሚችል ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት አዋጆች ባንኮች በራሳቸው ምርጫ በብድር የሰጡትን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር እንዲከተሉ አስገዳጅ መንገድ ስለመሆኑ የሚያሳይ ድንጋጌ አልያዙም፡፡ በሌላ አገላለፅ ባንኮች ብድራቸውን ለማስመለስ በፍርድ ቤት በኩል ክስ ሲመሰርቱ ጉዳዩ በአዋጅ መሰረት ሲፈፀም ይገባል ሊባል የማይችል ሲሆን መያዣ ንብረቶች ላይ ከአዋጁ ባገኙት መብት መሰረት እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመራቸው በሁለት መንገድ ክስ ቀርቧል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ባንኮች በራሳቸው ምርጫ በብድር የሰጡትን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር ሳይፈፅሙ በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርቱ ወይም በመረጡት መንገድ የመሄድ ሁኔታ አዋጁ ከወጣበት ዓላማ ጋር ሊፃረር ይችላል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም፡፡ የአዋጁ አይነተኛ ዓላማ ባንኮች በተቻለ ፍጥነት በብድር የሠጡትን ገንዘብ በመሰብሰብ እንደገና መዋዕለ ንዋዩን ለኢንቨስትመንት ስራ እንዲውል በማድረግ በአገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ አዎንታዊ ሚና መጫወት ነው፡፡ ስለሆነም ባንኮች በአዋጁ የተሠጣቸውን ሥልጣን በመተው ወይም እንቅስቃሴውን ጀምረው እያለም ቢሆን በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርቱ ተቀባይነት የለውም ወይም በቅድሚያ የተጀመረው እንቅስቃሴ ሊያልቅ ይገባል የሚባልበት ሕጋዊ መሰረት ያለው ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2/ሐ) ድንጋጌም በአንድ ፍርድ ቤት የቀረበ ክስ በሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ፍርድ ቤት እየታየ ከሆነ የሚከለክል እንጂ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ላለው አይነት ክርክር አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች በአዋጁ በተሠጠው ሥልጣን መሰረት እንቀስቃሴን ቀጥሎ በፍርድ ቤት ክስ ከመሰረተ በኋላ መያዣ ንብረቶችን ለመሸጥ እንቅቃሴ እያደረገ በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርት ወይም የመያዣ ንብረቶችን ክሱ እየቀጠለ ባለበት ሁኔታ መሸጡ ቢረጋገጥ ሊኖረው የሚችለው ውጤት የሚቀር እዳ መኖሩንና አለመኖሩን አረጋግጦ ክስ እንዲቀጥል ከማድረግ ወጪ ክሱን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም፡፡ ንብረቶቹ የሚሸጡበት ዋጋ በአፈጻጸም ጊዜ የሂሳብ መተሳሰብ ተሰርቶበት ሊቀናነስ የሚችል ከመሆኑ ውጪ የአመልካችን በፍ/ቤት ክስ ከመቀጠል የሚያግደው አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ባንክ ሊከተለው የሚገባው መንገድ አንድ ብቻ ነው ተብሎ ባልተደነገገበት ሁኔታ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2/ሐ) ድንጋጌን ያስቦታው በመጥቀስ በአመልካች ባንክ የተፈፀመ ድርጊት የተጠሪን የሂሳብ እንተሳሰብ ጥያቄ በአፈፃፀም ከማንሳት የማይከለክልባቸው ሆኖ እያለ የአመልካችን ክስ ማቋረጡ ሕጋዊ ባለመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ከአመልካች ባንክ የወሰዱት የገንዘብ ብድር አለመከፈሉን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት በመያዣ የተያዙ ንብረቶች በሓራጅ መሸጣቸውን በመግለፅ በመሆኑና ይህ ደግሞ በኃላፊነታቸው መጠን ካልሆነ በሌለው ላይ የተለየ ውጤት ሊያስከትል የማይችል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሠጥበት ጉዳዩን እንደገና መመለሱ የፍትሃ ብሔር ህግ ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሰረታዊ ዓላማ ክርክሮች በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ እልባት እንዲያገኙ ማስቻል ከመሆኑ አንፃር ሲታይ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊያን ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58998 ታህሳስ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64410 የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ሚያዝያ 05 ቀን 1987 ዓ.ም በተፈረመ የብድር ውል ከአመልካች ለወሰዱት ገንዘብ የከፈሉት ማንኛውም ገንዘብ እና የመያዣ ንብረቶች ሽያጭ ዋጋን በአፈፃፀም ወቅት ከአመልካች ጋር የመተሳሰብ መብታቸው የተጠበቀ ሆኖ በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትን ብር 396,904.52(ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) ወለድን በስምምነታቸው መሰረት ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ፣ እንዲሁም የመድን አረቦኑን ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡

3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 44720

ታህሳስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሃይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ጋምቤላ ሪጅን -

ነ/ፈጅ ነብዩ ሰለሞን ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ነብዩ ፈረደ - ቀረቡ

2. አቶ ጌታሁን ታሪኩ - አልቀረቡም

**ፍ ር ድ**

ፍርድ በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች ያለአግባብ የስራ ውላቸው የተቋረጠባቸው በመሆኑ ወደስራ እንዲመለሱ ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ለክስ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች ለስልክ ተጠቃሚዎች ደረሰኝ ሳይቆርጡ ገንዘብ እየሰበሰቡ ለራሳቸው ጥቅም ስላዋሉና ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው ስላመኑ ከስራ መሰናበታቸው አግባብ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የጋምቤላ ከተማና ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤትም ተጠሪዎች አጥፍተዋል ስለተባለው ገንዘብ ቃል መቀበል ያለበት ፖሊስ ነው፣ ከጥፋታቸው እንዲታረሙ ሆነ ውሉ ለመቋረጡ ማስጠንቀቂያ ያልተሰጣቸው በመሆኑ፣ አጥፍተዋል ቢባል እንኳን ደረጃውን ያልጠበቀ ቅጣት በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት ተጠሪዎች ወደ ስራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የጋምቤላ ከተማና ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔውን አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪዎች ክስ ሲመሰርቱ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው የሚሉት አመልካች ስራ መስራት ከፈለጋችሁ አጥፍተናል ብላችሁ ፈርሙ በማለት ስላስገደዳቸው ጥፋተኛ ነን ብለው ከመፈረም ውጪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ድርጊቱን ሳይፈፅሙ ከስራ መሰናበታቸውን በመግለፅ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከስልክ ተጠቃሚዎች ደረሰኝ ሳይቆርጡ ገንዘብ እየሰበሰቡ ለግል ጥቅም አውለናል ብለው መፈረማቸውን በክሳቸው ሳይም ማመናቸውን ተረድተናል፡፡ ክርክራቸው ተገደን ነው የፈረምነው የሚል በመሆኑ መገደዳቸውን የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስረጃ እንደሌለ ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ መገንዘብ ችለናል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ወደሚለው መደምደሚያ የደረሱት ተጠሪዎች ተገደው መፈረማቸውን በማረጋገጥ ሳይሆን በሌሎች ምክንያቶች ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ የሰጡትን ምክንያቶች ቀጥለን የምንመለከታቸው ቢሆንም ተጠሪዎች ተገደው ስለመፈረማቸው እንደክስ አቀራረባቸው ሳያስረዱ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ወደሚለው መደምደሚያ መደረሱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪዎች የስራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ለማለት የሰጡት አንደኛው ምክንያት የተጠሪዎችን ቃል መቀበል ያለበት ፖሊስ እንጂ የድርጅቱ ኮሚቴ አይደለም በሚል ነው፡፡ ነገር ግን አመልካች የድርጅቱ ገንዘብ በመባከኑ ጉዳዩን አስተዳደራዊ በሆነ መንገድ የማጣራት መብት አለው፡፡ ተጠሪዎችም ድርጊቱን መፈፀማቸውን አምነው የፈረሙት በዚሁ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም በድርጅቱ በኩል የተደረገው ወንጀልን የመመርመር ጉዳይ ስላልሆነ ተጠሪዎች ቃላቸውን መስጠት ያለባቸው ለፖሊስ ነበር በሚል ምክንያት ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው መባሉ ተገቢ አልነበረም፡፡ ተጠሪዎች በራሳቸው ፈቃድ ድርጊቱን መፈፀማቸውን እስካረጋገጡ ደግሞ የራስን ወይም የሌላን ሰው ብልፅግና በመሻት በማንኛውም የአሰሪ ንብረት ወይም ገንዘብ አለአግባብ መጠቀም ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት በቂ ምክንያት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27(1)(መ) ስር ስለተመለከተ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ መሰናበታቸው አዋጁን መሰረት ያደረገ እንጂ ህገ-ወጥ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ሌላው የስር ፍ/ቤቶች ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት ተጠሪዎች ከስራ ከመሰናበታቸው በፊት ሌሎች የዲሲፕሊን እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባ ነበር የሚለውን ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ድርጊቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት መሆኑ በአዋጁ ላይ የተመለከተ ሲሆን ከዚህ በተቃራኒው ለዚህ ጥፋት ከስራ ስንብት ባሻገር የተለያዩ የዲሲፕሊን ቅጣቶች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ባለደንብ ስለመካተቱ ለፍ/ቤቱ የቀረበለት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ቅጣቱ ደረጃውን ያልጠበቀ ነው በሚል ምክንያት ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈፀሙ መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡

## ው ሳ ኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

1. የጋምቤላ ከተማና ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1060/99 መስከረም 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የጋምቤላ ከተማና ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት 00934 መጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሸሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት በህጉ መሰረት ስለሆነ ወደ ስራ ሲመለሱ አይገባም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መዝገብ ቁጥር 45882

ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡ መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ወንዱ ለማ ቀረቡ

ተጠሪ፡ 1. ወ/ሮ እጅጋየሁ አራምዴ ጠበቃ ብስራት ወ/መስቀል

2. ጌታቸው ተ/አረጋይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ ጉዳይ ከጉምሩክ ቀረጥ አከፋፈል ጋር የተያያዘ ሲሆን አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ የተለያዩ ኤሌትሮኒክስ ዕቃዎችን በሕጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ አስገብተው በወኪል ደንበኛቸው 2ኛ ተከሣሽ አማካይነት ዲክለራሲዮን በመሙላት ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ከሚያስፈልጉ ሠነዶች ጋር በማቅረብ የዕቃዎቹ ዝርዝር ዋጋቸው በዳታ ቤዝ ስፈልግ 23 የሚሆኑት ዕቃዎች ዋጋቸው ባለመገኘቱ ትክክለኛ ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት እስከሚላክልን ድረስ ዕቃው እንዳይቆይ ዋጋው በፕሮፖርሽን ተሰልቶ ብር 285,259.85 ከፍለው ንብረቱን ተረክበው ወስደዋል፡፡

ሆኖም የእነዚህ 23 ዕቃዎች ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት ተገልጾልን በዚሁ መሠረት ቀረጥና ታክስ ሲሰራ መክፈል የነበረበት ብር 47,638.34 ሳይከፈል የቀረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ቀረጥና ታክስ በማንኛውም ምክንያት ከዋጋቸው በታች የተከፈለ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት ከሆነ ያልተከፈለውን ቀሪ ቀረጥ ወይም ታክስ የማስከፈል ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 60/89 በአንቀጽ 57/1/ መሠረት ለከሣሽ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተከሣሾች በቀሪነት የሚፈለገውን ክሰ የቀረበበትን ብር 47,638.34 ከነወለድ እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው በማለት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

1ኛ ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ ተከሣሽ አሟልቶ ማቅረብ የሚገባውን ሠነዶች በሙሉ ለከሣሽ አቅርቦ ከሣሽም ሂሳቡን አሰልቶ የሸቀጡን ዋጋ ትክክለኛነት አረጋግጦ ቀረጡን የተቀበለ ስለሆነ በቀረጥ ሰብሳቢው ታምኖበት ቀረጥ ተከፍሉ ዕቃው ከወጣ በኀላ ቀሪ ሂሳብ ስመጠየቅ ከሣሽ መብት የለውም፡፡ ከሣሽ በክሱ ኘሮፖርሽን ማለት ምን ማለት እንደሆነ በምን ሂሳብ ስሌት እንደተሳካ እና የዕቃዎቹን ዋጋ ግኝት ምንጩን በመጥቀስ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48 መሠረት ወደ አገር ስለሚገባ ዕቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዝርዝር አያስረዳም፡፡ ስለሆነም ከሣሽ በክሱ በሕጉ መሠረት እንዴት ተመርምሮ ቀሪ ሂሳብ እንደተገኘ በአዋጅ መሠረት ያሳስረዳ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተከሣሽም የቀረበልኝ ዶክመንት ትክክል መሆኑን አረጋግጪ ለከሣሽ መ/ቤት በማቅረብ በየደረጃው ያሉ የጉምሩክ ሠራተኞች አይተው የዋጋ ማስተካከያ ካደረጉ በኃላ የቀረጡን ትክክለኛነት አምነውበት በፊርማቸው ካረጋገጡ በኃላ ክፍያው የተፈጸመ ስለሆነ ክሱ ያሳአግባብ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከሣሽ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ ጥያቄው እንዴት እንደተገኘ እንዲያስረዳ በታዘዘው መሠረት የከሣሽ መ/ቤት የታሪፍና ትመና መምሪያ ክፍል ሠራተኛ ቀርበው ሲያስረዱ 1ኛ ተከሣሽ ያስገቡት ዕቃ የዋጋ ስጋት ካለባቸው አገር የመጡ በመሆኑ በጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 3/1996 አንቀጽ 8 ከተራ ቁጥር 1-3 በተመለከተው መሠረት ቀረጡ በኘሮፖሬሽን የተሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ የተባለውን መመሪያ አስቀርቦ እንደተመለከተው መመሪያው የወጣው ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ስሌሳ ወገን በሚተሳለፋበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ ስለሚታሰብበት ሁኔታ ሲሆን የመመሪያው አንቀጽ 8 ና ቀረጥ በኘሮፖርሽን እንደሚሳክ የማይደነግግ በመሆኑ የካሽ ክርክርም ሆነ የምስክርነት ቃሉ ተቀባይነት የለውም ካለ በኃላ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48/1/ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ለዕቃው መግዣ፣ዕቃውን እስከ ኢትዮጰያ የመጀመሪያ የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ እንደዚሁም ለመድን ዋስትና አረቦን የወጣው ወጭ ድምር እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን እነዚህ በአስመጪው በኩል የሚቀርቡት ሠነዶች ተቀባይነት የሳቸውም ተብሉ በጉምሩክ ባለሥልጣን ከተወሰነ ቀረጡ ሲሳካ የሚገባው በአንቀጽ 48/3/ እስከ 10/ ድረስ በተመለከተው አኳኃን መሆን እንዳለበት ተመልክቶአል፡፡ ሆኖም 1ኛ ተከሣሽ ከውጭ አገር ያስገባው ዕቃ ዋጋ ተቀባይነት የለውም፡፡ ተብሉ ቀሪ ቀረጥ እንዲከፍል የተጠየቀበት አግባብ በአንቀጽ 48 ላይ በዝርዝር በተደነገገው መሠረት ስለመሆኑ የባለሙያ ማስረጃ በማቅረብ ከሣሽ ያሳስረዱ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

https://chilot.me
https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram

ከሣሽ በውሣኔው ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪዎች ተጨማሪ ቀረጡን ሊከፍሉ አይገባም ተብሉ ውሣኔ መሰጠቱ ከሕጉ አኳያ ተገቢነቱ ተመርምሮ ሊወሰን እንደሚገባው በመታመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሉ የተመለከተው ሲሆን የአመልካች የቀሪ የቀረጥ ክፍያ ጥያቄ አግባብነት ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ወደ አገር የሚገባ ዕቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነና እንዴት እንደሚሰራ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48 ሥር ተዘርዝሯል፡፡ በሌላ በኩልም ወደ ሃገር በገባ ወይም ከሀገር በወጣ ዕቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ባለሥልጣኑ የዕቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥ ማስከፈል እንደሚችል በአንቀጽ 57/1/ ላይ ሥልጣን ተሠጥቶታል፡፡

አመልካች በቀሪነት የሚፈለግ የቀረጥ ክፍያ ስላለ ተጠሪዎች ይህንኑ ቀሪ ክፍያ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ክሱ የተመሠረተው ተጠሪዎች ያስገቡት ዕቃ ኢንቮይሳቸው ዋጋው በመ/ቤቱ ከሚገኘው ዳታ ቤዛችን ጋር ሲወዳደር አንሶ በመገኘቱ ውድቅ ተደርጎ በዳታ ቤዙ መሠረት ዋጋ ሲፈለግ የተወሰኑት ዕቃዎች ዋጋቸው ስላልተገኘ በተገኙትና ባልተገኙት መካከል ያለውን ልዩነት የመ/ቤቱ መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በኘሮፖርሽን ተሰርቶ ቀረጡን እንዲከፍሉ ከተደረገ በኃላ ዝራዝራቸው በዳታ ቤዝ ያልተገኙ ዕቃዎች ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት ሲላክልን በልዩነት የሚፈለግ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ መኖሩን አረጋግጠናል በሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም አመልካች በኘሮስፖርሽን ቀረጥ ለማስከፈል የሚያሰችል የሕግ ድጋፍ የለውም ተገቢ ሰነዶችንም አቅርበን ቀረጡ የተከፈለ ስለሆነ ቀሪ ክፍያ አለ ተብሎ የቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

ሆኖም ግን የአመልካች መ/ቤት የዋጋ ዝርዝራቸውን በዳታ ቤዝ በተገኘውና ባልተገኘው መካከል ልዩነቱን በኘሮስፖርሽን ስሌት መሠረት እንደሚያስከፍል ለተጠሪዎች ሲገልጽ ተጠሪዎች ተቀብለው ቀረጡን ከፍለዋል፡፡ አመልካች ቀረጡን የማስከፍላችሁ በኘሮስፖሬሽን ስሌት ነው ካለ በሌላ አገላለጽ የተጠሪዎችን ኢንቮይስ ውድቅ ማደረጉን የሚያመለክት ስለሆነ በአዋጁ አንቀጽ 53/1/ በተቀመጠው አግባብ መሠረት ተቃውሚቸውን አስመዝግበው የጉምሩክ ሹሙ በሚወሰነው መሠረት ቀረጥ መክፈል ይገባቸው የነበረ ሲሆን በዚህ መልኩ ተቃውሞ ካላደረጉ በኘሮፖርሽን ስሌት የተጠየቀውን የቀሪ ቀረጥ ክፍያ ጥያቄ እንደተቀበሉት የሚቆጠር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ስለሆነም አመልካች ክሰ የመሠረተበትን የቀረጥ ክፍያ ጥያቄ በተጠሪዎች በኩል በሕጉ አንቀጽ 53 አግባብ ተቃውሞ ያልቀረበበት እንደመሆኑ መጠን የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች ተቃውሞ ባላቀረቡበት ሁኔታ አመልካች በፕሮፖርሽን ቀረጥ ለማስከፈል የሚችልበትን አግባብ አላስረዳም በማለት የክፍያ ጥያቄውን ሳይቀበለው መቅረቱ ከአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 57 እና 53/1/ አኳያ ተገቢነት የሌለውና የሕግ ስህተት የተጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሣኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 68030 ሕዳር 19 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 76136 መጋቢት 2 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች አመልካች ክሰ ያቀረበበትን ብር 47,638.24/አርባ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ሠላሳ ስምንት ብር ከሀያ አራት / ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሠብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 45886

ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች:-** አቶ አብርሃም ሀብቴ - ከጠበቃ ኃ/ማርያም ካሣ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ:-** አቶ አስፋው አበበ - ከጠበቃ ደምሰው ዘገዬ ጋር ቀረቡ

መዘገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመኪና ሽያጭ ውሉን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሕዳር 21 ቀን 1999 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች የካቲት 21 ቀን 1998 ዓ.ም በተጻፈ ውል የሰሌዳ ቁጥር 3-11580 አ.አ የሆነው መኪና ግማሽ የተጠሪ ሆኖ ግማሹን የራሳቸውን ድርሻ በብር 63,000.00(ስድሳ ሦስት ሺህ) ለተጠሪ ሸጠውላቸው ከሽያጩ ገንዘብ ብር በእለቱ ብር 6000.00(ስድስት ሺህ) መቀበላቸውን፣ ቀሪውን ገንዘብ በተመለከተም የሚከፈልበትን መንገድና ጊዜ ገልፀው መስማማታቸውን፣ ሊብሬውንና መኪናውን ሻጭ ለገዥ ማስረከባቸውን፣ በስምምነቱ መሰረትም ገዢ ለሻጭ ቀሪውን ገንዘብ መክፈል ጀምረው ብር 6120(ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ብር) እንደከፈሉ፣ ሆኖም ሻጭ መኪናን ቦሎ ሳስደርግልህ በማለት ሊብሬውን ሐምሌ 23 ቀን 1998 ዓ.ም መውሰዳቸውን፣ መኪናውን ደግሞ የግል ስራቸውን ለመስራት ፈልገው ገዢ እንዲተባበራቸው ጠይቀው ነሐሴ 07 ቀን 1998 ዓ.ም ከገዢ ተረክበው ከወሰዱ በኋላ ሊብሬውንም ሆነ መኪናውን ለገዢ ሳይመልሱ መቅረታቸውን ገልፀው መኪናው በባለሙያ ታይቶ ሻጭ እንዲያስረክባቸው፣ መኪናውን በመውሰዳቸው የተቋረጠውን ጥቅም ብር 53,000.00(አምሳ ሦስት ሺህ) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነታቸው ቀርበው የውሉን ግዴታ ያልፈፀሙት ገዢ በመሆናቸው መኪናውን የሚያስረክቡበት ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ዘርዝረው የተጠሪ ክስ ውድቅ ሲሆን ይገባል በማለት ከመከራከራቸውን በተጨማሪ ገዢ መኪናውን ከተረከቡበት ከየካቲት 21 ቀን

1998 ጀምሮ መኪናውን ለሻጭ እስከመለሱበት እስከ ነሐሴ 07 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ ገዢ መኪናውን የተጠቀሙበትን ብር 75,000(ሰባ አምስት ሺህ) በውሉ መሰረት ካልተከፈለው ብር 40,880.00(አርባ ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ብር) ጋር ተጠሪ እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለአመልካች የስር የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሻጭን ለገዢ ክስ ኃላፊ በማድረግ የሠ.ቁ 3-11580 አ.አ የሆነውን መኪናው በባለሙያ ከታዬ በኋላ ባለበት ሁኔታ ከእነሊብሬ እንዲያስረክቡ፣ ገዢም ለሻጭ ያልከፈሉት ገንዘብ መኖሩን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከተቋረጠው የገዢ ጥቅም ጋር በማቻቻል ከአቀናነሰ በኋላ በገዢ ላይ ብር 5,880.00(አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ብር) በሻጭ ስለሚፈለግ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የመኪናውን ገቢ በተመለከተ የሠጠውን ውሳኔ በመሻር ገዢ ብር 50,880.00(ሃምሳ ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ብር) ለሻጭ እንዲከፍሉ፣ ሻጭ ደግሞ ለገዢ መኪናውንና ሊብሬውን እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል መኪናው የጋራ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ እና በወንጀል ችሎትም መኪናው የጋራ አለመሆኑ የተረጋገጠበት ማስረጃ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብ ተጠይቆ ታልፎ መኪናውን አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ መወሰኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 1733 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚፃረር በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም አመልካች መኪናውን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር መስከረም 19 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ የካቲት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረጉት የመኪና ድርሻ ሽያጭ ውል አመልካች በመኪናው ላይ ያላቸውን ድርሻ ለተጠሪ በብር 63,000.00 መሸጣቸውን፣ በወቅቱም ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ ተጠሪ ብር 6000.00 መክፈላቸውን፣ ብር 1000.00 በመጋቢት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ለመክፈልና ቀሪውን የሽያጭ ገንዘብ ብር 47,000.00 ተጠሪ በአመልካች ፀሐፊነት በሚሰበሰበው ዕቁብ ውስጥ በየሳመንቱ ብር 1020.00 እየከፈሉ ለመጨረስ ተጠሪ ግዴታ መግባታቸውን እና በውሉም ወቅት መኪናውን ከእነሊብሬ አመልካች የተረከቡ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች በዚህ የክርክር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩት በውሉ መሰረት አከራካሪው መኪና የጋራ ነው በሚል መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩ ውልን መሰረት ያደረገ እንደመሆኑ መጠን ከውል ሰነዱ ይዘት አንፃር መመርመር ያለበት መሆኑንም ተረድተናል፡፡

በመሠረቱ ውለታዎች ግልፅ ሆነው ሲገኙ ትርጉም የማያስፈልግ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1733 ድንጋጌ በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን፣ ግልፅ ባልሆነ ጊዜ ብቻ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ከፍ/ሕ/ቁጥር 1732፣ 1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሠረት መተርጎም የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች በፍ/ሕ/ቁጥር 1733፣ 1734 እና 1736 ሲሆኑ ተዋዋዮች ውላቸውን ከመዋዋላቸው አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበትን ሁኔታዎች፣ የፈፀሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሀሳባቸው ምን እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሉችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብ ያለውን ትርጉም መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ በ21/06/1998 ዓ.ም አደረግን ባሉት የሽያጭ ውል አመልካች በአከራካሪው መኪና ላይ ያላቸውን ግማሽ ድርሻ መሸጣቸውን ከመስማማታቸውም በተጨማሪ የመኪናውን ሊብሬ እና መኪናውን ለተጠሪ ማስረከባቸው በግልፅ ሠፍሯል፡፡ አመልካች መኪናው የጋራ ነው በማለት የሚከራከሩት በውሉ ላይ፤ *"ባለቤትነት መታወቂያውን ሊብሬ በሁለታችን ስምምነት እዳው ከአለቀ በኋላ በአንደኛችን ስም ለማዛወርና ለማስመዝገብ ተስማምቼአለሁ"* የሚል ዐረፍተ ነገር ሠፍሯል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲቀርብባቸውም ሆነ የተከሳሽነት ክስ በተጠሪ ላይ ሲመሰርቱ መኪናውን ከተጠሪ ጋር የጋራ ለማድረግ ስለመስማማታቸው ገልፀው የተከራከሩ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ በመሆኑም አመልካች መኪናው የጋራ ነው በሚል የሚከራከሩት በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ ክርክር በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ከላይ የተጠቀሰው የውሉ ዐረፍተ ነገር ከሌሎች በውሉ ውስጥ ከተጠቀሱት ስምምነቶችና

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

በግራ ቀኙ ከተፈፀሙት ድርጊቶች አንፃር ሲመረመር አመልካች በመኪናው ላይ ያሳቸውን ድርሻ ለተጠሪ ሽጠዋል ከሚባሉ በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ የካቲት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ያደረጉትን የሽያጭ ውል ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ጋር ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38345 ሚያዚያ 20 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 67810 መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም ተሻሽሎ የተወሰነው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 45889

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች:- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን

ነገረ ፈጅ ቢንያም እስጢፋኖስ ቀረበ

ተጠሪ:- ሳሙኤል ቁልቦ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል::

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አስቀድሞ በተሰጠኝ የደረጃ እድገት መሠረት ይከፈለኝ የነበረው ተጨማሪ ደመወዝ ያለአግባብ ስለተቋረጠብኝ ይኸው ሕገ ወጥ ድርጊት ተወግዶ ጭማሪው ደመወዝ እንዲከፈለኝ ይደረግልኝ በማለት ተጠሪ በመሠረተው ክስ መነሻነት የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው:: ክርክሩ የተጀመረው በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ከአመልካች የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ጭማሪው በእድገት ሳይሆን በስህተት ተሰጥቶ የነበረ ስመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጡን በመግለጽ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎአል:: በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልሳዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል:: በመቀጠልም ፍ/ቤቱ አመልካች እንዴ የሰጠውን ውሳኔ በራሱ የሚሽርበት አግባብ የለም የሚል ምክንያት በመስጠት በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል:: የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ሳይ ነው::

አመልካች ግንቦት 13 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበበተ ውሳኔ ሳይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቀርቦአል:: በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል:: በመቀጠልም ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል::

የተጠሪ የክስ ምክንያት በተሰጠኝ የደረጃ እድገት መሠረት ሲከፈለኝ የነበረው የደመወዝ ጭማሪ ያለአግባብ ተቋርጦብኛል የሚል ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ ተጠሪ ቀደም ሲል ሲሠራበት ከነበረው የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅነት ተመሣሣይ ደረጃ ወደሆነው የሪጅን ምክትል ሥራ አስኪያጅነት ነው የተዛወረው፡፡ ሁለቱም ሥራዎች እኩል ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ ዝውውሩ ሲደረግ የደመወዝ ለውጥ ማዘዣው በስህተት በመሠራቱ ነው ችግሩ የተፈጠረው፡፡ የተሠራው ስህተት እንደታወቀም የእርምት እርምጃ ተወስዶአል በማለት እንደተከራከረ ከመዝገቡ ለማየት ችለናል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎትም አመልካች ያቀረበው የፍሬ ነገር ክርክር ትክክል ሆኖ በማግኘቱ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው የደመወዝና የደረጃ እድገት የተነሳው (የተሰጠው) በአግባቡ ነው እሚል መደምደሚያ ደረሶአል፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ የሻረው በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጠው የተለየ ነገር አግኝቶ ሳይሆን፣ አመልካች እራሱ የሰጠውን ውሳኔ ያለምክንያት መልስ መለወጥ የሚችልበት አግባብ የለም፣ "እንደ ፍ/ቤት እራሱ የወሰነውን ውሳኔ መከለስ /Review of judgment/ ማድረግ የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ ውሳኔው የሚመረመረው ለመመርመር ስልጣን ባለው በሌላ አካል በjudicial review ነው፡፡" የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

እንደምንመለከተው የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ቀድሞ ከነበረው የተለየ ደመወዝና ጥቅም ወደሚያስገኝ ከፍያለ ደረጃ ወዳለው ቦታ አልተዛወረም እሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ክሱን ውድቅ ያደረገ ሲሆን፣ ተጠሪ ግን አንዴ የተሰጠኝ ደመወዝ ልነጠቅ አይገባም ከማለት አልፎ በእርግጥም በኋላ የተመደበበት ቦታ ከቀድሞው የተለየ እና ከፍ ያለ ደመወዝ የሚያስገኝ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ይግባኙን የሰማው ጠ/ፍ/ቤትም አመልካች ቀደም ሲል በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት ሲከፈል የነበረውን ደመወዝ በተገቢው የእድገት አሰጣጥ መሠረት የተገኘ አይደለም በማለት የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይችላል ወይስ አይችልም? በሚለው ነጥብ ላይ በመወሰን ውሳኔ ከመስጠት አልፎ በከፍተኛው ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር እውነት አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ የሚችል ማስረጃ አግኝቻለሁ አላለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰበር ችሎት ሊወሰን የሚገባው ጭብጥ አመልካች የቀድሞ ውሳኔህን መለወጥ ወይም ማረም አትችልም የሚባልበት የሕግ አግባብ አለ ወይ? የሚለው ነው፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ነው፡፡ አመልካች በአሠሪነቱ ተጠሪንም ሆነ ሌሎች ሠራተኞቹ የሚያስተዳድረው፣ የደረጃ እድገት አሰጣጥም ሆነ የደመወዝ አከፋፈል ወይም አመዳደብ የሚወሰነው ባለው አሠራረ እና ድርጅታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

መዋቅሩ መሠረት እንደሆነ ይገመታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በኋላ የተመደበበት የሥራ ቦታ ቀድሞ ከነበረበት የሥራ ቦታ ተመሣሣይ በመሆኑ ተጨማሪ ደመወዝ የሚያገኝበት አግባብ እንደሌለ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ የፍሬ ነገር መሠረት ስለሌለው ስህተት ነው ማለት ነው፡፡ ተጠሪ ተጨማሪ ደመወዝ እንዲከፈለው የሚያዘው ደብዳቤም የተጻጻፈ በተሳሳተ ውሳኔ ላይ በመመስረት በመሆኑ አመልካች ስህተቱን በማረም ተለዋጭ ውሳኔ ከመስጠት የሚያግደው የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በሥራው መሪነቱ (በአሠሪነቱ) ትክክል ነው ብሎ በሚያምነው መሠረት የመወሰን ሥልጣን ያለው እንደመሆኑ ስህተት መስሎ የታየው የራሱንም ውሳኔ ማረም ያለበት እራሱ እንጂ የተሳሳተ ውሳኔ ሰጥቻለሁና አርምልኝ ብሎ ለሌላ አካል አቤቱታ የሚያቀርብበት የህግ አግባብ የለም፡፡ አግባብ የሚሆነው በውሳኔው ተጎድቻለሁ የሚለው ወገን (ሠራተኛ) የውሳኔ ሕጋዊነት ይታይልኝ (ይመርመርልኝ) በማለት ሥልጣን ሳለው አካል አቤቱታ ቢያቀርብ ነው፡፡ ተጠሪም ያደረገው ይኸው ሲሆን፣ አመልካች ውሳኔውን ያረመው በአግባቡ ሆኖ በመገኘቱ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን በሰማው ፍ/ቤት ተወስኖአል፡፡ በመሆኑም የጠ/ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው የJudicial Review መርህ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ውሳኔው በሕግ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 24637 የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመ.ቁ 5223 ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡ በዚህ መሠረትም አመልካች የቀድሞውን ውሳኔ ያረመው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 45982

ታህሳስ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ስንቅነሽ ሳቀው የተማሪ ያብስራ አድማሱ ሞግዚት - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጋሻው እንግዳ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የውርስ ማጣራትን የሚመለከት ሲሆን በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውርስ አጣሪ ተቋቁሞ የሟች አቶ አድማሱ እንግዳ የውርስ ንብረት ተጣርቷል፡፡ የውርስ ማጣራት ሪፖርቱም ለፍርድ ቤት ቀርቦ በአብላጫ ድምጽ በቀረበው ሪፖርት ሳይ አመልካችና ተጠሪ ተቃውሞ እንደሌላቸው ፍ/ቤቱ መዝግቦ ሪፖርቱ ለሕግም ሆነ ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በማለት ተቀብሎ አፅድቆታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የቀበሌ ቤቱን በተመለከተ በቤቱ ለሚኖሩ ሰዎችና በነዋሪነት ቅጽ ላይ ለተመዘገቡ ሰዎች የሚገባ ነው በማለት ውርስ አጣሪዎች መወሰናቸው ከቀረበው ማስረጃ አንጻር ተገቢ ነው፡፡ ዕዳው በተመለከተ ሟች ከወ/ት ሚሚ ተሾመ ብር 20600 የወሰዱት በብድር ሳይሆን በአደራ ስለመሆኑ በሠነድና በሰው ምስክሮች የተረጋገጠ ስለሆነ ሟች በአደራ የተቀበሉት ገንዘብ የውርሱ አካል ሳይሆን እንደ ዕዳ ተወስዶ እንዲመለስ በውርስ አጣሪው መጣራቱ ተገቢ ነው ብሎ መ/ሰጭን ሳይጠራ ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን የቅሬታው ነጥብም በባንክ ያለው ገንዘብ በሟች ስም ያለ ሆኖ ሳለ ምስክሮች የሟች ንብርት አይደለም በአደራ የተቀመጠ ነው

በማለት የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሠረት በማድረግ የውርስ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት የሥር ፍ/ቤቶች ተቀብለው ማፅደቃቸው ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ ይህንኑ ነጥብ አጣርቶ ለመወሰን እንዲቻል አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙንም በቃል አከራክሯል፡፡

በበኩላችንም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ የሟች አቶ አድማሱ እንግዳ የውርስ ንብረት እንዲጣራ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት የውርስ አጣሪ ተቋቁሞ ውርሱን አጣርቶ በድምጽ ብልጫ የደረሰበትን ሪፖርት ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ጠይቆ ተቃውሞ እንደሌላቸው መግለጻቸውን የፍ/ቤቱ የውሳኔ ቅጂ ያረጋግጣል፡፡

ፍ/ቤቱ ሪፖርቱን ተቀብሎ በማፅደቁ አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ሆኖም አመልካች በሪፖርቱ ላይ ቅሬታ ካላቸው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን አስተያየት ሲጠይቅ ያላቸውን ቅሬታ ማስመዝገብ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች በሪፖርቱ ላይ ቅሬታ ያነሱት ከላይ እንደተጠቀሰው በሟች ስም በባንክ የተቀመጠው ገንዘብ የውርሱ አካል መሆን ሲገባው የአደራ ገንዘብ ነው ተብሎ የቀረበው ሪፖርት ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

ይሁንና በባንክ በሟች ስም የተቀመጠው ገንዘብ የሟች የግል ንብረት ሳይሆን ሟች በአደራ እንዲያስቀምጡ ተሰጥቷቸው የነበረ ገንዘብ ስለመሆኑ ውርስ አጣሪው በሰነድና በሰው ምስክር ያረጋገጠው ስለመሆኑ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ ተመልክቷል፡፡ በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ የሟች የግል ገንዘብ ነው ወይንስ በአደራ የተቀመጠ የሌላ ሰው ገንዘብ ነው የሚለው የሚጣራው በማስረጃ እንጂ ሕግን በመተርጎም አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ደግሞ በዚህ ረገድ የቀረበውን ማስረጃ ተመልክተው የሟች ንብረት አለመሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ይህንን በማስረጃ የተረጋገጠን ፍሬ ነገር ይህ ችሎት ባለበት ሁኔታ ከሚቀበለው በስተቀር ማስረጃውን ተመልሶ ለመመርመር የሚችልበት ሥርዓት የለም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ተቀብለው ማፅደቃቸው የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት አልተቻለም፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 53066 በ1-7-2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 78538 በ21/8/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ አጽንተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ. 46117

ሐምሌ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- ሐጐስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ

አመልካች:- ደበበ ግዛው - ጠበቃ ታምራት ብዙነህ ቀረበ

ተጠሪዎች:- 1. ሻለቃ ደሜ ማሞ
2. አማረ ደሜ
} ጠበቃ ማርቆስ ወ/ሰንበት ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል::

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.73 መሠረት የተዘጋው መዝገብ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ይታዘዝልኝ በሚል የቀረበውን አቤቱታ መነሻ ያደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው:: ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው:: ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ክርክሩን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ በያዘበት ዕለት ተከሣሾች ቀርበው ከሣሽ ሳይቀርብ በመቅረ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.73 መሠረት ተዘግቶአል:: በሌላ በኩል ደግሞ የአመልካች ጠበቃ ቀርቦ መዝገቡ እንዲከፈትለት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ሃሳብ ከሰማ በኋላ፣ የአመልካች ጠበቃ ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ አድርጐአል:: ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አፅንቶአል:: የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው::

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል:: ክርክሩ የተሰማው አመልካች ለሥር ፍ/ቤት ያቀረበው የመዝገብ ይከፈትልኝ አቤቱታ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከመመርመር አንፃር ነው:: በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኙ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል::

አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው በጠበቃው አማካይነት ሲሆን፣ ክርክሩን ለመስማት ቀጠሮ በተያዘበት ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ችሎት ሳይቀርብ የቀረውም ጠበቃው ነው፡፡ በዚህ ዕለት ተከሳሾች በመቅረባቸው እና ክሱን በመካዳቸው መዝገቡ በሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ መሠረት ተዘግቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጠበቃው ችሎቱ ሳይነሳ ስለመድረሱና አቤቱታውን ስለማቅረቡ የከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተመልክቶአል፡፡ ጠበቃው ዘግይቶ ሊቀርብ የቻለው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 7ኛ ፍትሐብሔር ችሎት በመ.ቁ 112423 ክርክር ስለነበረበት እንደሆነ በአቤቱታው መግለጹንም በትዕዛዙ ተመልክቶአል፡፡ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ያልተቀበለው መዝገቡን ለሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም (ክርክሩን ለመስማት የተያዘው ቀነ ቀጠሮ) ያስቀጠረው ጠበቃው እራሱ ነው፤ ይህን ቀጠሮ ለፍ/ቤቱ ሲያስይዝ የሚጋጭ አጀንዳ እንደሌለው አረጋግጦ ነው፤ የአጀንዳ መጋጨት አጋጥሞት ቢሆን እንኳ ይህን መረጃ ለከሣሽ (ለአመልካች) ወይም ለሌላ ወኪል በመግለጽ ተክቶት ሊቀርብና ተለዋጭ ቀጠሮ ሊጠይቅ የሚችልበት ወይም ቀደም ብሎ በማመልከት ተለዋጭ ቀጠሮ የሚጠይቅበት እድል ነበረው፤ ጠበቃው ሳይቀርብ የቀረው በሌላኛው ፍ/ቤት ያለውን ጉዳይ መርጦ በመሄዱ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

የሰበር ችሎቱ የአመልካችን አቤቱታ ተጠሪዎች ከሚሰጡት መልስ ጋር አገናዝቦ መመርመር የፈለገው የሥር ፍ/ቤት አቤቱታውን ሳለመቀበል የሰጣቸውን ምክንያቶች መነሻ በማድረግ ጭምር ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው አመልካች መዝገቡን ለማስከፈት በቂ ነው በማለት ያቀረበው ምክንያት የችሎት መደራረብ ነበረብኝ የሚለው ነው፡፡ በእርግጥ በሌላ ፍ/ቤት ክርክር እንደነበረበት የሚያመለክት ከፍ/ቤቱ የተጻፈለት ደብዳቤ ስለማቅረቡ የከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪዎች ለሰበር አቤቱተው ከሰጡት መልስ ማየት የቻልነው ግን አመልካች ከሚለው የተለየ በመሆኑ የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ክርክር ሳካሂድበት ነበር ያለው ቁጥር 112423 የሆውን መዝገበ ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አስቀርበን ሁኔታውን አጣርተናል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የቻልነው በመዝገቡ በሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የተያዘ ቀጠሮም ሆነ የተካሄደ ክርክር እንዳልነበረ (እንደሌለ) ነው፡፡ መዝገቡ ያረጋገጠው ሃቅ ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች ጠበቃ የሰጠው ምክንያትም ሆነ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 7ኛ ፍትሐብሔር ችሎት ጻፈው የተባለው ማስረጃ በእውነት ላይ ያልተመሠረቱ፤ ይልቁንም የተዘጋ መዝገብ እንዲከፈት ጥያቄ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ እንዲሰጥ ታስቦ የተደረጉ እንቅስቃሴዎች መሆናቸውን ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ ከዚህ የተነሣም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በራሱ ምክንያት ክርክሩም ሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ማስረጃው ባይቀበለውም፣ በአመልካቹ ጠበቃ የተደረገው ፍ/ቤቱን የማሳሳት ሙከራ ግን እንዲሁ የሚታለፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመቀጠል የተመለከትነው የአመልካች ጠበቃ ችሎቱ ከመነሳቱ በፊት ደርሶ ማመልከቱን መሠረት በማድረግ ሁኔታው ሲታይ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ባለበት ሁኔታ መተው አግባብ ይሆናል ወይ? የሚለው ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.73 መሠረት መዝገብ ከተዘጋ ከሣሹ ለመጀመሪያው ክስ ወይም ለይግባኙ መነሻ የነበረውን ነገር መሠረት በማድረግ አዲስ ክስ ለማቅረብ እንደማይችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.74(1) ተመልክቶአል፡፡ በእርግጥም ከሣሹ መዝገቡን እንደገና ለማስከፈት የሚያስችል በቂ ሆኖ የሚገመት ምክንያት ማቅረብ እስካልቻለ ድረስ ለመዝገቡ መዘጋት ኃላፊነት መውሰድ ያለበት እሱ(ከሣሹ) በመሆኑ አዲስ ክስ እንደገና የማቅረብ ዕድል መነፈጉ ተገቢ ነው፡፡ ይህ እንንግዲህ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠ መርህ ሲሆን ጉዳዮች በተናጠል ሲታዩ ደግሞ እንደየጉዳዩ የተለዩ ሁኔታ እየታዩ ውሳኔ መስጠት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀነ ቀጠሮውን ለሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ከማድረግ አልፎ በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የተነሳውን ክርክር የሚሰማበትን ሰዓት ወስኖ አላስታወቀም፡፡ ፍ/ቤቱ በችሎት የሚያስተናግደው በርካታ ጉዳዮች በመሆናቸውም የአመልካች ጠበቃ ችሎቱ ከመጠናቀቁ (ከመነሳቱ) በፊት ሲደርስ ችሎአል፡፡ በዚህን ጊዜ በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር ተስተናግዶ መዝገቡ ተዘግቶ የነበረው በአጋጣሚ ነው ከሚባል በቀር ሰዓት ተወስኖለት ስለተስተናገደ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ይህን ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከተቀመጠው የመስማት መብት ጋር አገናዝቦ መዝገቡን እንደገና መክፈት ይገባው እንደነበረ ነው በበኩላችን መገንዘብ የቻልነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 51352 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል መ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ.41910 የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ እንደገና ክርክሩን እንዲያይ ብለናል፡፡
3. አመልካች በቀድሚያ ብር 5000(አምስት ሺህ ብር) ለተጠሪዎች ኪሣራ እንዲከፍል ወስነናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://chilot.me
https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram

የሰበር መ/ቁ 46958

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. መንበረፀሃይ ታደሰ

2. ሂሩት መለሰ

3. ታፈሰ ይርጋ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

አመልካች:- የቡና ተክል ልማት ድርጅት

ተጠሪ:- አቶ ታደሰ አምቦ

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በጅማ ዞን ሊሙ ኮሳ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ በሱንጡ ቡና ተክል ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ እየሰሩ መሆኑንና አመልካች በ23/12/1997 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ወደ ጎማ ቁጥር 2 የቡና ተክል ያዛወራቸው መሆኑን ገልፀው ነገር ግን ድርጅት ውስጥ ከመቀጠራቸው በፊት የሰሩትን ቤት ባለማስረከባቸው መሸኛ ስለከለከላቸው ወደተዛወሩበት ቦታ ሄደው መስራት ስላልቻሉ ከጳጉሜ ወር 1997 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዝ ከፍሎ መሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ይህን ጉዳይ ፍ/ቤቱ ለማየት አይችልም የሚል መቃወሚያና በፍሬ ጉዳዩም ላይ የልማቱ ንብረት የሆነውን ቤት እና ንብረት ባለማስረከባቸው መከራከር አይችሉም፣ ወደ ተዛወሩበት ቦታ ሄደው ለመስራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሳልተሰራ ስራ ደሞዝ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን በብይን ከዘጋው በኋላ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመመሪያ ጉዳዩን ስለመለሰው የወረዳ ፍ/ቤቱ በድጋሚ ጉዳዩን አይቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ እንዲያስረክቡ የተጠየቁትን ቤት የገነቡት እራሳቸው መሆናቸውን፣ አንድ ሰራተኛ ወደ ሌላ ቦታ ሲቀየር ወደተቀየረበት ቦታ ሄዶ ለመስራት መሸኛ አስፈላጊ መስፈርት መሆኑን፣ አመልካች ተጠሪን በማይመለከት ጉዳይ መሸኛ ደብዳቤ መከልከሉ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ ወደተቀየሩበት ቦታ ሄደው ስራቸውን እንዲሰሩ መሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች

ስተጠሪ የአንድ አመት ደሞዝ ከፍሏቸው ወደስራ ተመልሰው አመልካች በመደባቸው ቦታ እንዲሰሩ በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ የስር ውሳኔ መሰረታዊ ህግ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው ተጠሪ በነበሩበት የልማት ድርጅት እንዲኖሩበት የተሰጣቸውን ቤት ሳያስረክቡ መሸኛ ሊሰጣቸው አይችልም፣ የወረዳ ፍ/ቤቱ ስለቤቱ እንዲያጣራ የሰየመው ኮሚቴ ያቀረበውን ሪፖርት ሳይቀበለው መቅረቱ አግባብ አይደለም፣ ተጠሪ ላልሰሩበት ጊዜ የአንድ አመት ደሞዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 54(1)ን ይቃረናል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች አከራካሪው ቤት የተጠሪ ነው ብለው የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኝ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ሰምቷል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክርና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት አመልካች ወደ አዛወራቸው ቦታ ሄደው ለመስራት የሚያስፈልጋቸውን የመሸኛ ደብዳቤ አመልካች ስለከለከላቸው ይህንኑ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው እና ያልከፈላቸውን ደሞዛቸው እንዲከፍላቸው ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ወደ ተዛወሩበት ቦታ ሄደው ለመስራት መሸኛ የሚያስፈልጋቸውና ይህንኑ ያልሰጣቸው መሆኑን ሳይክድ ነገር ግን ይህን መሸኛ ለመስጠት አመልካች በቅድሚያ ከልማት ድርጅቱ የተረከቡትን ቤት ሊያስረክቡ እንደሚገባ ገልጿል፡፡ በአመልካች በኩል የተጠሪ ቤቱን ማስረከብ የመሸኛ ደብዳቤውን ለመስጠት ቅድመ ሁኔታ አድርጎ ማስቀመጡን ከክርክሩ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን አመልካችም ሆነ ተጠሪ የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን ገልፀው ይከራከራሉ፡፡ የዚህ ቤት የባለቤትነት መብት አከራካሪ በመሆኑም ቤቱ የማነው የሚለው የባለቤትነት ጥያቄ በጭብጥነት ተይዞ መፈታት ያለበት ጉዳይ ይሆናል፡፡ በርግጥ የፍታብሔር ጉዳይ የስራ ክርክር የሚታየው በተመሳሳይ ፍ/ቤት ቢሆንም የቤት ባለቤትነትን ጥያቄ አከራክሮ ለመወሰን የስረ ነገር ሥልጣን ያለው ፍ/ብሔር ችሎት እንጂ የስራ ክርክር ጉዳዮችን ለማየት ስልጣን የተሰጠው ችሎት አይደለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበላቸው የስራ ክርክር ችሎቶች የቤት ባለቤትነት ጥያቄውን አከራክረው መወሰናቸው ከተሰጣቸው የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ውጪ በመሆኑ መሰረታዊ የሥነ - ሥርዓት ህግ ስህተት ፈፅመዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ቦታ አዛውሯቸዋል፡፡ ወደ ሌላ ቦታ ተዛውሮ ለመስራት ደግሞ የመሸኛ ደብዳቤ አስፈላጊ መሆኑን አመልካችም ያመነው ጉዳይ ቢሆንም በዚህ ችሎት በተደረገው የማጣሪያ ጥያቄ ተጠሪ ከነሐሴ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

አስመገኘታቸውን ገልጸዋል፡፡ አመልካች ደግሞ ተጠሪን ከስራ ያሰናበተ መሆኑን ገልጿል፡፡ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ቢሆን ይኸው ፍሬ ነገር መገለጹን የውሳኔው ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክርና ከይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ውሳኔ ሳይ የተረዳነው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው የስራ ውል ግንኙነት በክርክር ወቅት መቋረጡን ነው፡፡ የስራ ውላቸው የተቋረጠው ደግሞ አመልካች መዛወራቸው ሌላ ቦታ ሄደው ለመስራት የሚያስችላቸውን የመሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያቱ ተቋርጧል፡፡ ክሱ በሚቀጥልበት በማንኛውም ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡ ፍ/ቤቱ ሲገነዘብ ክሱ ሲዘጋ እስከሚገባ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 280 ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪ የስራ ውል የተቋረጠ መሆኑን እንደተገነዘቡ ክሱን ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው ተጠሪ አንድ አመት ደሞዝ ተከፍሏቸው የመሸኛ ደብዳቤ ተሰጥቷቸው ወደተዛወሩበት የስራ መደብ እንዲመለሱ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ተጠሪ ስራ ሳይሰሩ ደሞዝ ሊከፍል የማይገባው መሆኑን አንስቶ ተከራክሯል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው ተጠሪ ከነሐሴ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ሳይ ያልነበሩ መሆኑ ራሳቸው ገልጸዋል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የተጠሪ የስራ ውል የተቋረጠ በመሆኑ ደመወዝ ሊከፈላቸው የማይገባ ሲሆን ውሉ ባይቋረጥም እንኳን ለሰራተኛ ደመወዝ የሚከፈለው ለሰራው ስራ ብቻ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 54(1) ስር የተነገረ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ስራ ሳይሰሩ የአንድ ዓመት ደመወዝ እንዲከፈላቸው የተሰጠ ውሳኔ ቢሆንም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ ነው፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች ክርክር የተነሳውን ቤት የባለቤትነት ጥያቄ አከራክረው ለመወሰን የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የላቸውም፡፡ የተጠሪ የስራ ውል በክርክሩ ሂደት ስለተቋረጠ የክስ ምክንያት አብሮ የተቋረጠ በመሆኑ ተጠሪ ወደተዛወሩበት ቦታ ሄደው ስራቸውን እንዲጀምሩ የመሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው መወሰኑ እንዲሁም ተጠሪ ስራ ሳይሰሩ አንድ አመት ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ችሎቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሲሙ ኮሣ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 00764 ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 11313 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 79130 መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሸሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

2. ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያሳቸው የስራ ውል የተቋረጠ በመሆኑ ደመወዝ ተከፍሏቸው ለዝውውር የሚያስፈልጋቸው የመሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 47005

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ፈቃዱ ማናዜ - ቀረቡ

2. ወ/ት የዓለምወርቅ ሙሳቱ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሙሉ ድንቁ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የቤት ባለቤትነትን ክርክር የሚመለከት ሲሆን አመልካቾች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 ክልል ቁጥሩ 436 የሆነውን ቤት ከሳሾች ከሟች ወ/ሮ አየለች ዘውዴ በውርስ ያገኘነው ሲሆን በይዞታችን ውስጥ ከተሰሩት ቤቶች በአንደኛው ቤት ተከሳሽ ይኖራሉ፡፡ ተከሳሽ ይህንኑ ቤት ከአውራሻችን ገዝቻለሁ በማለት የውል ይፈጸምልኝ ክስ መስርተው ክሱ በይርጋ ታግዷል ተብሎ በመ.ቁጥር 01660 ውድቅ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ የከሳሾችን ቤት ይዘው የሚኖሩት ውልን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ስላልሆነ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ ቤቱን የሠራሁት በ1973 ዓ.ም ከከሳሾች አውራሽ ላይ በገዛሁት ባዶ መሬት ላይ ሲሆን የሽያጭ ውሉም አይፈርስም ተብሎ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ከመሆኑም በላይ መሬት የመንግስት ስለሆነ ከሳሾች ክስ በመሠረቱበት ቤት ላይ መብት የላቸውም፡፡ ክርክሩም በይርጋ ስለሚቋረጥ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም የከሳሾች አውራሽና ተከሳሽ ኅዳር 3 ቀን 1973 ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የከሳሾች አውራሽ ጠይቀው ውሉ አይፈርስም የሚል ውሳኔ ስለተሰጠ ከሳሾች ቤቱን ለማስለቀቅ መብት የላቸውም፡፡ ተከሳሽ የሚኖሩት በ1973 ዓ.ም በገዙት ባዶ ቦታ ላይ በሰሩት ቤት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ የተከሳሾች አውራሽ ባልሠሩት ቤት ከሳሾች እንዲለቀቅላቸው ሊጠይቁ አይገባም፡፡ በመዝገብ ቁጥር 01660

ክስ የቀረበው በከሳሾች እጅ የሚገኝ ቤት ለመረከብ ሲሆን በይርጋ ቀሪ ሆኗል የተባለውም ይህንኑ ቤት አስመልክቶ የቀረበውን ክስ በተመለከተ እንጂ ተከሳሽ ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ የምኖርበትን ቤት በተመለከተ አይደለም፡፡ ከሳሾች በማስረጃነት ያቀረቡትን ካርታ በተመለከተ የአራዳ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ሕግና ሥርዓትን ሳይጠብቅ የሠጠው የምስክር ወረቀት በመሆኑ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ይታዘዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኝ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተከሳሽ በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መርምሮ ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን በተመለከተም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት ተከሳሽ ይዘው የሚገኙት ከከሳሾች አውራሽ ጋር በ3/3/73 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል መሆኑን ከቀረበው ማስረጃ ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ይህ ውል ደግሞ አይፈርስም ተብሎ እስከ ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረስ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ በቤቱ ውስጥ የሚገኙት ውሉን መሠረት አድርገው ስለሆነ ከሳሾች ተከሳሽ ቤቱን ይዘው የሚገኙት መብት ሳይኖራቸው ነው በማለት ያቀረቡት ክስ በአግባቡ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሾች በውሳኔው ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቀርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካቾች ክስ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተገቢነቱ በሰበር ታይቶ ሲወሰን እንደሚገባው በመታመኑ ተጠሪን በመጥራት ችሎቱ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት በመ/ቁጥር 01660 ይህንኑ ቤት አስመልክቶ ተጠሪ የውል ይፈጸምልኝ ክስ አቅርበው አቤቱታው በይርጋ ታግዷል ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ በቤቱ ላይ መብት የላቸውም በሚል ነው፡፡

ሆኖም ግን ተጠሪ በመ.ቁ 01660 የውል ይፈጸምልኝ ክስ ያቀረቡት ከከሳሶች አውራሽ ጋር ባደረጉት የሽያጭ ውል ከገዙት ቤት ውስጥ ያልተረከቡትን አንድ ክፍል ቤት በተመለከተ እንጂ አመልካቾች ተጠሪ ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡበትን ቤት እንደማይመለከት ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም ሌላ አመልካቾች ክስ ያቀረቡበትን ቤት ተጠሪ ይዘው የሚገኙት ከአመልካቾች አውራሽ ጋር በ3/3/73 ዓ.ም ባደረጉት የሽያጭ ውል መነሻነት እንደሆነም የተገነዘብን ሲሆን የአመልካቾች አውራሽ በተጠሪና አቶ ለማ ደምሴ በተባሉ ግለሰብ ላይ በ3-3-73 ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል በተንኮል የተደረገና ተገቢውንም የውል አጻጻፍ ሥርዓት ተከትሎ ያልተከናወነ ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል በማለት ክስ አቅርበው እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረስ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

በተጠሪና በአመልካቾች አውራሽ መካከል በ3/3/73 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አይፈርስም ተብሎ አስቀድሞ ከተወሰነ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ይዘው የሚገኙት በዚህ ውል ባገኙት መብት እንደሆነ ከሚቆጠር በስተቀር መብት ሳይኖራቸው ቤቱን ይዘው ይገኛሉ ለማለት ስለማይቻል አመልካቾች ተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክስ የሥር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉት መቅረቱ በአግባቡ እንጂ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 50058 በ27/9/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ.ቁ 71162 በ23-7-2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. ተጠሪ ክስ ከቀረበበት ቤት ሊለቁ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሠ.መ.ቁ 47035

ታህሳስ 6 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች:-** ማስረሻ አበበ ከጠበቃ ሲሳይ ተፈራ

**ተጠሪ:-** የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ደስታ ሲበን

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል::

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ሳይ ባቀረበው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 6 ቀበሌ 03 ክልል የቤት ቁጥር 806 የሆነውን ቤት በወር ብር 125.45 ከሳይ ለመክፈል በመስማማት ጥቅምት 1 ቀን 1978 ዓ.ም በተደረገ የኪራይ ውል ተከሳሽ ከከሳሽ ተከራይተዋል:: ሆኖም ከ1/6/1985 ዓ.ም እስከ 30/1/88 ዓ.ም ድረስ ያለውን ውዝፍ የቤት ኪራይ ያልከፈሉ ስለሆነ ይህንኑ ውዝፍ ከነወለዱ ብር 4548.38 እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል::

ተከሳሽም ቀርበው ቤቱ የግሌ ስለሆነ ኪራይ የምከፍልበት ምክንያት ስለሌለ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል::

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ተከሳሽ የቤቱ ባለቤት ስለሆንኩ ኪራይ ልከፈል አይገባም ቢሉም ቀድሞ የተሰጣቸው ማስረጃ የተሰረዘ ስለሆነ የተጠየቀውን የቤት ኪራይ ከነወለዱ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል::

ተከሳሽም በውሳኔው ቅሬታ አድርባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ሠርዟል::

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ ከ1/6/85 እስከ 30/1/88 ላለው ጊዜ አመልካች ኪራይ እንዲከፍሉ ውሳኔ መስጠቱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024/መ/ አኳያ ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ከተባለበት ነጥብ አኳያ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 17068 በሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ላይ ያለው የሕግ ግምት ተከሳሹ ቀርቦ በመከላከያ መልሱ ካደም አልካደ ዳኞች የክፍያ ግምቱን በራሳቸው በማንሳት ተፈጻሚ ማድረግ እንዳለባቸው በማተት የሕግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በተያዘውም ጉዳይ አመልካች ኪራይ እንዲከፍሉ የተጠየቁት ከ1/6/85 ዓ.ም እስከ 30/1/88 ዓ.ም እንደመሆኑ መጠን በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተጠየቀው በአመልካች ክርክር ባይቀርብበትም አስቀድሞ ከተሰጠው ውሳኔ አኳያ ፍ/ቤቱ የክፍያ ግምቱን ተፈጻሚ ማድረግ ሲገባው በሕግ ግምቱ የማይሸፈነውንም ጊዜ ጨምሮ እንዲከፍሉ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተዋል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 22292 በ2/6/2001 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 78387 በ27/9/2001 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ በማሻሻል ተጠሪ ክስ ካቀረበበት ኅዳር 12 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ኋላ እስከ ኅዳር 12 ቀን 1986 ዓ.ም ያለው ጊዜ በሕጉ ላይ በተቀመጠው የ2 ዓመት ጊዜ የተጠየቀ ስለሆነ የ2 ዓመት የቤት ኪራይ ከነወለዱ እንዲከፈለው፣ ከ11/3/86 ዓ.ም እስከ 1/6/85 ዓ.ም ያለው የክፍያ ጥያቄ እንደተከፈለ የሚቆጠር ስለሆነ አመልካች ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰ/መ/ቁ 47469

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

**አመልካች:-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

**ተጠሪ:-** እነ አቶ ሥዩም ገብረፃዲቅ (22 ሰዎች)

ወኪል ወንድምአገኘ ጌታሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996ን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ሕዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው። የክሱ ይዘትም ባጭሩ ሳልተወሰነ ጊዜ ተቀጥረን ስንሰራ ሌሎች ሠራተኞች የሚያገኙትን የበረሃ አበል፣ ቦነስ፣ የሳምንት ዕረፍት ቀን ክፍያ፣ የኤሌክትሪክ ፍጆታ በነፃ መጠቀም፣ የዝናብ ልብስ ጥቅማ ጥቅም የማግኘት መብት እንዲከበርላቸው እና የደመወዝ እርከንና ማሻሻያ ከሌሎች ጋር እኩል እንዲደረግላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል ስተወሰነ ጊዜ የሚቆይ በሚል የተፈረመ ሆኖ አመልካች ግዴታውን እየተወጣ የቆየ መሆኑን፣ ተጠሪዎች በሳምንት የሚሰሩት የስራ ሰዓት ብዛትም በቀን ከስምንት ሰዓት በታች የሚሰሩ መሆኑን፣ የሚያሳይ በመሆኑ የሳምንት የእረፍት ጊዜ ክፍያ ተቀባይነት እንደሌለው ለቋሚ ሰራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎችም ለተጠሪዎች ሊከፈሉ እንደማይገባ ገልጾ ክሱ ውድቅ ሲሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል። የስር ፍርድ ቤትም በአመልካች በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ ካደረገና የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የስራ ውሉ ሳልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር ነው በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram
https://chilot.me

አመልካች ለተጠሪዎች የሣምንት እረፍት ቀን ክፍያ፣ የበረሃ አበል ክፍያ፣ ነጻ የኤሌክትሪክ፣ ቦነስ ይከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሐምሌ 08 ቀን 2001 ዓ.ም አምስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሁነው እያለና ቋሚ እንሁን የሚለው ጥያቄም የክስ ምክንያት የሌለው መሆኑ እየታወቀ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል ተብሎ ለቋሚ ሠራተኞች የሚገባቸው ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከፈላቸው መወሰኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የቅጥር ውል፣ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 10(1/ሀ) የድርጅቱን የህብረት ስምምነት እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 18832 የሠጠውን አስገዳጅ ውሳኔ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑ እየታወቀ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት አመልካች ድርጅት ለተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ይክፈላቸው በማለት የሠጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር ይገባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ድርጅት አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው በማለት ነው፡፡ ለዚህም መሰረት የሚያደርገው ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና የስራ ውሉ በጊዜ ተገድቦ በግራ ቀኙ መካከል ውል የተፈፀመበትን ሰነድ ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በጡረታ ተገልለው የቆዩ መሆኑን ሳይክዱ በአመልካች ድርጅት ሥራ የጀመሩት የጡረታ ደብተሩን በመመለስና በማስያዝ ስለመሆኑና ይህም በስር ፍርድ ቤት በሚመለከታቸው አካላት የተረጋገጠ መሆኑን፣ እንዲሁም የስራ ውሉ በየጊዜው እየታደሰ ለበርካታ አመታት በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ መቆየታቸው የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ያስቆጥራል በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የቅጥር ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ አመት እየተባለ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና እየታደሰ እንደ አዲስ የሚታይ መሆኑ ይታመናል፡፡ በዚህም መሰረት ጊዜው ሲያልቅ ውሉን ማቋረጥ የሚቻል መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 11924 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ድንጋጌዎችን በመመርመር አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የሠጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰራተኛ ከአሰሪ ሳልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ ሲቆጠር እንደሚገባ ሕጉ ግምት እንደሚወስድ፣ በዚህ የሕግ ግምት የስራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ነው በማለት የሚከራከረው ሠራተኛ ተጠቃሚ በሆኑ ይህን ክርክሩን የመደገፍለት ማስረጃ በቅድሚያ ያቀርብ ዘንድ እንደማይጠበቅበት፣ ይልቁንም በሕግ በተወሰደለት ግምት ክርክሩን ከማስረዳቱ ግዴታው ነፃ እንዲሆን እንደሚያደርገው፣ በውጤቱም በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረጉ ስውሮች በአንቀፅ 10 ስር የሚሸፈኑ ናቸው ሲል በሚከራከር በአሰሪው ላይ የሚወድቅ መሆኑን በመዘርዘር ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ከእዚህ የሰበር ችሎት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው ሰራተኛው በየዓመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻውን ሰራተኛን ለተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ ሲወሰድ የማይገባ መሆኑን ነው፡፡ ዋናው ሰራተኛው የተቀጠረበት ሥራ ቀጣይነት ያለው መሆኑ ነው፡፡ አሰሪው ይህንኑ ለማስተባበል የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 10 ስር የተመለከቱት ምክንያቶች የስራ ውሉ መፈፀሙን በማስረዳት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለማሳያነት ያቀረበው ማስረጃ በ3ኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገ የስራ ውል ሆኖ ውሉ ከሀምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሀምሌ 01 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 10 ስር በተመለከተው ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ለጥበቃ ሥራ የተቀጠሩ መሆኑን በመግለፅ የተፈፀመ ነው፡፡ ተጠሪዎች ሁሉም ለአንድ አይነት ሥራ የተቀጠሩ አስመሆናቸውንም የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ገልባጭ ቢያሳይም የቅጥሩ ዓይነት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን ግን ተጠሪዎችም ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታውን የተወጣ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉ ሆነው በቋሚነት ሲቀጠሩ አይችሉም በማለት ያቀረበው ክርክርም ተጠሪዎች በዕድሜ ጣሪያ በጡረታ የወጡ መሆኑን በዚህ ችሎት በተደረገው የክርክር ሂደት አረጋግጠዋል፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት የጡረታ ደብተራቸውን በመያዝ የመብቱ ተጠቃሚ ሁነው እያለ በአመልካች ድርጅት በመስራት ላይ የሚገኙ ባለመሆኑ ቅጥሩ እንደቋሚ የሚቆጠር፤ ሕጋዊ ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ አሰሪ በጡረታ የተገለለን ሠራተኛ በድጋሚ ሳልተወሰነ ጊዜ ቀጥሮ ያሰራል ለማለት የማይቻል መሆኑን ይህ ሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18832 አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ከመሆናቸውም በላይ እድሜያቸው በጡረታ ደርሶ ከስራ ከተሰናበቱ በኋላ በአመልካች ድርጅት ውስጥ የተቀጠሩ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት እንዲወሰኑላቸው ያቀረቧቸው የክፍያ ጥያቄዎች ለቋሚ ሠራተኞች የሚሠጡ መሆኑን ተጠሪዎችም በክርክራቸው ገልፀው የሚከራከሩት ነጥብ በመሆኑ ተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች ካልሆኑ ክፍያዎቹ የሚገባቸው አይሆንም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑ እየታወቀ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት አመልካች ለተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኛቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን ይክፈላቸው በማለት መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 10 የአመልካች ድርጅት የሕብረት ስምምነትንና ከላይ የተጠቀሱትን የሰበር ችሎት ውሳኔዎችን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19930 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03718 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች በእድሜ ጡረታ ተገልለው ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆኑ አመልካች ለቋሚ ሰራተኞች የሚከፍላቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያገኙበት ወይም ሊከፍላቸው የሚገባ ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የሰበር መ/ቁ 47487

ታህሳስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ታፈሰ ይርጋ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

አመልካች:- አቶ ሀይለራጉኤል ደበሳ - ጠበቃ ገመቹ ሮሮ ቀረቡ

ተጠሪ:- 1. ወ/ሪት አስምፀሀይ ፈስገ
2. አቶ አቦነህ ፈስገ } ጠበቃ ባርናባስ ደስታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይስቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ጥር 13 ቀን 1999 ዓ.ም በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የአመልካች አባት የነበሩት ሟች አቶ ደበሳ ልቡ ከወ/ሮ ክብነሽ ጎንዴል ጋር ጋብቻ ከማድረጋቸው በፊት የነበሯቸውንና ቁጥራቸው 1056/1057 የሆኑት የግል ቤቶች መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ በሕይወት እስከአሉ ድረስ እንዲኖሩ እና እንዲጠቀሙበት ከሞቱ በኋላ ወደ ወራሾች እንዲተላለፍ በማለት መናዘዛቸውን፣ ኑዛዜውም በፍ/ቤት መፅደቁም፣ ኑዛዜው ወ/ሮ ክብነሽ ቤቱን ከፈለጉ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ የሚል ቢሆንም በውርስ እንዲያስተላልፉ የሚያዝ ሆኖ እያለ ለዘመዶቻቸው ማውረሳቸውን ገልፀው ተጠሪዎች ያላግባብ የያዙትን ቤት ለቀው እንዲያስረክቧቸው፣ ተጠሪዎች ለተጠቀሙበት የቤት ኪራይ አመልካች የመጠየቅ መብታቸው ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎችም በተከሳሽነት ቀርበው በሠጡት መልስ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ በሟች አቶ ደበሳ ልቡ ኑዛዜ መሰረት ንብረቱን ወደራሳቸው በማዞር የግል ንብረት በማድረግ ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑና ክሱም ኑዛዜው ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ በመሆኑ እንዲሁም ኑዛዜውን ለመቃወም

የሚቀርብ ክስን ስርዓት ተከትሎ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚሉ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ሟች አቶ ደበላ ባደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ ቤቱን ለመሸጥ፣ ለመለወጥ እንዲችሉ ስልጣን የሚሠጥ በመሆኑ ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ለሌላ የማስተላለፍ መብት አላቸው ንብረቱንም በስማቸው አዙረው ሲጠቀሙበት ቆይተው ግንቦት 27 ቀን 1996 ዓ.ም በውልና ማስረጃ በተደረገ ኑዛዜ ለተጠሪዎች የሰጧቸው በመሆኑ የአመልካች ክስ ውድቅ ሲሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ሟች አቶ ደበላ ልቡ መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዴል በኑዛዜ ንብረቱን ለማስተላለፍ ሥልጣን የሚሠጥ አይደለም፣ የሟች ደበላ ልቡ ኑዛዜ ከወ/ሮ ክብነሽ ጎንዴል ሞት በኋላ ተፈፃሚነት አለው በሚል ምክንያት ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ የቤት ኪራይ በተመለከተ ከቤቱ ጋር ክስ መቅረብ የነበረበት ስለሆነ የአመልካች ወደፊት የመክሰስ መብት ሲጠበቅ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከአከራካሪው ኑዛዜ ይዘት ጋር በማገናዘብ መርምሮ በኑዛዜው ላይ ሟች አቶ ደበላ ልቡ ወ/ሮ ክብነሽ ሕይወቷ እስካለ ድረስ በከፊል ወይም በሙሉ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ልትሸጥና ልትለውጥ ትችላለች፣ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ወራሾቿ ወይም ወራሾቼ እርሷ ፈቅዳ ካልሰጠቻቸው ሊቃወሟት አይችሉም በሚል ያስቀመጡ ስለሆነና ይህ የተናዛዡ ሀሳብ የሚያስገነዝበው ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ካልፈቀዱ በቀር ቤቱን ለፈለጉት ሰው ቢሰጡ ከኑዛዜው መልዕክት ውጪ እንዳደረጉ የሚያስቆጥር አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሟች አቶ ደበላ ልቡ ባደረጉት ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዴል ንብረቱን ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ትችላለች ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ በኑዛዜ ለሌላ ሰው መሥጠትን ያጠቃልላል ተብሎ የተተረጎመው ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ይችላሉ የሚል ግልፅ የሆነ ቃል እንጂ ለሌላ ሰው ጥቅም ንብረቱን እንዲለውጡ ወይም እንዲሸጡ የሚል መልዕክት የሌለው ግልፅ ቃል ሆኖ እያለ ይህንኑ ግልፅ ቃል በሚጻረር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me join telegram

መልኩ መተርጎሙ ያሳግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ሟች አቶ ደበሳ ልቡ ያደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ሊሸጡ፣ ሊለውጡ እንጂ እርሳቸው በኑዛዜ እንዲያስተሳልፉ የሚያስችላቸው እንደሆነ ተደርጎ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መስከረም 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ንብረት የሟች አቶ ደበሳ ልቡ የግል ንብረት መሆኑን ተጠሪዎች አለመካዳቸውን፣ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል የሟች አቶ ደበሳ ልቡ ሚስት የነበሩ መሆኑን፣ አቶ ደበሳ ልቡ ለወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም የተደረገ ኑዛዜ የተውላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ ኑዛዜም በከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1553/59፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ በመ/ቁጥር 70/62 ማስፀደቃቸውን፣ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ግንቦት 27 ቀን 1996 ዓ.ም ውል እና ማስረጃ ክፍል ባደረጉት ኑዛዜ ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት ለ2ኛ ተጠሪ፣ ለወ/ት ትዕግስት ፈለገ፣ ለወ/ት ኩሳገር ፈለገ፣ ለወ/ት ወለሳ ፈለገ፣ ለወ/ት ሙሳቷ ፈለገ እና ለሕፃን ዮሴፍ እንዳሳ ፈለገ የተናዘዙላቸው መሆኑን ነው፡፡ አከራካሪው ነጥብ ሟች አቶ ደበሳ ልቡ በተውት ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ንብረቱን ከፍጻሜ ሕይወታቸው በኋላ በኑዛዜ ለሌላ ሰው የማስተሳለፍ መብት/ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ወይስ አልተሰጣቸውም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ለጉዳዩ እልባት መስጠት ይቻል ዘንድም ሟች አቶ ደበሳ ልቡ መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ቃል አግባብነት ያለውን ክፍል ተመልክተናል፡፡ ይኸው የኑዛዜ ክፍል "*የሰጠኋትን ቤት ከነቦታው ሕይወቷ እስካለ ድረስ በከፊል ወይም በሙሉ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ልትሸጥ ልትለውጥ ትችላለች፣ በዚህን ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ወራሾቿ ወይም ወራሾቼ እርሷ ፈቃዳ ካልሰጠቻቸው ሊቃወሟት አይችሉም፣ ..... ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃል የሰጠኋትን ሀብትና ንብረት ለውጣ እራሷ የምትጦርበት ሲሆን ከርሷ የተረፈ ቢኖር ግን ውርሱ ለልጇ አርያና ለልጅ ልጇ ለኃይለራጉኤል መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከቀሪው ሀብቴ ጋር አንድ ላይ ተደባልቆ ከኔ በተወለዱት ማለት ከሙሉነሽ ላይ ለወለድኳቸው ልጆች ብቻ ከክብነሽ የማደጎ ልጆቿ ጋር እንደየድርሻቸው ሊከፋፈሉ ይችላሉ .....*" በሚል የተቀመጠ ነው፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ ሲተረጎም የሚገባው ቃላቶቹ እና መልእክቱ ግልፅ ሳይሆን ሲቀር ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ኑዛዜው ግልፅ ቃላቶችንና መልዕክትን የያዘ ከሆነ ትርጓሜ መስጠት አያስፈልግም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ይህንን መሰረታዊ መርህን መከተል ያስብን መሆኑን ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(2) ድንጋጌ በግልፅ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የኑዛዜው ቃል መተርጎም ያለበት ስለኑዛዜው መልእክት ጥርጣሬ በሚፈጥርበት ጊዜ አሻሚ ወይም ግልፅ ያልሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህን ደንብ ተፈጻሚ የሚሆንበትን መንገድም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(1)፣ 911፣ 925 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ያሳዩናል፡፡ ስለሆነም የኑዛዜው ቃላት ግልፅ የሆኑ እንደሆነ የተናዛዡ እውነተኛ፣ ትክክለኛ ፈቃድ የትኛው ነው ብሎ ትርጓሜ መስጠትና ከኑዛዜው ቃል መራቅ የማይፈቀድ ስለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሟች አቶ ደበላ ልቡ ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል በሕይወት እስካሉ ድረስ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ የሚያስችላቸው እንጂ ከራሳቸው ጥቅም ውጪ ለሌላ ሰው በኑዛዜ እንዲያስተላልፉ የሚይስችላቸው አለመሆኑን ከላይ የተገለፀው የኑዛዜ ክፍል ያሳያል፡፡ በመሆኑም ይኸው የኑዛዜ ክፍል የሟች ፍላጎትና መልዕክት ግልፅ የሚያደርገው ሆኖ እያለ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የኑዛዜውን አንደን ክፍል ብቻ ነጥሎ ትርጉም የሠጠው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን የኑዛዜ አተረጓጎም መርህን ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 60988 ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 44232 ሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15647 ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram
https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ 48266

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ታምሩ ደሳለኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ምትኩ መንግስቱ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ይዞታ ክርክር ነው ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በቀበሌ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር የቅሬታ ኮሚቴ የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በቄጳ ቀበሌ ቀጠና ውስጥ የባህር ዛፍ ተክል ለመትከል ከቀበሌ አስተዳደር በሕጋዊ መንገድ የተመራሁትን ቦታ ተጠሪ ድንበር አልፎ በመያዝ እንዳልሰራ በማድረግ ሁከት ስለፈጠረ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ቀርበው በጉዳዩ በማሻ ወረዳ ፖሊስ ምርመራ ክፍል ቀርቤ ታስሬ ስለወጣሁ እና በወረዳ ፍርድ ቤትም ስለተያዘ በዚያው በኩል የሚያልቅ ነው በማለት መልሳቸውን የሠጡ ስለመሆኑ ቅሬታ ሰሚው አካል የመዘገበው የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ቅሬታ ሰሚ አካልም የሕግ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ ተጠሪ በአመልካች ቦታ ላይ መግባታቸው ተረጋግጧል በማለት ማሳውንና የተከሉትን ቡና ጭምር ለአመልካቹ ሊለቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ለቄጳ ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሠጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ ለማሻ ወረዳ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ውሳኔ ጸንቷል፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ ይግባኛቸውን ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤቶች ይርጋንና ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት የተከራከሩ መሆኑን በመግለፅ ተጠሪ በእጁ ከሁለት ዓመታት በላይ አድርጎ ቡና ያስማበት መሆኑ

ተረጋግጧል የሚል ምክንያት በመያዝ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሠጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር የቀረበለት የዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ውሳኔውን አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ይርጋንም ሆነ የመከላከያ ማስረጃ አንስቶ ባለተከራከረበት ሁኔታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ከዚያ በላይ ያሉት ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ይርጋን መሰረት አድርገው ውሳኔ መስጠታቸው ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የይርጋ ክርክር በተጠሪ ሳይነሳ ውሳኔ መስጠቱ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መስከረም 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊታይ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪውን የመሬት ይዞታ አመልካች በሕጉ አግባብ ከተሠጣቸው በኋላ ሊጠቀሙበት ባለመቻላቸው በደን ተሸፍኖ እንደቆየ እና ተጠሪ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ መሬቱን በመያዝ ቡና ተክለው ያለሙት መሆኑ መረጋገጡን፣ ተጠሪ የይርጋ ክርክር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት በአግባቡ መመሬት ከአለባቸው የወረዳ ፍርድ ቤት እና ከዚያ በላይ ባሉት አካላት አንስተው የተከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ የይርጋውን ክርክር በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም አንስተው የተከራከሩ ስለመሆኑ የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ ያረጋገጠው ነጥብ ሲሆን ከዚያ በላይ ያሉት ፍርድ ቤቶችም የዞኑ ፍርድ ቤት የይርጋ ክርክር ተነስቷል በማለት የገለፀውን ነጥብ እንዳለ በመቀበል ውሳኔ የሠጡበት ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የይርጋውን ክርክር በተገቢው የዳኝነት አካል ዘንድ ያቀረቡት መሆኑን በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ሆኖ ስለአገኘን በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03493 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁጥር 22151 ሐምሌ 19 ቀን እንዲሁም በዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 23718 መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

የፍ/ይ/መ/ቁ 50157

ታህሳስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች:- አሰግድ ጋሻው

ፀጋይ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

**ይ/ባይ:-** አቶ ንጉሴ መላኩ

**መ/ሰጪዎች:-** 1. የቀድሞ ወረዳ 08 ቀበሌ 06 መስተዳድር ፅ/ቤት የአሁኑ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 19/20 ፅ/ቤት - ቀርቧል

2. አቶ ከድር ናስር - ቀርበዋል

3. " ምህረት ተካ - በሌሉበት

4. " ተስፋዬ ነጋሶ - ቀርበዋል

ጉዳዩ ተመርምሯል፤ የሚከተለውም ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍ ር ድ

ይግባኙ የቀረበው ይ/ባይ ጥቅምት 30/2002 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው ክስ ሳቀረብኩበት የቤት ጉዳይ በመጀመሪያ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጳውሎስ ምድብ ችሎት የካቲት 03/1991 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩ የአ.አ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ስልጣን እንጂ እኔን የሚመለከት አይደለም ብሎ መዝገቡ ወደ ከተማ ነክ ፍ/ቤቱ ቢያስተላልፍበትም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 09058 ነሐሴ 27/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩ የማየት ስልጣን እንደሌለው በመግለፅ መዝገቡ ስለዘጋብኝ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 ዓንቀፅ 42(1) መሠረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው እንደሆነ ይወሰንልኝ በማለታቸው ነው:: ይ/ባዩ በዋና ጉዳዩ ያቀረቡት ጥያቄም በወረዳ 08 ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 144 ተብለው የሚታወቁትን አራት ክፍል ቤቶቼ ያልተወረሱና የግል ቤቶቼ ሆነው እያስ መልስ ሰጪዎቹ አከራይና ተከራይ በመሆን ስለተዋዋሉ ቤቶቼ ያስረክቡኝ የሚል ነው::

2ኛ እና 4ኛ መልስ ሰጪዎች ህዳር 22/2002 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው ይህ አይነቱ ጉዳይ በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 29502 ሃምሌ 10/2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የአ.አ ከተማ ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁ 361/95 ዓንቀፅ 41(1)(ረ)

መሠረት ስልጣን የሚኖራቸው ከባለቤትነት ውጭ ያሉ ክርክሮች እንደሆነ ማለትም የቤት ባለቤትነት አከራካሪ ወይም ክሱ የባለሃብትነት ጥያቄ የሚያስነሳ በሆነ ጊዜ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው በአዋጅ ቁጥር 25/88 ዓንቀፅ 14(1) መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንደሆነ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 454/97 ዓንቀፅ 4 መሠረት ይወሰንልን ብለዋል፡፡

3ኛው መልስ ሰጪን በተመለከተ ክርክሩ በሌሉበት እንዲካሄድ ህዳር 22/2002 ዓ.ም ትእዛዝ የተሰጠበት ስለሆነ የሰጡት መልስ የለም፡፡

1ኛ መልስ ሰጪውም ህዳር 22/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተካሄደው የቃል ክርክር መልስ የሰጠ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም አከራካሪው ቤት የይ/ባዩ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ካርታም ሆነ ሌላ ሰነድ የለም፤ በክፍት ቦታ ቤት መስራታቸውም ባለቤትነት አይፈጥርላቸውም፤ የንግድ ቤቶቹ ከይ/ባይ ይዞታ ውጭ ናቸው የሚል ሲሆን 2ኛ መልስ ሰጭም በዚሁ የቃል ክርክር በሰጡት መልስ ቤቱ ከይ/ባይ ተከራይተን ነበር፤ ቀበሌ ግን ኪራይ ለእኔ ክፈሉ ካልሆነ አስወጣችኋለሁ አለን፤ እኔም ይ/ባይ የሰጠኃቸው ኪራይ እንዲመልሱልኝ ጠየቅኳቸው፤ እሳቸውም ቤቱ ቀበሌው ከሚያሸገው ለጊዜው ከቀበሌው ጋር ብስማማ የተሻለ እንደሆነ ተማምነናል ብለዋል፡፡

የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር በአጭሩ ከላይ እየተዘረዘረ እንደመጣው ሲሆን ይህ ፍ/ቤትም ይህንን ጉዳይ የማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የትኛው ነው? የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወይስ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከዚህ ክርክር መረዳት እንደሚቻለው በይ/ባይና በ1ኛው መልስ ሰጪው መካከል በአከራካሪው ቤት ላይ የባለቤትነት መብት ያለኝ እኔ ነኝ በሚል ያለ መስማማት እንዳለ ነው፤ ማለትም ቤቱ በአዲስ አበባ መስተዳደር ስር ባለው በ1ኛው ተጠሪ ባለቤትነት ስር ስለመሆኑ ግራቀኙ ወገኖች አልተማመኑም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ ጉዳዩን የማከራከሩ ስልጣን የፌደራል ፍርድ ቤቶች እንጂ የአዲስ አበባ ፍ/ቤቶች ስልጣን አይደለም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 29502 ሃምሌ 10/2000 ዓ.ም በሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ በሰጠው ፍርድ አረጋግጧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ ያሳረፈባቸው ጉዳዮች ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 4 መሠረት እንደ ተመሳሳይ ጉዳዮች እንደ ህግ ሆነው የሚቆጠሩና ገዢ ናቸው፤ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 09058 ነሐሴ 27/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) በማፅናት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጳውሎስ ምድበ ችሎት በመ/ቁ 4190 የካቲት 03/1991 ዓ.ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡
2. ጉዳዩን አከራክሮ የመወሰን ስልጣን ያለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፤ ጉዳዩን አከራክሮ እንዲወሰን ይፃፍለት፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ፤ ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሬ/ታ

https://chilot.me
https://t.me/ethiopianlegalbrief
join telegram

የሰበር መ/ቁ 45266

ታህሳስ 13 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ምንዳየሁ ግርማ ከሊሳ ቀረበች

**ተጠሪ፡-** ዋና ሳርጀንት ሰጌ ሳንታ - መቅደስ ሰጌ ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ሃብት ይገባኛል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ አመልካችን የከሰሰው በወራሽነቴ ከአባቴ የተሳለፈልኝ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘው ቁጥር 483 የሆነውን ቤት ከሕግ ውጪ ይዛ ስለምትገኝ እንድትለቅልኝ በቤቱ በመቀመጥዋም ኪራይ እንድትከፍለኝ በማለት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠችው መልስ ቤቱ የከሳሽ አባት እና የአክስቴ ወ/ሮ ወደሬ ከሊሳ የጋራ ንብረት ነው፡፡ ሁለቱ ሰዎች በሃገር ባህል መሠረት ጋብቻ መስርተው አብረው ሲኖሩ የነበሩ በመሆናቸው ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት እንጂ የከሣሽ አባት የግል ሃብት አይደለም በማለት ተከራክራለች፡፡ ከዚህ በመቀጠል ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር የመረመረ ሲሆን፣ በመጨረሻም ቤቱ የከሳሽ አባት (አውራሽ) የግል ሃብት ስለሆነ ተከሳሽ ቤቱን ለቃ ለከሳሽ ታስረክብ፡፡ ተከሳሽ በየወሩ ብር 320 እያከራየች ከታህሳስ 14 ቀን 99 ዓ.ም ጀምሮ የተጠቀመችበትና ቤቱን ለቃ ለከሳሽ እስክታስረክብ ድረስ በየወሩ ብር 320.00 ሂሳብ ትክፈል፡፡ በእጅዋ ያለው የቤት ባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቁጥር 11/16709 ለከሳሽ ታስረክብ በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የበኩሉን ክርክር ከሰማ በኋላ ይግባኙ የተባለበትን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ሳይ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ ሳይ ተፈጽሞአል የምትለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታዋን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

አቅርባለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰ ነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የተጠሪ አባት የግል ሃብት ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

አከራካሪው ቤት የተሠራው የተጠሪ አባትና የአመልካች አክስት ከመጋባታቸው በፊት በ1948 ዓ.ም ነው የሚል ክርክር በተጠሪ በኩል የተነሳ ቢሆንም፣ የተጠሪ አባትና የአመልካች አክስት ከ1959 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስረው በተባለው ቤት ውስጥ ሲኖሩ እንደነበረ ግን አላከራከረም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ቤቱ እየፈረሰ ሲታደስ እንደነበረ የሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ምስክሮች በሰጡት ቃል ተረጋግጦአል፡፡ ቤቱን በተመለከተ ከአስተዳደር ክፍሉ የተሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርም በባልና ሚስቱ ስም የተመዘገበ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካች የአክስትዋ ወራሽ አይደለችም የሚል ክርክር ከተጠሪ አልቀረበም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ በቤቱ ኖሮ እንደማያውቅ አመልካች ግን እቤቱ ውስጥ ከባልና ሚስቱ ጋር አብራ ትኖር እንደነበርና አስታማ የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ያስፈጸመችው እስዋ ስለመሆንዋ በክርክሩ የተመለከተ ሲሆን፣ በተጠሪ ማስተባበያ አልቀረበበትም፡፡ የአመልካች አክስት እና የተጠሪ አባት ሐምሌ 28 ቀን 87 ዓ.ም ቤቱን አስመልክተው ያደረጉት በአራት ምስክሮች የተረጋገጠ ስምምነት እንዳለም ተመልክተናል፡፡ በዚህም ባልና ሚስቱ ቤቱ የጋራ ንብረታቸው እንደሆነ ተማምነው ተፈራርመዋል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ቤት የተጠሪ አባት የግል ንብረት ሳይሆን፣ የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት መሆኑን የሚያረጋግጡ አግባብነትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ለፍ/ቤቱ ቀርበውለታል፡፡ ሐምሌ 28 ቀን 87 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት በተጠሪ በኩል በቀረበው ክርክር እንደተገለጸው ለፍ/ቤት ቀርቦ አልፀደቀም ቢባልም በአስረጂነቱ ግን ዋጋ የለውም የሚባል አይደለም፡፡ ባልና ሚስቱ ያለፈውን የብዙ ዓመታት የጋብቻ ዘመናቸውን እግምት ውስጥ በማግባት ያደረጉት መቋጫ የሚያመለክት በመሆኑ አስረጂነቱ ከፍ ያለ ዋጋ ያለው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ሰነድም ባይኖር ኖሮ ሌሎቹ ሁኔታዎችም ሲታዩ በእርግጥም ቤቱ የተጠሪ አባት የግል ሃብት መሆኑን የሚያሳዩ ስላይደሉ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በቂ የሕግ መሠረት ያለው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሳም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

https://t.me/ethiopianlegalbrief
https://chilot.me
join telegram

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 25339 ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 74280 ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አከራካሪው ቤት የተጠሪ አባት እና የሟች አክስት የጋራ ሃብት ነው ብለናል፡፡ በዚህ መሠረትም አመልካች ተጠሪ ከአባቱ ሊያገኝው የሚገባውን የውርስ ድርሻ እና ጥቅም ታካፍለው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ